## ምዕራፍ አሥር

# በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም አቅጣጫዎች

“ስለአፍሪካ አንድነት ማህበር የሚናገሩትን ሰዎች የም ጠይቃቸው ፥ ምናችንን ለመካፈል ነው? የየአንዳንዳች ንን ድህነት?

—ፕሬዚዳንት ሁፌት ቡዋኚ
(አይቮሪኮስት)

“በጊኒ በመጀመሪያዎቹ ሃያ ዓመታት ያተኮርነው የሕዝ ባችንን አስተሳሰብ በማዳበር ነው ። አሁን ወደሌላው ጉዳይ ለመሸጋገር ዝግጁ ነን ።

—ፕሬዚዳንት አህመድ ሴኩ ፡ ቱሬ(ጊኒ)

አይቮሪ ፡ ኮስትና ጊኒ በምዕራብ አፍሪካ ከሚጋሯቸው ነገሮች አንዱ የጋራ ድንበር ነው ። ሁለቱም የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት የነበሩ ናቸው ። ሁለቱም የእርሻ ልማትን የላቀ ግምት ሰጥተውታል ። የፖለቲካ መረጋጋትም ነበራቸው ። ሁለቱም የኢኮኖሚ እድገት ፥ የግለሰብ ክብርና በራስ መተማመንን ብሔራዊ ግብ ለመጨበጥ ይታገላሉ። ነፃነታቸውን የተቀዳጁትም በሁለት ዓመት ልዩነት ነው ። ጊኒ በ1958 ፥ አይቮሪ ኮስት ደግሞ በ1960 ።

በቅኝ አገዛዝ ማከተሚያ ግድም ጊኒ ሀብታም አገር ነበረች ። በጥቁር አፍሪካ ከሁሉም የበለፀገች ሀገር ትሆናለች ብለው ብዙዎች ይናገሩ ነበር ። በከርሰ ምድርዋ በዓለም ካለው የቦክሳይት ክምችት አንድ ሶስተኛውን አቅፋ ነበር ። በአፍሪካ ግንባር ቀደም ሙዝ አምራችና ላኪም ነበረች ። ከለም መሬቷ የሚመረተው አብዛኛዎቹን

በምዕራብ አፍሪካ የሚገኙ የፈረንሳይ ቅኝ አገሮች ይመገብ ነበር። ሁለት ቢሊዮን ቶን የሚገመት ጥራት ያለው ቦክሳይት የነበራት ሲሆን፣ ብቂ አልማዝና ወርቅም ነበራት። ሶስቱ ታላላቅ ወንዞችዋ ለኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫ እጅግ ምቹ ነበሩ። ዋና ከተማዋ ኮናክሪ በደሴቶችና በውቅያኖስ የተከበበች የምታምርና የፈረንሳይ ቱሪስቶችን የምትስብ ነበረች። የባህር ዳርቻ አሸዋማ መዝናኛው አካባቢ በዘምባባ ዛፎች የተዋበ ነበረ። ምቹ የሆኑ ውብ ሆቴሎችም ነበሩ።

አይቮሪኮስት ይህን የመሰለ መልካም ሀብት አልነበራትም። ወደቦችዋም ምቹ አልነበሩም። የማዕድን ክምችትም ስላልነበራት የመጀመሪያዎቹን የአውሮፓ መጤ ሠፋሪዎች ተስፋ አስቆርጧቸው ነበር። ስለዚህም ወደምሥራቅ በመግፋት ጋና ምድር ውስጥ መኖርን መረጡ። በደቡብ ምዕራብ ያለው ጥቅጥቅ ጫካ የሚደፈር አልነበረም። በሰሜን ያለው ደረቅ መሬት ደግሞ ከአቧራ ሌላ ምንም አልነበረውም። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ላይ አይቮሪ ኮስት ከቡና በስተቀር ሌላ የረባ የውጭ ምንዛሪ ምንጭ ስላልነበራት ብዙዎቹ በምፅዋት የምትኖር ሀገር ትሆናለች ሲሉ ነበር።

ትንበያው ግን ስህተት ሆነ። ሁለቱ ሀገሮች ጊኒና አይቮሪ ኮስት ነፃ እንደወጡ የተለያዩ የእድገት አቅጣጫዎችን ያዙ። ጊኒ የማርክሲዝምን ፈር ተከተለች፣ አይቮሪ ኮስት ደግሞ ካፒታሊዝምን መረጠች። በሁለቱም ሀገሮች የፖለቲካ ሥርዓቱን የመረጡት ፕሬዚዳንቶች ናቸው፤ በሕዝቦች ውሳኔ የተመረጠ አልነበረም። ከሃያ ዓመት በፊት የተደረጉት እነዚህ የተለያዩ ምርጫዎች የሚያስደንቅ የተለያየ ውጤት አስገኙ። በሶስተኛው ዓለም የርዕዮተ ዓለም ሚናና ፕሬዚዳንት ብቻ የአንድ ሀገርን የወደፊት የዘመናት እድል ለመወሰን ሥልጣን ያለው የመሆኑን ጉዳይ ለማጤን የሚያስገርም ምሳሌ ነው።

ፕሬዚዳንት ፈሊክስ ሁፌት ቡዋኚ አይቮሪኮስትን የመሩት በእርጋታና በማስተዋል ሲሆን፣ ለገድያ ያሴሩባቸውን ሳይቀር ይቅር የሚሉና ሕዝባቸውን በርጋታ እንዲራመድ የሚመክሩ ነበሩ።

ካቶሊክ ክርስቲያን የሆኑት ቡዋኚ ከአተካራ ይልቅ ውይይት



ብዙ ችግሮችን እንደሚፈታ በመገንዘብ ከደቡብ አፍሪካ መንግሥት ጋር ሳይቀር በምሥጢር ይወያዩ ነበር። ፈረንሳይን ስለሚወዱ የዓመት ዕረፍታቸውን የሚያሳልፉት ፓሪስና ስዊዘርላንድ በሚገኘው መሬታቸው ነው። በአፍሪካ ፖለቲካ እየተዘወተረ የመጣውን የተራማጆች መፈክርና ድንፋታ ይነቅፉም ነበር። አይቮሪ ኮስት የምትደብቀው ነገር የላትም በሚል ሁሉንም ጋዜጠኞች መግቢያ ቪዛ እንዲያገኙ ይፈቅዱ ነበር። እውነትም አንድም ሰው ስላላስገደሉና የፖለቲካ እሥረኛም ስለሌላቸው የሚደብቁት ነገር አልነበራቸውም።

ሁፌት ቡዋኚ አገራቸውን ለፈረንሳይ ሸጠዋል፤ በሚል ሂስ የሚሰነዝሩባቸው ሰዎች ባይታጡም እሳቸው ግን የፈረንሳይን ሀብትና የተማረ ኃይል ለአገራቸው ጥቅም ለማዋል በዝቅተኛ አንፃራዊ ወጪ ተጠቀሙባቸው እንጅ አገራቸውን አልሸጡም። አፍሪካዊ አለባበስ በመምረጥ የውሸት ሀገርወዳድ ለመምሰልና በፈረንጆች ላይም ርባና የሌለው አጉል ጥላቻ ለማሳየትም አልቃጡም። ማንነታቸውን በትክክል የሚያውቁ ሰው ናቸው። አይቮሪኮስት ተዓምራዊ እድገት አሳይታለች። ዋና ከተማዋ አቢጃን የተዋበችና ንጽህናና ሥርዓት ጠብቃ ያደገች የተለያዩ ዜጎች መኖሪያ ሆናለች። መንገዶቿ ሆቴሎቿ፣ ከየትኛውም የአፍሪካ ሀገር ቢሻሉ እንጅ አያንሱም። ከደቡብ አፍሪካ በስተቀር በሌላ የጥቁር አፍሪካ አገር የሌለ ሰው ሰራሽ የበረዶ መንሸራተቻ አስገንብታለች። ያልተቋረጠ ተከታታይ እድገት በመቀዳጀት ነዳጅ ከሌላቸው የጥቁር አፍሪካ አገሮች በአንደኝነት የምትጠቀስ ናት። የቱሪስት መጉረፊያ በመሆንዋ ከዚህም በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠር ገቢ ታገኛለች። እድገቷ ላይ ላዩን የሚታይና ሥር ያልሰደደ፣ በፈረንሳዮች መኖር የተፈጠረ እንጅ በገጠር ዘልቆ መሠረት ያለው ልማት አይደለም ሊባል ይቻል ይሆናል። እንዲያም ሆኖ ከብዙዎች አገሮች ይልቅ በአርአያነት የሚታይ መሠረተ ልማት ተዘርግቷል። ይሁን እንጅ በአንድ ፓርቲ ሥርዓት ዲሞክራሲ አለ ማለት ይቻላል ወይ ብለው የሚጠይቁም አሉ።

አይቮሪ ኮስት በመከላከያና ዋጋ በሌላቸው ፕሮጀክቶች ላይ ብዙ በጀት ባለመመደብ ለትምህርት ከበጀትዋ ሃያ በመቶ በመስጠት

የትምህርት እድል ከ22% ወደ 55% እንዲያድግና የተማረው ሕዝብ
ቁጥርም ወደ 60% እንዲመጥቅ አድርጋለች ። ይህም በአህጉሪቱ ካለው
አማካይ ግምት በእጥፍ ድርብ ይበልጣል ። የምርትና የአገልግሎት
ተቋሞች እድገት የሚደነቅ ሲሆን ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢም ከነ
ፃነት ወዲህ ከሰባ ዶላር ወደ አንድ ሺህ ዶላር አድጓል ። ይህም ከደ
ቡብ አፍሪካና ከሲሼልስ በስተቀር ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች (ነዳጅ
አምራቾችን ሳይጨምር) የሚበልጥ ነው ። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች
አገሪቱ በእግሮቿ የቆመች በመሆንዋ የአሜሪካንን የልማት ርዳታ
ለማግኘት አልቻለችም ።

የእርሻ ምርቶችን አይነት በማበራከትም አይቮሪ ኮስት ከአፍ
ሪካ አገሮች አንዷዋ ናት ። የኢኮኖሚዋ መሠረት በመሆኑ የቡና ምር
ትን በሶስት እጅ በማሳደግ ፤ ስኳር ፤ የደን ውጤት ፣ ሙዝና ሌላም
ፍራፍሬ በብዛትና በጥራት በማምረት ገቢዋን አዳብራለች ። በአገ
ሪቱ ሰሜናዊ ክፍል ያለውን ደረቅ መሬት ለሸንኮራና ስኳር ማም
ረቻ በመጠቀም ፣ የደቡቡን ረግረግ ምድር ለሙዝና ፍራፍሬ ልማት
በማዋልና የደቡብ ምዕራቡን ጥቅጥቅ ደን ለእንጨት ሽያጭና ዛፍ
ተከላ በመጠቀም ሁሉም የገቢ ምንጭ እንዲሆን አድርጋለች ። አሸ
ዋማውን መሬት ቆፍረው ሰፊ ቦይ በመሥራትም በአቢጃን ሰው
ሠራሽ ወደብ እንዲሠራ አድርጋለች ። በአጭሩ አይቮሪ ኮስት ያሳየ
ችውን እድገት ዓይነት ያከናወነች አፍሪካዊት ሀገር ኬንያ ብቻ ስትሆን
ሌላው በወሬ ብቻ ቀርቷል ።

ሆፌት ቡዋኚ ለውጭ ባለሀብቶች አገሪቱን ክፍት በማድረግ
ልማት እንዲፋጠን በማድረጋቸው አይቮሪ ኮስትን ለእጅ አዙር ቅኝ
አገዛዝ አጋልጠዋል የሚሏቸው አሉ ። ያለቅጥ በብሔራዊ ስሜት ሳይ
ዋጡ ይህን በማድረጋቸው በበኩላቸው ለአገሪቱ እድገት አስገኝቻ
ለሁ ይላሉ ። በእርግጥም በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ ማተኮራቸውና
ከዚያም ቀጥሎ በመገናኛ ፣ በኃይል ምንጭ ፣ በወደቦች ግንባታና
በአውራ መንገዶች ሥራ ላይ ቅድሚያ መስጠታቸው ትክክለኛ የት
ኩረት አቅጣጫ ነው ።

የአፍሪካ ተራማጅ ነን ባይ ወጣቶች ሁፌት ቡዋኚን ቡርዥዋ፤



የፈረንሳይ ቲፎዞና አብዮተኛ ያልሆኑ መሪ አድርገው ይነቅፏቸዋል ።
ያስገኙዋቸው የልማት ውጤቶች ግን ከአብዮት ያነሱ አይደሉም ።
ያውም አንድም ሰው ያልሞተበት አብዮት አንድም ዜጋ በፖለ
ቲካ ስደተኝነት ያልተባረረበት አብዮት ነው ። ሁሉንም ችግር በኃ
ይል ሳይሆን በውይይት መፍታትን በመምረጥ ለአገራቸው ብዙ
ውጤት እንዳስገኙ ይናገራሉ ።

ሆፌት ቡዋኚ በእርቅና በመተሳሰብ የሚያምኑ በመሆናቸው
በብዙ አጋጣሚዎች በአፍሪካ ተሰምተው የማያውቁ የምሕረትና
የይቅርታ ርምጃዎችን በመውሰድ ለግድያ ያመፁባቸውን ሳይቀር
መክረውና አለዝበው በምህረት በመልቀቅ ለሀገራቸው የሚ
ጠቅሙ ዜጎች አድርገዋቸዋል ። ለምሳሌ በ1961 የመንግሥት ግልበጣ
ሙከራ ያደረጉ የጦር መኮንኖችን ፕሬዚዳንቱ በየቀኑ በመጎብኘት
ስረጅም ጊዜ በማወያየት ስህተታቸውን አሳምነው በምህረት እንዲ
ለቀቁ አድርገዋል ። እስር ቤት እየተመላለሰ ከተቃዋሚዎቹ ጋር ለብዙ
ሰዓቶች የተወያየ አፍሪካዊ መሪ ማነው? ከአምስት ዓመት በኋላ ደግሞ
በሌላ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ የተሳተፉና ሲጓኟቸው የነበሩ
ባለሥልጣናትን በማነጋገር እንዲሁ ሶስት ሚኒስትሮችንና ዘጠና ሶስት
ሌሎች ባለሥልጣናትን በነፃ ለቀዋል ። ሌሎች እሥር የአድማው መሪ
ዎች የተበየነባቸውን የሞት ፍርድ ውሳኔ ወደ ስድስት ዓመት እሥር
በመቀነስ አስተያየት አድርገዋል ። ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የነበሩትን
ጆን ሞኪ በማወያየትና ከእስር ሲወጡም ወዳጅ በማድረግ በልጃቸው
ሠርግ ላይ ከመገኘታቸውም በላይ በኋላ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር
አድርገዋቸዋል ።

በ1977 የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ትምህርት ሲያቆሙ ሆፌት
ቡዋኚ ሌሎች የአፍሪካ መሪዎች እንደሚያደርጉት ወታደር አልላኩ
ባቸውም ። ሶስት ቀናት ሙሉ ተማሪዎችን በማወያየት ቅሬታቸውን
አዳመጡና መረመሩ ። ከዚያም አሳምነው ወደ ትምህርት ገበታቸው
እንዲመለሱ አደረጉ ። ።

የአይቮሪ ኮስት ሕዝብ ጭቆናና ጭፍጨፋ ብሎም እሥራት
በመፍራት አልተሰደደም ። ይልቁንም ከአገሪቱ 8,000,000 ሕዝብ

ውስጥ አንድ አራተኛው ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ተሰድዶ በመምጣት አይቮሪ ኮስትን ሀገሩ ያደረገ ነው ። ብዙዎቹም በልማት ጣቢያዎች ሥራ ፍለጋና ገንዘብ ለማፍራት የመጡ ናቸው ። በዚህም በአንድ የምርት ወቅት እስከ ስምንት መቶ ዶላር ያገኙ ነበር ። ከዚያም በአገራቸው የማያገኙዋቸው ብዙ ሸቀጦችን ገዝተው ይመለሱ ነበር ።

እኒህ ሰው ለአይቮሪኮስት የማደግ ዕድል ቢያስገኙላትም ይህ ውጤት የተገኘው በፈረንሳይ ካፒታልና የሰው ኃይል ጥምር ነው። በአገሪቱ የፈረንሳዮች ቁጥር ከነፃነት ወዲህ አምስት እጅ እየጨመረ ሄዶ ወደ 50,000 አድጓል ፤ ተሰሚነታቸውም እንደዚያው ነው ። የተማረ ሰው በሚያስፈልግበት ቦታ ሰማንያ በመቶውን የያዙት ፈረንሣዮች ናቸው ። ከአገሪቱ ኢንዱስትሪ ልማት አርባ በመቶ ፤ ከንግዱ ሃምሳ በመቶ ፤ ይዘዋል ። የእርሻው ክፍል በሀገሪቱ ዜጎች የተያዘ ቢሆንም በሌላው ሁሉ ወሳኝ ኃይል ሆነው ተመድበዋል ። በአገሪቱ የውጭ ስለላ ስድስት መቶ ፈረንሳዮች ተሠማርተዋል ። ይህ የመከላከያ ወጭዋን ቢቀንስላትም ደህንነቷን በባዕዶች የመጠበቁ ጉዳይ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ወድቋል ። በሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ቁልፍ ሚና የሚጫወቱት በዚያ የተቀጠሩት ፈረንሳዮች ናቸው ። በሚኒስትርነትና በምክትልነት ደረጃ አይሰሩ እንጅ ከዚያ በታች ወሳኝ ሥፍራዎችን ሁሉ ይዘዋል ። በሌሎች የአፍሪካ አገሮች ግን አውሮፓውያን ተወግደዋል ። በአይቮሪ ኮስት ግን ፈረንሳዮች የሆቴል አሳላፊ ፣ የመጋዘን ፀሐፊ ወዘተ በመሆን ሳይቀር ይሠራሉ ።

የፈረንሳዮች መኖርም የተማሩ የአገሪቱ ዜጎችን የሥራ ዕድል ዘግቷል ። የአገሪቱ ዓመታዊ ዕድገት እስታትስቲክስ የሚያስደስት ርምጃ ቢያሳይም አይቮሪኮስት በውጭ ሠራተኞች ፣ በውጭ ካፒታል ፣ በውጭ ቴክኒሽያኖች ፤ በውጭ ገበያ የመመካቷ ጉዳይ አንድ ቀን ፈረንሳዮች ቢወጡ አገሪቱ ሽባ ትሆናለች ያሰኛል ። ፖርቱጊዞች አንጎላን ለቀው ሲሄዱ የደረሰው ዓይነት መንኮታኮት ባይደርስባትም (የተማሩ ሰዎች ያፈራች ስለሆነ) ያለፈረንሳዮች ያ ፣ ሁሉ ታምር አይታሰብም ።



ሌሎች ችግሮችም አሉ ። ምዝበራ ተስፋፍቷል ። በደሀና ሀብታም መካከል የሰፋ ልዩነት አለ ። ይህ ሁሉ ሆኖ ግን ቡዋኝ ሌላው አማራጭ ቤታችንን ዘግተን እንደጎረቤቶቻችን እንደ ጋና ፣ ቡርኪናፋሶ ፣ ማሊ ፣ ላይቤርያና ጊኒ መደህየት ነው ባይ ናቸው ።

ከአይቮሪኮስት ወደ ጊኒ ስሄድ ትልቅ ልዩነት ተሰማኝ ። የዘመን መቁጠሪያ ካሌንደርን ሃምሳ ዓመት ወደ ኋላ የመመለስ ያህል ሆኖ ታየኝ ። ከአውሮፕላን ጣቢያው ወደ ከተማው የምትወስደዋ መንገድ ጠባብና አሮጌ ናት ። በመንገዱ አጠገብ ያለው ዲዶንቃ የተሰኘ አሮጌ ሆስፒታል ንጽሕናው ያልተጠበቀ ነው ። የቀድሞ የፈረንሳዮች የተከሉ ልማት ዳዋ ለብሷል ፤ በፈራረሱት ቤቶች ውስጥ ሳይቀር ዛፎች በቅለው ይታያሉ ። የሰፈሩ ነዋሪዎች አርጅተው የወዳደቁ የማንጎ ፍሬዎች ይለቃቅማሉ ። ሱቆች ባዶ ሆነዋል ፣ በሮቻቸው ተገንጥለው አንዳንዶቹ በአንድ ማጠፊያ ላይ ብቻ ተንጠልጥለዋል ። በጊኒ ሁሉ ነገር የመንግሥት ነው ። ትልቁ የገበያ አዳራሽ “ናፍያያ’ ይባላል ። የተትረፈረፈ ማለት ነው ። ነገር ግን ምንም የሚሸጥ ሸቀጥ የለበትም ። የቻይና የጢም ብሩሽ ፣ ጥቂት የፍሬ ጭማቂ ቆርቆሮዎችና ጥቂት ካርቶን መኮረኒ ተደርድረዋል ። የሥጋ መሸጫው መደዳ አቧራ ለብሶ ማቀዝቀዣው አይሰራም ። በአዳራሹ አንዱ ዳር የፊደል ካስትሮ ፎቶግራፍ በትልቁ ተሠርቶ ተሰቅሏል ። በሌላው የአዳራሹ ግድግዳ ላይ “መሰቃየት ድል ማድረግ ነው” የሚል መፈክር ተሰቅሏል ።

በጊኒ ያሉት የውጭ ዜጎች ቁጥር 350 ብቻ ነው ። በከተማው መንገድ ግራና ቀኝ ያሉ ዛፎች እየደረቁ ሲሆን ፣ ማንም ግድ ያለው አይመስልም ። ከተማው ፍዝዝ ያለ ሆኖ ምንም እንቅስቃሴ አታይበትም ። ለሥራ የሚጣደፍ ሰው አይታይም ።

ጊኒን ለመጎብኘትና ፕሬዚዳንት ሴኩቱሬን ለማነጋገር ፈቃድ አግኝቼ ኮናክሪ በገባሁ በሁለተኛው ቀን በአሜሪካ ኢምባሲ በኩል መልእክት ደረሰኝ ። መልእክቱም ቱሬን ለማነጋገር በአሥር ሰዐት ቤተመንግሥት እንድገኝ የሚያሳስብ ነበር ። በሰዐቱ ደርሼ ስጠባበቅ ቆየሁና አሥራ ሁለት ሰዓት ሲሆን ቱሬ ከመኖሪያቸው ወጡና ሲጀራ

በእጃቸው እንደያዙ ነጭ ባርኔጣ አድርገው በአንገታቸው ሰላምታ ሰጥተውኝ አልፈው ተራመዱ ። ግዙፍና ደህና ገጽታ ያላቸው ቱሬ በፍጥነት እየተራመዱና ዓይናቸው እየቃዠ ደረጃውን ወረዱና መኪናቸው አጠገብ ሲደርሱ ቆም አሉ ። ተከትለዋቸው ይራመዱ የነበሩት ሚኒስትሮቻቸውም ከኋላቸው ቆም አሉ ። የክብር ዘቡ ሰላምታ ሰጠ ፤ በጥሩምባ የታጀበ ሰላምታው እንዳበቃ ስምንት የፀጥታው ሠራተኞች የሆኑ ሞተረኞች ማስነሻዎቻቸውን በመርገጥ እነዚያን ቢ.ኤም ደብሊው ሞተር ቢስክሌቶች እንደብራቅ አንጣጡአቸው ።

እኔም በሁለት የክብር ዘቦች መካከል ከመኪናው ኋላ ተጣብቤ ከግቢው ወጣን ። በመንገድ የቆሙ ሰዎች የሚሰጡትን ሰላምታ ነጭ መሀረብ በማውለብለብ አፀፋ እየመለሱ ቀጠሉ ። ቱሬ ከ1958 ጀምሮ ሀገራቸውን የመሩት ተቃዋሚዎቻቸውን በመደምሰስና ሕዝቡን 2,500 በሚደርሱ የቀበሌ ምክር ቤቶች በማደራጀት ሲሆን ፤ ላመኑበት አብዮት ማንኛውንም መስዋዕትነት በማስከፈል ነው ።

እስካሁንም የተጨበጡት ግኝቶች በጣም ጥቂት ናቸው ። ቱሬ ራሳቸውን በሥልጣን ላይ ለማቆየት ከመቻል በስተቀር ይህን ገነቡ ለማለት ያስቸግራል ። በበኩላቸው ግን “የአፍሪካ መጥፎ ልጅ ብለው ሲጠሩኝ ምን ማለታቸው እንደሆነ አላውቅም ፤ ለኢምፔሪያሊዝምና ለቅኝ አገዛዝ ባለማጎብደዳችን ይሆን?” ብለው ይጠይቃሉ ። ”ይህ ከሆነ አይበገሬ በመባላችን እንኮራለን ። የእኛ ምኞት እስከሞት ድረስ የአፍሪካ እውነተኛ ልጅ ሆኖ መኖር ነው” ይላሉ ።

ከፕሬዚዳንቱ ጋር ቃለ ምልልስ ለማድረግ አሥራ አምስት ጥያቄዎች በጽሑፍ አቅርቤ ስለነበር ስምንቱ ተሰርዘውና ነቀፋ ተጽፎባቸው ሰባቱ ተፈቅደው ተመለሱልኝ ። ወዲያው ወደቡን ጉበኙና ተመልሰን በቤተመንግሥት የእንግዳ መቀበያ ክፍል ውስጥ እንደተቀመጡ አጠገባቸው ካለው ሰማያዊ ፎቴ ላይ ሆንሁና መቅረጸ ድምጽ አስተካከልሁ ። የካቢኔ ሚኒስትሮች በሙሉ ተሰብስበዋል ፤ የቴሌቪዥን ፊልም ቀራጺ ቡድን መጥቷል ። የሁሉም ዓይን እኔ ላይ ነው ። ቴፑን ተጫንሁና የመጀመሪያውን ጥያቄ ላቀርብ ስል አንድ ባለሥልጣን ከኋላዬ ጠጋ አለኝና “አሁን አይደለም ፤ ጊዜው አይደለም ፤ ወደ ሆቴል



ሂድ ፤ አለኝ ። አፍሬ እየተሸማቀቅሁ ከትልቁ አዳራሽ ወጣሁ ። “ቃለ መጠይቁን ለሌላ ቀን እናዘጋጅልሃለን ፤ አታስብ” አለኝ የሸኘኝ ባለ ሥልጣን ።

መልስ የሚሰጠኝ ሳጣ ከአምስት ቀናት ቆይታ በኋላ ምን እንደነካቸው ሳይገባኝ ወደ ናይሮቢ ተመለስሁ ። እዚያ ስደርስ ለሰባቱ ጥያቄዎች የሚሆን አሥራ ሰባት ገጽ ቴሌግራም ጠበቀኝ ።

ቱሬ ፕሬዚዳንት ዴጎልን አሻፈረኝ ብለው ነፃነትን ሲመርጡና ፈረንሳዮችን ሲያስወጡ የጊኒ ሕዝብ በደስታ ፈንድቆ ነበር? ነገር ግን ቱሬ ወዲያው ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግን ከለከሉ ። ጊኒን ከሁሉም የተገለለች አደረጓት ። ከፈረንሳይ ኮሚኒስት ፓርቲ ጋር በመጠባበቅ ቱሬ የሌኒን የሰላም ሽልማት አሸናፊ ተባሉ ። ምዕራቡ ዓለም በተራማጅነታቸው ሲያገላቸው ለመርዳት ፈቃደኛ ሆና የቀረበችው ሶቭዬት ብቻ ሆነች ። ምዕራቡ ዓለም ሁልጊዜም የግራ ዝንባሌ ያላቸውን ገሸሽ እያደረገ እንደ አውጉስቲኖ ኔቶ ፤ ሳሞራ ማሼል የመሳሰሉ ተሰሚነት ያላቸው የአፍሪካ ፕሬዚዳንቶችን በማግለል ምርጫ በማጣት ወደ ራሽያ ጉያ እንዲገቡ አድርጓቸዋል ። በተደጋጋሚ የተፈጸመ ስህተት ነው ።

ከሞስኮ ያገኙት ርዳታ መናኛ ሲሆን ሶቭዬት በበኩልዋ ግን ለአንጎላ ለምታመላልሰው መሣሪያ ጊኒን መረማመጃ አደረገቻት ። ከጊኒ የባህር ጠረፍ ሞስኮ ዓሣዎችን በነፃ በማጥመድ ፤ ስድሳ ከመቶውን በመውሰድና ቀሪውን ጊኒ ውስጥ በመሸጥ ሞስኮ ጥቅሟን ማባረር ጀመረች ። በሶቭዬት በኩል የተደረገው ጠቃሚ ድጋፍ የጊኒን ቦክሳይትና አሉሚኒየም ማዕድን ማውጣት ሲሆን ፤ ይህንንም ቢሆን ሶቭዬት ከሌላ አገር ሊገዛበት በማይችል የራሽያ ሩብል እየገዛች በርካሽ ዋጋ የምትወስደው ራሷ ነበረች ። ከጊኒ የሚወጣው ማዕድን በሙሉ ለሶቭዬት ዕዳ መክፈያ እንዲውል ስምምነት ስለነበራቸው በተለይ ከአንዱ ትልቅ የማዕድን ሥፍራ የሚመረተው ዘጠና በመቶ ወደ ሶቪዬት ይጫን ነበር ። በሌላ በኩል ከአንድ የምዕራብ ኩባንያዎች ቅንጅት የሚወጣ ማዕድን ለጊኒ በዓመት 100,000,000 ዶላር በማስገኘት ከአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ሰባ በመቶውን ይሸፍን ነበር ።

ከሃያ ዓመት ነፃነት በኋላ ቱሬ የምሥራቁ ካምፕ ርዳታ ብቃት
እንደሌለው ማማረር ጀመሩ ። ሶቭዬት በየዓመቱ ከጊኒ የብድር ክፍያ
25,000,000 ዶላር እየወሰደች "ከካፒታሊስቶች የበለጠች ካፒታሊ
ስት ሆነችብን "በማለት ያጉተመትሙ ። በዚህ ላይ የፈረንሳይ ቅኝ
እያሉ ሲነቅፉዋት የነበረችውን አይቮሪኮስት በደረሰችበት የዕድ
ገት ደረጃ ተደንቀው አፋቸውን ያዙ ። ከዚያም ቱሬ ለመዋዕለ ንዋይ
ርዳታ ፊታቸውን ወደ ምዕራብ አዞሩ ። የፈረንሳይን ፕሬዚዳንት ጂስካር
ዴስታንግ ወደ ጊኒ በመጋበዝ ጠፍቶ የኖረ ወንድም አቀባበል ዓይ
ነት አደረጉላቸው ። ቀጥለውም ወደ አሜሪካ ለጉብኝት ሄዱና በመ
ካከለኛው ምዕራብ ያለውን እጅግ የተራቀቀ ዘመናዊ እርሻ ልማት
በማየት ተደነቁ ። ከሞስኮ ጋር የነበራቸውን ግንኙነት እያላሉና የማር
ክሲስት ድንፋታቸውን እያቀዘቀዙ ወደ አፍሪካዊ ሶሻሊዝም ፣ ብሔ
ረተኝነትና እስልምና እየተመለሱ ሄዱ ። የጭቆና አገዛዛቸውንም ላላ
አደረጉ ።

ነገር ግን ከቀድሞው ባህርያቸው መለወጥ ቀላል አልነበረም ።
አንድ አቅጣጫ ብቻ የሚያዩ ፣ ጩካኝና ለአብዮቱ ግቦች ያለማወላ
ወል የቆሙ ፣ ሥልጣናቸው ጥያቄ ውስጥ የማይገባ ነበሩ ። ሚኒስት
ሮቻቸው አስተያየት ያቀርቡ እንደሆነ እንጅ ወሳኙ እሳቸው ብቻ
ናቸው ። መንግሥት ማለት ፣ ፓርቲ ማለት ፣ ምክር ቤት ማለት በእ
ሳቸው ውሳኔ የሚሄድ አንድ አካል ማለት ነው ። ፖለቲካዊ ውይይት
የሚካሄደው በሹክሹክታ ብቻ ነበር ። አመራራቸውን የሚፈታተን
ቂል የሆነ ነው ።

አመራሩን እንታገላለን ያሉ በሺህ የሚቆጠሩ የጊኒ ተወላጆች
ታስረዋል ፣ ወይም ተገድለዋል ። በትክክለኛ አቆጣጠር ከ1958 እስከ
1970 አሥራ ሰባት የቱሬ ሚኒስትሮች ተገድለዋል ። ወይም ተሰቅ
ለዋል ። ሌሎች አሥራ ስምንት ደግሞ ከባድ የጉልበት ሥራ እየ
ሰሩ የእድሜልክ እሥራት እንዲገፉ ተፈርዶባቸዋል ። ከብዙ ዓመታት
በፊት ደግሞ በስቅላት የተቀጡ አምስት ባለሥልጣኖች አስከሬኖች
ከተሰቀሉበት ሳይነሱ ለሁለት ቀናት እንዲንዠዋዠው በማድረግ
ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆን አድርገዋል ። ቱሬ ከገደሏቸው ምሁራን



ውስጥ የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ዲያል ኦቴሊ
ይገኙባቸዋል ። ከጠቅላላው የጊኒ ሕዝብ ቁጥር አርባ በመቶ የሚሆኑት
ሁለት ሚሊዮን ዜጎች በፍርሃት ከአገራቸው ወጥተው በስደት ይኖ
ራሉ ።

አምነስቲ ኢንተርናሽናል የተሰኘው ድርጅት የቱሬን መንግሥት
በሰብዓዊ መብት ረገጣ በከሰሰበት ወቅት ፕሬዚዳንቱ ለክሱ ቦታ
ባለመስጠት" ስለማታውቁት ሕዝብ አትቀባጥሩ" በማለት መልሰ
ዋል ። በእሳቸው በኩል ዘረኝነትንና የጾታ አድሉን በማስወገድ ከብዙ
ዎቹ አገሮች የተሻለ እኩልነት እንዳለ ገልጠዋል ።

ቱሬ እዚህ ላይ እውነት አላቸው ። በጊኒ ለእርሻ ምቹ ከሆነው
መሬትዋ 12% ብቻ ቢታረስምና ለምግብ የሚያሻትን እህል ከውጭ
ለመግዛት ብትገደድም ፤ የነፍስወከፍ ዓመታዊ ገቢ ከነፃነት በኋላ
በማዘቅዘቅ ወደ 210 ዶላር ቢወርድም ፣ የጊኒ የተፈጥሮ ሀብት ጥቅም
ላይ ባይውልና አገሪቱ 300 ማይልስ ብቻ አስፋልት መንገድ ቢኖ
ራትም ፤ በጊኒ ምዝበራ ፣ ሴትኛ አዳሪ ፣ ለማኝ ፣ የሚባሉ ነገሮች የሉም ።
በነጭ የተያዘ ቁልፍ የመንግሥት ሥልጣን ቦታ የለም ። በከተሞች
የሚስብ ነገር ስለሌለ የገጠሩ ሕዝብ ወደ ከተሞች አልጐረፈም ።
ሕዝቡ ምንም እንዳያውቅ ስለተደረገና ምንም ካላወቁ ደግሞ ይህ
ቀረብኝ የሚባል ስለማይኖር ለሕዝቡ ያልተሟላለት ምኞት የለም ።
ወደ ጎረቤት አገር አይቮሪ ኮስት ሄደው የሌላውን ሕይወት ለማየ
ትና ለማነፃፀር አይችሉም ። ሬዲዮና ጋዜጣ በመስማት ስለሌላውና
ስለራሳቸው ነፃ አስተያየት ማዳመጥ አይችሉም ። ሁሉም ድሀ ስለሆነ
በሀብታምና ድሃ መካከል የጉላ ልዩነት የለም ። የኮናክሪ ከበርቴ የሚ
ባሉትም ቢሆን በአፂራማ ቤት ከዶሮዎችና ፍየሎች ጋር የሚኖሩ
ናቸው ።

የጊኒ ሕዝብ ብዙ ቢያምረውም አይገልጠውም ። ይልቁንም ብሔ
ራዊ ስሜታቸው ጠንካራ የሆነና በሀገራቸው የሚኮሩ ናቸው ። ይህ
ዓይነቱ አመለካከት ደግሞ በአፍሪካ የተለመደ አይደለም ። ሕዝቡን
ከሚያጓጓ ሕይወት ፣ ከስግብግብነትና ከግል ፍላጐት ፣ አገርን ከሚቦ
ረቡር ስሜት አውጥተው ብሔራዊ ስሜትን ማጎልበታቸው የሚቀገስ

ቁምነገር ነው ። ግን በድህነትና በጭቆና መምራታቸው የሚያስነቅፋቸው ነው ።

ሕዝቡን በማደራጀት በዲሲፕሊን መምራታቸው እንደ መልካም ተግባር ይወሰድ ይሆናል ። ነገር ግን የጊኒ ሕዝብ ምርጫ ቢሰጠው ምን ይፈጠራል? የሚያምኑበትን ሀሳብ እንዲናገሩ ፣ የበቀል ርምጃ ሳይሰጉ የሚፈልጉትን እንዲገልጡ ፣ ያሻቸውን እንዲጠይቁና እንዲንቀሳቀሱ ነፃነት ቢሰጣቸው ምን ይሉ ይሆን?



## ምዕራፍ አሥራ አንድ

# የእንግዳ ባህል ተፅዕኖ

"በአፍሪካ ሰዓቱ ሁልጊዜም ለአሥራ ሁለት አምስት ደቃቂ ጉዳይ ነው ።"

አስተሳሰቡ ደካማ የሆነ ፈረንጅ አፍሪካዊን ኋላቀር ብሎ ሊያስብ ይችላል ። የቀድሞ ሠፋሪ ነጮችም እንዲያ ነበሩ ። እንዲያውም አውሮፓውያን ወደአፍሪካ ባይሄዱ ኖሮ እስካሁን ጨለማ አህጉር ሆና ይቀር ነበር የሚሉም አሉ ። ይህ እውነት አይደለም ። አፍሪካውያን የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ሥርዓት ነበራቸው። ያም ሥርዓት ለእነሱ በሚገባ ተስማምቷቸው ነበር ። እነዚያ በሂደት የቀረጿቸው ሥርዓቶች መንኮታኮት የጀመሩት ምዕራብ ነክ ዓለም ውስጥ ከተገፈተሩ ወዲህ ነው ። አንድ የውጭ ዜጋ በአፍሪካ የሚያጋጥመውን የእንግዳ ባህል ተጽዕኖ መመልከት ያለበት ከዚህ አስተሳሰብ አኳያ ነው ። ምክንያቱም የሁሉም ነገር መጥፎ ትዝታ የሚመነጨው አፍሪካውያን ከዘመናዊው ዓለም ባደረጉት ግጭት እንግዳነት ነው ።

በሠለጠነው ዓለም ያለው ዓይነት ሰዐት የማክበር ፣ ሥራን በጥራት የማከናወን ፣ ይህ ቢሆን ይሄ ነው ብሎ የማሰብ ነገር በአፍሪካ እምብዛም አይታሰብም ። ከእውቀት ይልቅ ትዕግሥት የሚበልጥበት ቦታ ነው ፤ ምክንያቱም ለመኖር የግድ አስፈላጊው እሱ ነውና ። አፍሪካ የአውሮፓን አስከፊ ቢሮክራሲያዊ ዘይቤ በሙሉ ወርሳ ከድንቁርናና ግዴለሽነት ጋር በማዳመር አቅጣጫ መለወጫ አካል እንደሌለው ጀልባ ሊራመድ የማይችል አዝጋሚ ሥርዓት ፈጥራለች ።

በምዕራብ አፍሪካ ያሉ አውሮፓውያን የየዕለት ሕይወት ሂደት አልሳካ ሲላቸው "ምዕራብ አፍሪካ ዳግም ረታች" ይላሉ ። አልሆን ካለ አትጨነቅ ፤ እንደ ሥርዓቱ ሁን ለማለት ነው ። ስልክ ባይሠራ ፤ በሆቴል ምግብ ባይኖር ፤ የአየር መቅዘፊያው ቢበላሽ ፤ ባለሥልጣን በሰጠህ ቀጠሮ ባይገኝ ፤ አውሮፕላን ቢዘገይ ፤ "ምዕራብ አፍሪካ ዳግም ረታች" ብለህ ዝም ይሻላል ።

እነዚህን በመሳሰሉ ጉድለቶች አውሮፓዊ ሲበሳጭ አፍሪካውያን ይገረማሉ ። እንዲያውም ፈረንጅን ትዕግሥት የለሽ አድርገው ይመለከቱታል ። አፍሪካዊ በዚያ ንዳድ ፀሐይ ሀገር ውስጥ በሰዓት ተመርቶ አይኖርም ፤ ነገሮች አዘገሙ ወይም ጨርሰው ቆሙ ደንታ የለውም ። የማይገባውን የመሪዎች ፍልስፍና ዲስኩር ለመስማት ለብዙ ሰዐት ተሰልፎ ስታዲየም ይገባል ። የውሃ ሒሳቡን ለመክፈል ሶስት ሰዐት በትዕግሥት ይሰለፋል ። ሀኪም ለማነጋገር ሙሉ ቀን ተሰልፎ ባይሳካለት ነገ ለመመለስ በትዕግሥት ይሄዳል ። ምን ያስቸኩላል? የሚል ጥያቄ ያቀርባል ። በዓለም ላይ እንደልብ የሆነ በሽበሽ ነገር ቢኖር ጊዜ ነው ።

ስለአፍሪካ ያለኝ የማይጠፋ ትዝታ ያለሥራ መዋል ነው ። ስንፍና ግን አይደለም ። በኬንያ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በየመናፈሻው ሳር ላይ ተጋድመው ይውላሉ ። በየአደባባዩ ተጎልተው ቀኑን ያሳልፋሉ ። በየመሥሪያ ቤቱ በሰልፍ ሆነው ተራ ሲጠብቁ ይውላሉ ። በድንገተኛ አደጋ ለሕክምና የመጡ በከባድ የቆሰሉ ሳይቀር ሀኪም ለማነጋገር ተስፋ በማድረግ ድንገተኛ ክፍል ለሰዓቶች ይጠብቃሉ ። አንዳንድ ጊዜ ወደ ናይሮቢ ቢሮዬ ብቅ ስል ከኡጋንዳዊት ፀሐፊዬ ጋር አሥር የሚሆኑ ሰዎች ሲያወሩ አደርሳለሁ ። አንዳንዶም ዝም ብለው እጃቸውን ጭናቸው ላይ አጣምረው ግድግዳ ላይ ሲያፈጡ ይታያሉ ። መሄጃ የላቸውም ፤ የሚሰሩትም የላቸውም ። የሥራ ዕድል ትንሽ ነው ። ለሚሰሩትም ቢሆን የሥራ ማበረታቻ ክፍያ አነስተኛ ነው ። ስለዚህ ያለሥራ መንገላወድ ምን ያድርጉ ብለን የምናልፈው አማራጭ ሆኗል ። በእነዚህ ሁኔታዎችም ሕይወት በሰዓት የሚኖርባት አይደለችም ። ግን አንድን አፍሪካዊ ሾፌር አድርገህ ብትቀጥረው



ለምሳሌ ይለወጣል ። ሲቸኩል አደጋ ያጋጥመው እንደሆን እንጅ ቦዝኖ ተግባሩን ቸል አይልም ። በአፍሪካ የመኪና አደጋ ከፍተኛ ነው ።

የአየር መንገዶችም ሁኔታ በአፍሪካ አስገራሚ ነው ። ብዙዎቹ በኪሣራ የሚካሄዱና ለሀገሪቱ ክብር ሲባል ብቻ ያሉ ናቸው ። አንዳንዶቹ ፕሬዚዳንቱንና ሚኒስትሮችን ወደ አውሮፓ ለመውሰድ ሲባል የተቋቋሙ ናቸው ። አንዳንዶቹ ወደ ጦር ግንባሮች የወታደር ስንቅና ትጥቅ ለማመላለስ ሲባል የሚሰሩ ናቸው ። ከተጠበቀው ሰዐት ዘግይቶ መምጣትም ሆነ ጨርሶ አለመምጣት አዲስ ነገር አይደለም ። አንድ ጊዜ የዛየር ፕሬዚዳንትና ባለቤታቸው አንድ አንድ አውሮፕላን ይዘው በየፊናቸው ለጉብኝት በመሄዳቸው ቲኬት የቆረጡ መንገደኞች ሲንጫጩ ሰነበቱ ። አምስትና አሥር ቀን መዘግየት ለብዙ አፍሪካዊ ስሜት አይሰጠውም ።

በአፍሪካ ነገሮች እንደሠለጠነው ዓለም ባይከናወኑ መበሳጨት አይገባም ፤ ትርፉ የሆድ ሕመም ነውና ። አንድ ጊዜ ሰባ አምስት አሜሪካዊ ቱሪስቶች ዳሬሰላም የሚገኘው ክሊማንጀሮ ሆቴል ክፍል ይዘው አደሩና ለሳምንት በዚያው እንደሚሰነብቱ አስታውቀው ለጉብኝት ወጡ ። መንግሥት ለጋበዛቸው ልዑካን የሆቴሉ ክፍሎች ይፈለጋሉ ስለተባለ አስተናጋጆቹ የቱሪስቶችን ሻንጣዎች ሰብስበው እንግዳ መቀበያው ክፍል ጥግ አስይዘው ከመሩት ። ቱሪስቶች ከጉብኝት ሲመለሱ ሌላ ማደሪያ ፈልጉ ተባሉ ። አንድ አሜሪካዊ ተናዶ ፊቱ በርበሬ መስሎ "አታደርጉትም" አለ ። አስተናጋጁ መለሰና የልዑካኑ ማቆያ ሆቴል ስለጠፋ ወስደንባችኋል ሲል በትህትና አስረዳው ። ቱሪስቶቹ ተበሳጭተው ወደ ሲሸልስ በአውሮፕላን ሄዱ ። ማን ግድ አለው ።

በአሚን ዘመነ መንግሥት ኡጋንዳ ውስጥ ብጥብጥ ሲአይል ስደተኞችን ለማነጋገርና ዜና ለመሥራት በማሰብ ከጋዜጠኛ ባልደረባዬ ጋር ሆነን መኪና ተከራይተን ወደ ድንበሩ ተጓዝን ። ድንበሩ አጠገብ እንደደረስን ብዙ ስደተኞች ሽማግሌዎች ጭምር ተመለከትን ። ሁኔታውን ከየአቅጣጫው ለመዘገብ ፈልገን ወደ ድንበሩ ዘበኞች በመጠጋት የኡጋንዳን የኬላ ዘቦች ለመጠየቅ ሄድን ። እንደደረ

ሰን የድንበር ዘቡ በጠመንጃው እየነዳ ወደአቅራቢያው ፖሊስ ጣቢያ
አቀረብን ። የጣቢያው አዛዥ "የሲ.አይ.ኤ. ቅጥረኞች" በማለት ወረ
ዱብን ። ለሕይወታችን በጣም ፈራን ። ጋዜጠኛ መሆናችንን ብንገል
ጥም "ምን ልዩነት አለው" የሚል መልስ ተሰጠን ። በመጨረሻ
ስለኡጋንዳ የምታውቁትንና የሰማችሁትን ፃፉ ተባልንና ወረቀት
ተሰጠን ። ማን እንደነገራችሁም ግለጡ ተባልን ። አንድ ገጽ ፅፌ
ብሰጠው ጨምር አለኝ ። ግማሽ ገጽ ጨምሬ ደግ ደጉን ፃፍሁ ። ከዚ
ያም ስልክ ደውሎ እየተጨዋጨዋሽ ከአዛዡ ሲነጋገር አለቀልን
ብለን ፈራን ። በመጨረሻ ፈገግታ እያሳየ መጣና ጨብጦን "ጥሩ
ነው ፤ ሌላም ጊዜ መምጣት ትችላላችሁ ፤ አሁን ሂዱ" አለን ። ከዚያ
ከንፈን ወጣንና ግደላቸውም ቢለው ይገድለን እንደነበር በመገንዘብ
በድንጋጤ ወደናይሮቢ ተመለስን ።

በብዙ መልኩ አፍሪካ በቆየሁ ቁጥር ጭራሽ የአፍሪካዊን ባህ
ርይ መገንዘብ ይሳነኝ ጀመር ። ከዚህ በፊት በእስያ ለአራት ዓመታት ፤
ፀአውስትራሊያ ለሁለት ዓመታት ስለኖርሁ ከሞላ ጎደል በዚህ
ያለውን ሕዝብ ስሜት ፤ የሚያስደስተውንና የሚያስቆጣውን ለማወቅ
ችያለሁ ። በአፍሪካ ግን ሊታወቅ የማይችል የሰዎች ባህርይ አጋጠመኝ።
በማስመሰል መልክ ካልሆነ ብዙው እውነተኛ የውስጥ ስሜቱን አይ
ገልጥም ። ራሱ የሚያምንበትን ከመግለጥ ይልቅ ብዙ ጊዜ ልትሰማ
የምትወደው የሚመስለውን ቢነግርህ ይመርጣል ። የራሱን አስተያየት
ሰንዝሮ ቅር ከሚያሰኝህ ይልቅ የምትወደውን ሊነግርህ ይወዳል ።
ብዙ ጊዜ ሥልጣን አይጋፋም ፤ አለቃ ወይም መሪ ሆኖ ለሚመጣበት
ሁሉ በሚያስገርም ፈቃደኝነት ይታዘዛል ። እህሉ ቢወድምበት ፤ ልጆቹ
ቢሞቱበት ፤ መሪዎቹ በአሰቃቂ ሁኔታ ቢበድሉት አፍሪካዊው ያለ
አንዳች ተቃውሞና ያለአቤቱታ ኑሮውን ይቀጥላል ። ለማመን በሚያ
ስቸግር ሁኔታ ወደቀድሞው የኑሮ ሁኔታው ይመለሳል ።

ይህ ሕዝብ ለምዕት ዓመታት አያሌ የፍትሕ መጓደል ቢያጋጥ
መውም በመሠረቱ እስከአሁን ትሁት ነው ፤ ጨዋ ነው ፤ ትክክለኛ
አመለካከት ያለው ነው ። ታዲያ አንዳንድ ጊዜ ሌባ ሲያዝ የሚያሳ
ዩት የጭካኔ ድብደባ ይገርማል ። አንዳንዶቹ እስኪሞቱ ይደበደባሉ።



የአፍሪካን ባህርይ ለመረዳት ግን የአካባቢውን ሁለተንናዊ ሕይወት
ማጤን ያስፈልጋል ። የፀሐዩ ሙቀት ፤ የበሽታዎቹ ብዛት ፤ የሥራ ማጣት፤
የንግግር ነፃነት ማጣት ሁሉ ኃይላቸውን በመምጠጥ ሁሉንም አፍ
ሪካዊ ክርስቲያናችን ጨምሮ ጨካኝ አድርጓቸዋል ። ለራሱ በሕይወት
መኖር ብቻ በማሰላሰል ከእሱ የባሰ ላልታደሉት ምንም አይጨነ
ቅም ። አንዳንዶቹ እንደነገሩኝ አፍሪካውያን ለሌባ የማይራሩት ከቆየ
ባህላቸው አኳያ ሲሆን ፤ ሌብነት የኅብረተሰብን ደህንነት እንደማናጋት
የሚቆጠር ስለሆነ ወዲያው ቅጣቱን ይሰጣል ። ይህ የማይመስል አን
ጋር ቢሆንም በበኩሌ ይህ ባህርይ ከከተሜው አፍሪካዊ በሕይወት
መደበርና መሰላቸት የመጣ ይመስለኛል ።

አፍሪካውያንና አውሮፓውያን በባህርይ ተግባብተውና ተጣጥመው
ይኖራሉ ማለት ያስቸግራል ። አንጐላና ሞዛምቢክን ሳይጨምር በጥ
ቁር አፍሪካ በቅኝ ግዛት ዘመን ከነበረው የነጭ ሕዝብ ቁጥር የዛ
ሬው ይበልጣል ። በጠቅላላ ግማሽ ሚሊዮን ሲሆኑ ፤ ከዚህ ውስጥ
20,000 የሚሆኑት አሜሪካውያን ናቸው ። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው
ፈረንጆች የሚኖሩት በዚምባብዌ (135,000) ፤ በኬንያ (75,000) ፤
እንዲሁም በአይቮሪ ኮስት (50,000) ናቸው ። ብዙዎቹ በቅርብ ዘመን
የመጡ ስለሆነ ተግባቢ አይደሉም ። ለአንዳንድ ኩባንያዎች የሚሰሩ
ልዩ ልዩ ሙያ ያላቸው ፤ የቴክኒክ ሰዎች ፤ ወይም የእጅ ጥበብ ያላቸው
ናቸው ። ከዚህም ውስጥ አውሮፕላን አብራሪዎች ፤ የሆቴል ሥራ አስኪ
ያጆች ፤ የእርሻ ጠበብቶች ፤ ነዳጅ ቆፋሪዎች ፤ የሚኒስትሮች አማካሪ
ዎች ፤ የሥነሕንፃ መሐንዲሶች ፤ ሐኪሞች ፤ የፋይናንስ ኤክስፐርቶች
ሲሆኑ ፤ ሶስትና አራት ዓመት ሠርተው ወደ ተከታዩ ሥምሪት የሚሄዱ
ናቸው ።

እስካሁን በዚያ መቆየታቸው የሚያስታውሰን ቅኝ ገዢዎች
አፍሪካን ለነፃነት በሚገባ አለማዘጋጀታቸውን ነው ። በአመዛኙ
አፍሪካ እንግዳ ተቀባይ ሆና ቀርታለች ። የነጮች መኖር ጉዳይም
በየጊዜው የሚነሳ ጉዳይ ነው ። በአፍሪካ በሚኖሩ ነጮች ላይ የሚነ
ሳው ተቃውሞ በአራት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ የሚመረኮዝ ነው ።
ያአገሬው ሕዝብ መያዝ ያለበትን ሥራ ፈረንጁ መያዙ አንዱ ነው ።

አፍሪካውያን ራሳቸውን ማስተዳደር አይችሉም የሚለውን ለማጉላት የኤኮኖሚ ሻጥር እየሠሩ የሥራ ዕድላቸውን እንዳይነጠቁ ተንኮል ይሸርባሉ ። ምቾታቸው በልዩ ሁኔታ ተጠብቆላቸው ይኖራሉ ። በራሳቸው አገር ዝቅተኛ(ሁለተኛ) ደረጃ የሚሰጣቸው ሙያተኞች ሆነው ሳለ በአፍሪካ ራሳቸውን እንደ ኤክስፐርት በማቅረብ ብዙ ይከፈላቸዋል ። በብዙ አገሮች የአፍሪካ ምሁራን ይህን ሁኔታ በተደጋጋሚ ተቃውመዋል ።

ዛሬ ኬንያን በመሰሉት አገሮች ነጮች እንደ ቅኝ ግዛት ዘመን በምቾት ይኖራሉ ። ትልቅ ቤትና ግቢ ፣ ሰፊ የአትክልት ቦታ ኖሮዋቸው በመንደላቀቅ ሕይወታቸውን ይቀጫሉ ። በቀበሌው የስፖርት ክበብ በአባልነት በመመዝገብ በሰዓት አንድ ዶላር ከሃያ አምስት ሳንቲም በሚከፈልበት ርካሽ የሜዳ ቴኒስ ሥፍራ ላይ ይጫወታሉ ። ለኳስ አቀባይ ልጆች በጨዋታ አሥር ሳንቲም ብቻ እየከፈሉ በቁጠባ ይኖራሉ ። ከዚህ ውጭ ማህበራዊ ግንኙነታቸው ግን ከነጮች ጋር ብቻ ነው ። ከአፍሪካውያን ጋር ጓደኝነት አይሹም ። ከፓሪስ ታትሞ የሚመጣለትን ሄራልድ ትሪቢዩን እያነበበና ከዓለም ክስተቶች ጋር ለመተዋወቅ ቢ.ቢ.ሲ. እያዳመጠ የኑሮ ውድነት በየዓመቱ ኑሮውን ሳያናጋበት ፈረንጁ በተረጋጋ ሁኔታ ይኖራል ።

በናይሮቢ ዶናቫን ማውለ የሚባል የእንግሊዝ ባለሙያዎች ትያትር አለ ። ቦቢ ቢስትሮ የተሰኘ ከአስተናጋጆች በስተቀር ጥቁር የማይታይበት ምግብ ቤትም አለ ። ንጉንግ በሚባል ቦታ ደግሞ በእንግሊዝ አገር ካሉት ያላነሰ የሚያምር መጋለቢያ ባለው የፈረሰኞች ክበብ ነጭ ጓንትና ሰፊ ባርኔጣ ያደረጉ አውሮፓውያን ሴቶች ሲወዳደሩ ይውላሉ ። የእንግሊዝ ጋዜጦች የሞሉበት ቤተ መፃሕፍትና የእንግሊዝ ባህላዊ ምግቦች የሚዘጋጁበት ልዩ ምግብ ቤትም አላቸው ። በዚህም የሸመገሉ ነጮች ሳይቀር እየተሰበሰቡ በእንግዳ ክፍል ቡና እየተጐነጩ ያለፈውን ዘመን ያወጋሉ ።

እንግሊዞች ዛሬም በሚስተናገዱባቸው ሆቴሎች ሲንቀባረሩ አይጣል ነው ። መጠጥም ፣ ምግብም ሲያዝዙ በመንቦጥረር ነው ። አስተናጋጁ ኬንያዊም ነጭ ጃኬት ዩኒፎርሙን ለብሶ በሙሉ ታዛዥነት



ልክ ከአርባ ዓመት (ከነፃነት) በፊት እንደሚያደርገው ሮጦ በመጠጋት ትዕዛዛቸውን ያሟላል ።

ኬንያ በሶስተኛው ዓለም ለነጮች ምቾት ያላት ቦታ ሆና እስካሁን ብትቀጥልም ብዙዎቹ የአፍሪካ አገሮች ግን ለመጤ ነጮች የሚያባቡና ምቾት የጐደላቸው ናቸው ። ኑሮ ውድ የሆነባቸውም አሉ ፤ እንግልት የሚጐላባቸው ይበዛሉ ። በየሱፐር ማርኬቱ የሸቀጥ መደብር መደርደሪያዎች አግጠው መሠረታዊ ሸቀጥ አልባ ሆነዋል ፤ ነጭ ጋዝ በራሽን መልክ ስንት ተጠብቆ የሚገኝ ነው ፤ ራስን ለማኖር ሲባል የግድ መገዛት ስላለበት ትንሿ ሥራ ብዙ የምታደክም ትሆናለች ።

በናይጀሪያ ዋና ከተማ በሌጐስ ፣ ሶስት መኝታ ቤት ያለው ቪላ በዓመት 50,000 ዶላር ይከራያል ። ለዚያውም የሶስት ዓመት ኪራይ በቅድሚያ ይጠየቅበታል ። በታንዛንያ ደግሞ አይብም ሆነ ቅቤ እንደ ብርቅ አልፎ አልፎ የሚገኝ ነው ። በዛምቢያ ዝናብ ሲዘንብ የስልክ መስመሮች አይሰሩም ። የቴሌኮሙኒኬሽን ኩባንያ ተደውሎ ቢጠየቅ የሚሰጡት መልስ "ዝናቡ እስኪያባራ ጠብቁ" የሚል ነው ።

በዛየር የሚኖር ቦብ ሄይሲ የተሰኘ አሜሪካዊ አግኝቼ እንዳጫወተኝ ባለሶስት መኝታ ክፍል መኖሪያ ቤቱ ኪራይ በወር ወደ 1,100 ዶላር አድጓል ። ለዚያውም ስልክ የለውም ፤ አንዳንድ ጊዜ ውሃም ይቋረጣል ፤ ሶስት ጓደኞቹ በዚያ ሰሞን በባህሩ ዳርቻ ፎቶግራፍ ሲያነሱ በዛየር ፖሊሶች ተይዘው ታስረዋል ። ከዚያ አጋጣሚ አንድ ሳምንት ቀደም ብሎ ካሜራውን ሌባ ሰርቆበታል ። የወጥ ቤት ሠራተኛው ከሄደ ሳምንት አልፎታል ፤ አትክልተኛውም ተጨማሪ ብድር ካልተሰጠኝ ብሎ ያጉተመትማል ። የአየሩ ሙቀት መቶ ዲግሪ ደርሷል ፤ የአየር መቅዘፊያው ስለማይሰራ ሙቀቱን አልቻለውም ። ነፋስ መሳቢያውን ለማሰራት ሞክሮ በዛየር መለዋወጫ አጣ ። መኪናውም ተመሳሳይ ችግር አጋጥሚታል ።

ከዚህ ሁሉ መጥፎ አጋጣሚ ለመሸሽና ለመዝናናት ብሎ ካቴን ለራት ይዟት ወደ ሆቴል ሄደ ። የራት ዋጋ ያውም የወይን ጠጁን ሳይጨምር 150 ዶላር ተጠየቀ ። ወደ ቤቱ ሲመለስ ፖሊሶች አስቁ

መው ገንዘብ ወሰዱበት ። "ይህ ኑሮ አይደለም" በማለት "አንቺ ምን እንደምትይው አላውቅም ፤ በሕይወት ለመቆየት ሲባል ትይው እንደሆነ እንጅ ኑሮስ አልደለም" አላት ለካቴ ።

ወደ ዩናይትድ እስቴትስ ለእረፍት ከባለቤቴ ጋር በተመለስሁ ቁጥር ጓደኞቼ "አፍሪካ በእርግጥ ምን ይመስላል?" እያሉ ይጠይቁኛል ። የተሻለው መልስ "ልዩ ነው" የሚል ነው ። ድህነት ሥር ሰዷል ። ግን በአገሬው ደረጃ የአፍሪካ ገበሬ በልቶ ያድራል ። ለመኖር የሚያስፈልጉት ምግብ ፥ ልብስ ፥ መለስተኛ መጠለያና የቤተሰብ ፍቅር አለው ፤ የጤና ሁኔታ አሰቃቂ ቢሆንም ብዙዎቹ አፍሪካውያን ከጥንቱ የተሻለ የሕክምና አገልግሎት እያገኙ ነው ። የስልክ ብልሽትና ስለሰዐት ማክበር አለመጨነቃቸው አሜሪካዊ ጐብኝዎችን ያስገርም ይሆናል ፤ የአፍሪካውያንን ሕይወት ግን አያናጉትም ። የሶስተኛው ዓለም የባህል ተጽዕኖ ምዕራባውያንን ግራ ያጋባ ይሆናል ። አፍሪካዊውን ግን ምንም አይለውም ። ሥርዓቱን የቀየሰው ራሱ ስለሆነ እንዴት እንደሚሠራና በዚያ ክልል ውስጥ እንዴት እንደሚኖር ያውቀዋል ።

በአንድ ወቅት በዛየር ኢንተር ኮንቲኔንታል ሆቴል ዕሰነብት ዜና በስልክ ወደ ሎስ አንጀለስ አስተላልፋለሁ ብዬ ሁለት ሌሊት ሙሉ አፕሬተሩ አላገናኝ ብሎኝ ብዙ ደከምሁ ። መስመር ማግኘት አስቸጋሪ ነው እያለኝ አስቸገረኝ ። በሌላው ቀን አንዱ ጓደኛው "በፀባይ" አትገባውም እንዴ አለኝ ። ምንድነው ብዬ ጠየቅሁት ። በል እንግዲያው ለአፕሬተሩ "በፀባይ" ብታገናኘኝ በለው አለኝ ። በማግስቱ እንደተነገረኝ ስለው በቅጽበት አገናኘኝ ። እንደጨረስሁ አፕሬተሩ ክፍሌ ድረስ መጣና መቶ ዶላር ሰጠሁት ። የጥሪው ሂሳብ የክፍሌ ኪራይ ውስጥ አልተጨመረም ፤ የቴሌ ኮሙኒኬሽን መዝገብም ላይ አይታይም ። መንግሥትን አታለው ፥ ሆቴሉንም አታለው ፥ እኔን ግን አሜሪካ አገናኘተውኛል ። "በፀባይ" እውነትም በፀባይ አሸናፊ ሆነዋል ።



<u>ምዕራፍ አሥራ ሁለት</u>

# የዜና ሳንሱር

"እውነት ማለት መንግሥት የሚያራምደው ሁሉ ነው ። አንድ ነገር ለሀገር ተስማሚ ካልሆነ እንግዲያው እውነት አይደለምና ውሸት ማተም የለብህም ።"

—የሶማሊያ ባለሥልጣን ስለአፍሪካ ዜና
ማሰራጫ የሰጠው አስተያየት

በየሳምንቱ ማክሰኞ ጥዋት ለብዙ ወራት ናይሮቢ ወደሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ እየሄድሁ መግቢያ ቪዛ ለማግኘት ስማፀን ቆየሁ። አንድ ቆንሲል በፈገግታ ይቀበለኝና ቢሮው ውስጥ ሻይ እየጠጣን ስለአፍሪካ ፖለቲካ እናወራለን ። በመጨረሻም ስለቪዛዬ ጉዳይ ስጠይቀው ፤ አ! ችግር የለም ፥ መንግሥት እያሰበበት ነው ይለኛል ። ትንሽ ጊዜ በትእግሥት እንድጠብቅ ያግባባኛል ።

በእነዚያ ዘመናት ኢትዮጵያ ጠቃሚ የዜና ምንጭ ነበረች ። ኃይለሥላሴን የገለበጠው የመኮንኖች ቡድን ከሞስኮና ከዋሽንግተን ጋር ኩኩሉ ይጫወት ስለነበር ስለአብዮቱ ዜና ከምንጩ ለማግኘት ብዙ የምዕራብ ጋዜጠኞች ለቪዛ ይሯሯጡ ነበር ። በመጨረሻ አንድ ምሽት በአሥራ ሁለት ሰዐት ቆንሲሉ ደወለልኝና ነገ ቪዛየን መውሰድ እንደምችል ገለጠልኝ ። ምድረ ጋዜጠኛ ሊያገኝ ያልቻለውን እድል በማግኘት ያለተሻሚ ዜናውን ሁሉ ለብቻዬ ለዓለም ላቃምስ ነው ብዬ ተደሰትሁ ። እንዲያ ግን አልተሳካልኝም ። ሰማንያ ሰባት የምዕራብ ጋዜጠኞች ቪዛ ተሰጥቷቸው ኖሮ ከሁለት ቀን በኋላ ከለንደን ፥ ከፓሪስ ፥ ከናይሮቢ ፥ ከኒውዮርክ ፀመጉረፍ አነስተኛ ብርጌድ

የሚሆን የሪፖርተሮች ቡድን ካሜራና ታይፕ ማድረጊያ በማንገብ
አዲስ አበባ ፈሰሰ ። ያልተለመዱ ከፍተኛ የጋዜጠኞች ቁጥር ስለነበረ
ለኢትዮጵያ የሕዝብ ግንኙነት ማዕበል ነበር ። ከዚያም ከአብዮቱ ተቃ
ዋሚዎች ባላነሰ ሁኔታ እየተከታተሉን በፕሮግራም መመራት አለ
ባችሁ ተብለን እስረኛ ሆንን ።

ፕሮግራም በሚል ሽፋን ብዙ የአፍሪካ አገሮች የውጭ ጋዜጠ
ኞችን በመቆጣጠር የሚፈለገውን ዜና ብቻ እንዲሰሩና መንግሥት
እንዲያዩለት የሚፈልገውን ሥፍራ ብቻ እንዲመለከቱ የሚያስገድድ
ዝግጅት ነው ። ግትር የሆነና የተጣበበ የፈለግነውን የማናይበትና
ያሻንን የማናነጋግርበት ፕሮግራም ነበር ። ከዚህ ውጭ እሰራለሁ
ያለ ጋዜጠኛ ወይም ሾፌሩን እንኳን አነጋገራለሁ ቢል“ አትችልም
በፕሮግራሙ ውስጥ አልተጠቀሰም” ይባላል ።

በአዲስ አበባ ቦሌ አውሮፕላን ማቢያ በፍጥነት በተዘጋጀልን
መኪና ተወስደን ግዮን ሆቴል ታጎርን ። አንድ የጦር ሠራዊት ሻለቃ
ሽጉጡን እንደሻጠ መመሪያ ሰጠን ። ከመመሪያው ውስጥ ከሆቴሉ
ግቢ መውጣት የተከለከለ መሆኑን ፣ ታክሲ መከራየት የማይፈቀድ
መሆኑን ፣ ሰው ሳይመደብልን ለብቻችን የትም መሄድ ክልክል መሆ
ኑን ፣ በፕሮግራሙ ውስጥ ከተጠቀሱ ክስተቶች አንዱንም ቢሆን
ሳያዩ መቅረት የተከለከለ መሆኑን ፣ ከዚህ ሆቴል ውጭና ከተጠቀ
ሰው ሰዐት በቀር ሌላ ቦታና በሌላ ሰዓት ምሳ መብላት የማይፈቀድ
መሆኑን አስጠነቀቀን ።

ነገር ግን የምዕራብ ጋዜጠኞችን በፕሮግራም አሥረው ማቆም
አልተቻላቸውም ። ሁላችንም በየፊናውና ከምሳ ላይ ለመታጠብ የወ
ጣን እየመሰልን ከተማውን አሰስነው ። የቀይ ሽብር ሰሞን ስለነበረ
በየማታው ተኩስ ሲያጓራ ያድራል ። በነጋታው ጠዋት በየመንገዱ
ዳር አምስትና ስድስት የ“ፀረ—አብዮት” ሬሳ ወድቆ ይታያል ። አስጎ
ብኝዎቻችን ፎቶ እንዳናነሳ ያስጠነቅቁናል ፤ ግን ሾለክ ብለን ቀጭ
ቀጭ አድርገን እንመለሳለን ።

“ምን ዓይነት አስቸጋሪ ሰዎች እንደሆናችሁ አይገባኝም ። የእኛ
ጋዜጠኞች እንደነገርናቸው ነው የሚፈጽሙት ። እናንተ ለምን እን



ዲያ አታደርጉም” ሲል አንድ የማስታወቂያ ሚኒስቴር የሕዝብ ግን
ኙነት አስጎብኚ ገሰፀን ።

አንድ ቀን ከኦጋዴን ጦር ግንባር ስንመለስ የአገር ውስጥ ሪፖ
ርተሮች ከበው ስለ ሁኔታው ጠየቁን ። በዚያን ጊዜ የኢትዮጵያና
የኩባ ጦር የሶማሊያን ወራሪ ጦር እያጠቃ ስለነበር ትኩስ ዜና አለ።
ነገር ግን የኢትዮጵያን ጋዜጦች የሚያነብ ሁሉ ከዚያ ይልቅ እኛ
በምናስተላልፈው እምነት አለው ። በአፍሪካ የብዙኃን መገናኛ ሚና
መንግሥትን ማገልገል እንጅ ሕዝብን ስለሁኔታዎች እውነቱን ማሳ
ወቅ አይደለም ። ፕሬስ ሕዝቡን ለማደራጀትና ለመቆጣጠር የሚጠ
ቀሙበት የፕሮፓጋንዳ መሣሪያ ነው ። ጥያቄ የሚያቀርብ ሁሉ እንደ
አስጊ ስለሚታይ መንግሥት ሕዝቡ ሊያውቅ የሚገባውን ብቻ ያቀ
ርብለታል ። ለምሳሌ የሶማሊያ ሪፑብሊክ ስለብዙኃን መገናኛ ሚና
ባስፈረው መመሪያ ፣ “የሚዲያ ተግባር ሕዝቡን ወደ አንድ ወጥ
ኅብረተሰብ ፣ ወደ አንድ አመለካከት ፣ የሀገሪቱን ጥቅም በመጠበቅ
ረገድም ወደ ተመሳሳይ ቁርጠኝነት መምራትና መቅረጽ ነው”ይላል ።

ከጥቂቶች በስተቀር የጥቁር አፍሪካ ጋዜጦች የመንግሥት ናቸው ።
የሚፃፉትና የሚታረሙት በመንግሥት ተቀጣሪ ሠራተኞች እንጅ ራሳ
ቸውን በቻሉ ሪፖርተሮች አይደለም ። ይዘታቸውም አጉል ወገናዊነት
የተጠናወተው ነው ።የአሜሪካ ፓርቲዎችም በምርጫ ውድድር ሰሞን
እንዲሁ ናቸው ። ጥሩ ጥሩውን ሁሉ ይገልጣሉ ፣ ከመጥፎው አንድም
አይጠቅሱም ። በባለሥልጣኖች ሥነከሣር ንግግር ላይ በማተኮር
የፕሬዚዳንቱን በርካታ ፎቶዎች በአንድ እትም ላይ በማጨቅ ያቀር
ባሉ ። ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሄራልድ ጋዜጣ የሶማሊያን የመጀመሪያ
ማጥቃት በተመለከተ ምንም አላቀረበም ፣ የመረጠው ስለጦርነቱ አለ
ማውራትን ነበር ። ኢትዮጵያ ማጥቃት ስትጀምር ግን ጋዜጣው ስለ
ግጭቱ ማቅረብ ጀመረ ። ያን ጊዜም ቢሆን ስለኩባና ራሽያ ሚና
አልተነፈሰም ። በአሜሪካና በአውሮፓ ግን የሁለቱ ሚና ነበር በመጀ
መሪያ ገጾች የሚታተመው ።

የመንግሥት ጋዜጣ በሶስተኛው ዓለም እንዲሁ ቢሆንም በአፍ
ሪካ ግን በነፃነት ሰሞን የወረሱትን ድንቅ ደረጃ የነበረው ፕሬስ

በሚያስገርም ሁኔታ በማውደም የወደፊቷ አፍሪካ መገናኛ ብዙኃን ሚና ምን ሊሆን እንደሚችል ማንም ሊጠይቅ አይፈልግም ። ይልቁንም ለመሆኑ ወደፊት እድል አለ ወይ? ብለው መጠየቅን ይመርጣሉ ። ከናይጄሪያ በስተቀር ማለትም በ1959 “ኢዊ ኢሮህኒን” የሰተኘ ጋዜጣ ታትሞ የነበረ ከመሆኑ በስተቀር ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ አገዛዝ መመሥረት ጋር ነው ጋዜጣ የጀመሩት ። ከነፃነት በኋላ መንግሥታት ያልተማረውን ሰፊ ሕዝብ ማታለያ መሣሪያ ያደረጉት የብዙኃን መገናኛን ስለነበር ጨምድደው በመያዝ የፕሬስ ነፃነትን ድራሹን አጠፉት ። ዜናው ሁሉ ሳንሱር ስለሚደረግ የሚታተመው የመንግሥት መግለጫ ብቻ ነው ለማለት ይቻላል ። በናይጀሪያ የመጀመሪያው መንግሥት ለአንድ ዓመት የአገሪቱን አኩሪ የጋዜጠኝነት ታሪክ በመርሳት ሂሳዊ አስተያየት ላለመቀበል ወሰነ ። በዚህም ወቅት በ1961 ቾኬ አቢ የተሰኘ ጋዜጠኛ ነቀፌታ ያዘለ ፅሁፍ በማተሙ የናይጀሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅጣት በይኖበታል ። በቀረበው ትችት የሚከተለው ይገኝበታል ።

“የሕዝቡ ጠላቶች የሆኑ ፣ ደካማውን የሚበዘብዙ ፣ ድሃውን የሚጨቁኑ ይውደሙ!. . . በደሀው ላብና ኪሣራ ራሳቸውን ያበለጸጉ መውደቂያቸው ተቃርቧል ። ተራው የናይጀርያ ሕዝብ ከአሁን ወዲያ ለመመረጥ ሲሉ የሚጥም ንግግር እያሰሙ ሥልጣን ከተከፋፈሉ በኋላ ግን እንደቆሻሻ በመቁጠር የሚበዘብዙትን በየዋህነት ዝም ብሎ አይመለከታቸውም ።”

በመላው አህጉሪቱ ታሪኩ ተመሳሳይ ነው ። የማላዊ ፕሬዚዳንት ባንዳ በ1970ዎቹ የግል ጋዜጦች ሠራተኞችን በሙሉ አሰሩ ። በዛምቢያ የጋዜጣ ዋና አዘጋጆችን የሚሾሙትና የሚሽሩት ራሳቸው ፕሬዚዳንት ካውንዳ ናቸው ። በዛየርና በኡጋንዳ ጋዜጠኞች በየጊዜው እየታሰሩ ስለሚፈቱ አንድ ሰሞን ተሰውረው ሰንብተው ሲመጡ ሚስቶቻቸው እንኳን ስለሚያውቁ ምንም አይጠይቁም ። የኢኳቶሪያል ጊኒ ፕሬዚዳንት ቢዩን በ1979 ሲገለበጡና ሲገደሉ ያላሰሩትና ያላስገደሉት እውቅ ጋዜጠኛ እንዳልነበረ ተጋለጠ ።

ደቡብ አፍሪካ ከብዙዎቹ በፕሬስ ነፃነት ሻል ትላለች ማለት



ይቻላል ። የአገሪቱ አርባ ሶስት ዕለታዊና ሳምንታዊ ጋዜጦች ምርመራዊ (ኢንቬስቲጌቲቭ) ሪፖርት በማቅረብ የተደበቁ ሻጥሮችን የሚያጋልጡበት ሁኔታ አለ ። እንዲያም ሆኖ ግን ጋዜጠኞች የት ድረስ ማጋለጥ እንደሚችሉ ገደባቸውን ያውቃሉ ። ደቡብ አፍሪካ የኢንፎርሜሽን ሥርጭትን የሚገድቡ ሃምሳ ሕጎች ሲኖሯት ፣ የሕዝቡን የማወቅ መብት የሚገድቡ ሌሎች ሃምሳ ደንቦች አውጥታለች ። ለምሳሌ አንድ ሪፖርተር ጥቁር አፍሪካዊ ታጋይ ብሔረተኛ ቢታሰርና ዜናውን ማውራት ቢፈልግ የሰውየውን የትውልድ ቀንና አድራሻ እንዲጠቅስ የሚያዝዝ ደንብ አለ ። ይህም ብዙ አፍሪካውያን የትውልድ ቀናቸውን ስለማያውቁ ዜና ለመከልከል የወጣ ደንብ ነው ። ባለሥልጣኖቹ ግን ያሰሩትን ሰው ትውልድና አድራሻ አይገልጡም ፤ ግዴታም የለባቸውም ፡

በአፍሪካ የጋዜጦች ሚና ስለተዳከመ በኅብረተሰቡ ውስጥ ተቀባይነታቸው በጣም ዝቅተኛ ነው ። የሚሰራጩበት ቅጅም አነስተኛ ነው ። በ1960ዎቹ በአረብ አፍሪካና በደቡብ አፍሪካ ፣ እንዲሁም በነጭ በሚገዙት የደቡባዊ አፍሪካ አገሮች ጭምር በጠቅላላው በአህጉሪቱ 299 ዕለታዊ ጋዜጦች እንደነበሩ ለንደን የሚገኘው ኢንተርናሽናል ፕሬስ ኢንስቲትዩት ባቀረበው ጥናት ይገልጥና ፣ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ ይህ ቁጥር ወደ 150 መውረዱን ያስረዳል ። ይህ ቅነሳ በአመዛኙ የታየው በጥቁር አፍሪካ ሲሆን ፣ ዘጠኝ አገሮች ጭራሽ ጋዜጣ የላቸውም ።

የጋዜጦች ቅጅ ቁጥርም በአፍሪካ በዚያው ዘመን ከሶስት ሚሊዮን ወደ ሁለት ሚሊዮን አዘቀዘቀ ። በዚህም መሠረት 455 ሚሊዮን ሕዝብ በሚኖርበት አህጉር ያለው የጋዜጣ ሥርጭት የአንዱን በለንደን የሚታተም “ዴይሊ ሚረር” ጋዜጣ የቀን ሥርጭት ሁለት ሶስተኛ ያህል ብቻ ነው ።

የኢንተርናሽናል ፕሬስ ኢንስቲትዩት ኃላፊ ፍራንክ ባርተን ሲናገሩ ፤ “በአፍሪካ ያለውን የፕሬስ ትግል ስትመለከቱት የሚያሳዝነው ሐቅ እየተሸፈነ መምጣቱን ነው ። የወደፊት እድሉም የተሻለ ይሆናል ብዬ አልገምትም ። ባለፉት አሥር ዓመታት በአፍሪካ ሁሉም ነገር እድገት አሳይቷል ፤ ትምህርት ፣ አውራ መንገዶች ፣ የሕክምና አገ

ልግሎቶች ፣ ጨምረዋል ። ጋዜጦች ግን እየተዳከሙ ሄደዋል ። እንዲያውም ከአሥር ዓመት በኋላ ከሃምሳ የበለጡ ጋዜጦች የሚኖሩም አይመስለኝም” ብለዋል ።

በአፍሪካ ለሁሉም ሕዝብ የሚደርስ ዜና ማሰራጫ ሬዲዮ ብቻ ነው ። እውነት ባይኖረውም የሚያስተላልፈው መልዕክት የመንግሥት መልዕክት ነው ። በገዢውና በተገዢው መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት የሚፈጥር ሚዲያ ነው ። በ1955 በአፍሪካ ግማሽ ሚሊየን ሬዲዮ ነበረ ። ዛሬ ግን ከሃያ አምስት ሚሊየን ሬዲዮ በላይ በአፍሪካ እንዳለ ይገመታል ። ይህም ማለት በአማካይ ግምት ለሃያ ሰው አንድ ሬዲዮ አለ ማለት ነው ። አንድ ጋዜጣ ቅጅ ለሁለት መቶ አሥር ሰው ፣ አንድ ቴሌቪዥን ደግሞ ለአምስት መቶ ሃያ አምስት ሰው እንዳላቸው ያህል ተሰልቷል ።

በአፍሪካ ሬዲዮ ጣቢያዎች ለአገሮች እርስ በርስ መወነጃጀያም ይውላሉ ። ብዙ የአፍሪካ አገሮች ለሀገር ውስጥ ሥርጭትና ለውጭ ሀገሮች የሚጠቀሙበት ሬዲዮ ጣቢያ አላቸው ። የውስጡ የራሳቸውን ሕዝብ እንደሚፈልጉት ለመቅረጽ ሲሆን ፣ የውጭው ደግሞ ከአገር ውጭ ያሉ ተቃዋሚዎችን ለመድረስና ሌሎች መንግሥታትን ስለራሳቸው ለማሳወቅ ነው ። ሶማሊያ ለምሳሌ በየቀኑ አንድ ሰዐት ወደ ኢትዮጵያ ፕሮፖጋንዳዋን ትረጫለች ። ከዚያም ወደ ደቡብ አቅጣጫ ታዞርና በኬንያ ላይ ታምባርቃለች ። አሜሪካንና እንግሊዝ በየቀኑ የአፍሪካ መንግሥታት በሬዲዮ የሚወነጃጀሉትን እየቀረጹ ይለዋወጣሉ ። ግማሽ እውነት የማይገኝበት ውሸት የሚያስተጋቡ ቢሆንም ስለአፍሪካ መንግሥታት አስተሳሰብ ጠቃሚ ፍንጭ የሚሰጥ ነው ። ስለ አዲስ ፖሊሲ ለውጣቸው ሁሉ አቅጣጫ የሚጠቁም በመሆኑ ለውጭ ጋዜጠኞችም ሆነ ለሥለላ መረጃዎች አሰባሰብ ጠቃሚ ነው ።

“እንደሚመስለኝ ሕዝባችን በሬዲዮ የምንነግረው ሁሉ ይዋጥለታል ብለን ማሰባችን ትክክል ያልሆነና የዋህነት ነው ። “ ይህን የተናገሩት የኬንያ የቀድሞ አቃቤ ሕግ ቻርልስ ንጆንጆ ናቸው ። እንግዲያው አፍሪካውያን እውነተኛውን ዜና የሚያዳምጡት ከየት ነው?



ከምዕራባውያን ፣ በተለይም ከቢ.ቢ.ሲ. እና ከአሜሪካ ድምፅ ሆኗል ። እነዚህ ሬዲዮ ጣቢያዎች ወኪሎች በየሀገሩ በማስቀመጥ አፍሪካውያን ስለራሳቸው አገር ከሚያቀርቡት ይልቅ ይበልጥ እውነትነት ያለው ዜና ያቀርባሉ ። ባለአጭር ሞገድ ሬዲዮ ላለው አፍሪካዊ ሁሉ ዓለም ዓይኑ ሥር ናት ።

በየዓመቱ በአ.አ.ድ. የመሪዎች ስብሰባ የልዑካን ቡድን አባላት በየምሽቱ ወደ ሆቴላቸው በመሄድ ቢ.ቢ.ሲ. እና የአሜሪካ ድምፅ ስለጉባዔው ምን እንደሚሉ ለመስማት ይጣደፋሉ ። በሶማሊያ በየቀኑ ከቢ.ቢ.ሲ. በአሥራ አንድ ሰዐት የሚተላለፈውን የሶማሊኛ ፕሮግራም ለመከታተል የቢሮ ሥራ ይቆማል ። የዛምቢያ ፕሬዚዳንት ካውንዳ በአሥራ ሁለት ሰዐት የቢ.ቢ.ሲ. ዜና ለመስማት የጋዜጠኞችን ቃለምልልስ አቋርጠው ሄደዋል ። የዛየር ፕሬዚዳንት ሞቡቱ ሴሴሴኮ ቢቢሲ እና ቪ.ኦ.ኤ. መስማት ስለሚያዘወትሩ በየጊዜው የእንግሊዝና የአሜሪካ አምባሳደሮችን እየጠሩ ሚዛናዊነት የጐደላቸው ስለሚመስሏቸው አንዳንድ ዜናዎች ቅሬታቸውን ይገልጣሉ ። አምባሳደሮቹ የዜና ወኪሎቹን ማዘዝ እንደማይችሉ ሲገልጡላቸውም ማመን ያቅታቸዋል ።

የናይጀሪያ መሪ የነበሩት ጄኔራል ያኩቡጎዋን በ1975 በኡጋንዳ በአ.ኡ.ድ. አመታዊ ስብሰባ ላይ እንዳሉ ከሥልጣን መወገዳቸውን የሰሙት ከየትም ሳይሆን ከቢ.ቢ.ሲ. ነው ። በአፍሪካ የቢ.ቢ.ሲ. ወኪል በመሆን ለሃያ ዓመታት ከአገር አገር እየተዘዋወረ ዜና ሲያስተላልፍ የነበረው ጆን፡ ኦስማን እጅግ ታዋቂ ከመሆን ሌላ በአገራችን ስለሚካሄደው የምናውቀው በአንተ ሪፖርት ነው በማለት አፍሪካውያን ይወዱት ነበር ።

አፍሪካ የራሷን ጋዜጠኞች ባለማመን ስለአፍሪካ ጉዳይ የውጭዎች በሚያቀርቡት ሪፖርት የመመካቷ ሁኔታ አንዳንድ ችግሮችን ይጠቁማል ። በሶስተኛው ዓለም የኢንፎርሜሽን ሥርጭት በምዕራቡ ቁጥጥር ሥር ነው ። በተለይም በአራቱ ታላላቅ የዜና ምንጮች በሮይተርስ ፣ በአጃንስ ፍራንስ ፕሬስ ፣ በአሶሺየትድ ፕሬስና በዩናይትድ ፕሬስ ኢንተርናሽናል አማካይነት የሚካሄድ ነው ። የምዕራብ ዜና

ወኪሎች አፍሪካን ያለሀዘኔታ ያጋልጡታል የሚሉት አፍሪካውያን እውነት አላቸው ። ምዕራቡ የሚጐረጉረው እንግዳ የሆኑ ጆሮ የሚስቡ ስሜታዊ ወሬዎችን እንጅ የአገር ግንባታ ችግሮችን ትንተና አይደለም ።አፍራሽ ክስተቶችን ብቻ ማስተጋባት ይመርጣሉ ።

በሌላ በኩል ስንመለከተው ደግሞ አፍሪካ ራሷ ስለአሜሪካ የምታቀርበው ዜና የበለጠ ስሜታዊ ነው ። ለምሳሌ በአሜሪካ ግዛት በኔብራስካ አንድ ገበሬ ተበሳጭቶ ቤተሰቦቹን ገደለ የሚለው ዜና ከፍተኛ ቦታ ሲሰጠው በወቅቱ አሜሪካ አናሳ ብሔረሰቦችን ለማበልፀግ የምታደርገው ጥረት ቸል ተብሏል ።

የአፍሪካ ችግር አገሯ ውስጥ የሚሰራጩትን የምትቆጣጠረውን ያህል ወደ ውጭ የሚላኩ ዜናዎችን ሳንሱር ማድረግ አለመቻሏ ነው ። ለምሳሌ በ1977 ኢትዮጵያ የዋሽንግተን ፖስት ጋዜጠኛ የነበረውን ዴቪድ ኦታዌ በማባረር ስለአብዮቱ ሚዛናዊ ትንተናሲያደርግላት የቆየውን ሪፖርተር አጣች ። ከሳምንታት በኋላ ደግሞ የአሜሪካ ጋዜጦች አብዮቱን ባለመውደድ የዜና ወኪል ለመመደብ ፈቃደኛ አልሆኑም ስትል አማረረች ። ናይጀርያም በአንድ ወቅት ሁሉም የአሜሪካ ሪፖርተሮች አገሯን እንዳይረግጡ አዘዘችና ከስድስት ወራት በኋላ ለአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት በላከችው የቅሬታ ደብዳቤ በአሜሪካ ጋዜጦች ስለናይጀሪያ አልተገለጠም በማለት ከሰዋል ።

በሶስተኛ ደረጃ የአሜሪካ ሪፖርተሮች የሚጽፉት ስለአፍሪካ አስከፊ ገጽታ ብቻ ነው የሚባለውም ስህተት ነው ። በአንድ ጥናት ውስጥ የተቀመረውን እንደተመለከትሁት አግባብ ባለው ቁጥር ዋና ጉዳዮችን ደጋግሞ የዳሰሰ ነው ። በዚህ ጥናት መሠረት የአንድ ሳምንት ዘገባ እንደሚያመለክተው በሳምንቱ ውስጥ ከተላለፉት የአፍሪካ ዜናዎች እንደሌላው ሶስተኛ ዓለም ሁሉ 62% ኤኰኖሚን ፣ የውጭ ግንኙነትንና የአገሩ መንግሥትን የሚመለከቱ ሲሆኑ ፣ 22% ደግሞ ስፖርትን ፣ ጤናን ፣ ሌሎችን የሚያካትት ነው ። ስለወታደራዊ ስለሁከት ፣ ሽብር ፈጠራ ፣ አደጋ ፣ ወንጀልና ፍርድ ነክ ጉዳዮች የተላለፉት ዜናዎች ቀሪዎቹ 16% ብቻ ናቸው ።

በዜና ነፃነት በኩል የተሻሉት አገሮች ኬንያ ፣ አይቮሪ ኮስትና



ሴኔጋል ሲሆኑ ፣ ለምዕራብ ጋዜጠኞች መግቢያ ቪዛ በመስጠት ረገድ ገደብ አያደርጉም ። ነገር ግን ብዙ መንግሥታት ዛሬም የጋዜጣ ወኪሎችን የሚመለከቷቸው በጠላትነት ነው ። የጋዜጠኞች ሥራም ፈታኝና አንዳንዴም አደገኛ እየሆነ ነው ። ሁሉን ዜና ከማስተላለፍ ይልቅ አስቸኳዩን እየመረጠ ማስተላለፍን መርጧል ። አስፈሪ የሚመስለውን ወይ ጐረቤት አገር ያስተላልፋል ። ያለዚያም ወደጋዜጣው እስኪመለስ ያቆየዋል ። ይህን ጥንቃቄ ባለማድረግ ያመኑበትን ከዚያው ያስተላለፉ ጋዜጠኞች በማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክ በቦካሳ ዘመን ፣ በናይጀሪያ ፣ በላይኛው ቮልታ ፣ ከፍተኛ አደጋ የደረሰባቸው አሉ ።

እንደሌሎች የአፍካ አገሮች ሁሉ ናይጀሪያ በበኩሏ ሚዛናዊ ሪፖርት ካስተላለፋችሁ ቅሬታ የለኝም ስትል ለምዕራብ ጋዜጠኞች ትናገራለች ። ከዚሁ ጋር አንዳንድ ማጋለጦች ቢተላለፉም ትክክል እስከሆኑ ድረስ አልታወምም ባይ ናት ። በተግባር ግን አውነቱ ከዚህ የተለየ ነው ። የአፍሪካ መሪዎች የሚፈልጉት ጋዜጠኝነት ጉራ የሚነፋ ፣ ድክመቶችን ቸል ብሎ የተከፈቱ የሕዝብ መገልገያዎችን በማድነቅ ለመንግሥት ጥብቅና የሚቆም ጋዜጠኝነት ነው ። ደግ ደጉን ብቻ በማቅረብ የሚጠቀሙት እነማን ናቸው ? ስለመልካሙ ነገር ብቻ መፃፍ መጥፎው ጉዳይ በኖ እንዲጠፋ አያደርገውም ።

የአፍሪካ አገሮች ከኮምኒስቱ ካምፕ ጋር በመወገን “ አዲስ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት ” እንዲፈጠር የተሟገቱትም ለምን እንደሆነ ስለሚታወቅ አያስገርምም ። የዚህም ውሣኔ ዓላማ የዜናን ነፃ ሥርጭት ለማገድ ነው ። ምክንያታቸውም ጋዜጠኝነት እጅግ ከፍተኛ ጉዳይ ስለሆነ በጋዜጠኞች ብቻ የሚተው አይደለም የሚል ነው ። ከቀረበው የውሣኔ ሃሳብ አንዱ ለምሳሌ መንግሥት ለጋዜጠኞች የሥራ ፈቃድ እንደሚሰጥና የዜና ድርጅቶች አንድ አገር በተሳሳተ መልኩ ዜና ቀርቦብኛል ካለ ማስተባበያ እንዲያወጡ እንደሚያስገድድ ይገልጣል ። አንዱን አንቀጽ ብንጠቅስ “ በራሳቸው ፍርድ ሰጪነት በአገራቸው የሚሰራው የብዙኃን መገናኛ በተገቢው መንገድ መሥራቱን ማረጋገጥ የመንግሥት ተግባር ነው ” ይህ ማለት ፕሬስን በሙሉ የመንግሥት ማድረግና የተባበሩት መንግሥታትን የሳንሱር እገዳ ኃላፊ እንደማድረግ ነው ።

አፍሪካ አሁን ባለው ሕግም ቢሆን ካስፈለጋት ዜናን መቆጣጠር ትችላለች ። የውጭ ጋዜጠኞች እንዳይገቡ ቪዛ መከልከል ብቻ ይበቃታል ። ያን ጊዜ ወደውጭ ሳይፈለግ የሚወጣ ዜና አይኖርም ። ሌላው አፍሪካ ያልገባት ነገር መንግሥት የሚቆጣጠረው ዜና በሶስተኛው ዓለምም ሆነ በአውሮፓና አሜሪካ የማይታመን መሆኑ ነው ። አፍሪካ ጋዜጠኞችዋ የሚጽፉት ዜና እንዲታመን ከፈለገች የሳንሱር መሰናክሎችን አውልቃላቸው ጋዜጠኞች እንዲሆኑ መፍቀድ ብቻ ነው ያለባት ።

ናይጀሪያና ኬንያ በአንፃራዊ ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች የተሻለ የፕሬስ ነፃነት የሚታይባቸው አገሮች ናቸው ። አያሌ ሂስ ያዘሉ ጽሁፎች በጋዜጦች ይቀርባሉ ። በናይጀሪያ አሥራ አራት ዕለታዊና ሃያ አራት ሳምንታዊ ጋዜጦች ሲኖሩ ፣ "ዴይሊ ታይምስ" የተሰኘው ጋዜጣም በ300,000 ቅጅ በመሰራጨት ከአፍሪካ ከፍተኛነቱን ይዟል ። ጋዜጠኞቹዋም ለመሪዎች ባለማጎብደድና በወታደሮች የመታሰርና ፀጉር የመላጨት መስዋዕትነት በመክፈል የአፍሪካን የመጨረሻውን የፕሬስ ነፃነት ከመዳፈን አድነውታል ።

የኬንያ ጋዜጦችም በርዕሰ አንቀጾች ጠንካራና የበሰሉ ሂሳዊ አስተያየቶች በመሰንዘር ገንቢ ሂስ ያቀርባሉ ። ከዚህም በቀር ስለወሲብ ፣ ስለወንጀል ፣ ስለቅሌት አወዛጋቢ እውነቶችን በማቅረብ ተወዳጅ ሆነዋል ። "ዴይሊ ኔሽን" የተሰኘው ዕለታዊ ጋዜጣ በ80,000 ቅጅ የሚቀርብ ሲሆን ንብረትነቱ የልዑል ላሪም አጋ ከሀን አምስተኛ ነው ። "እስታንዳርድ" የተሰኘው ሌላው ጋዜጣ ደግሞ ባለቤቱ የእንግሊዝ ድንበር ዘለል ኩባንያ የሎርንሆ ነው ። ብሔራዊ ፕሬስ በግል ባለቤትነት የሚካሄድባት ብቸኛዋ አፍሪካዊት አገር ኬንያ ናት ። እንዲያውም እነዚህ ትላልቅ ዕለታዊ ጋዜጦች እዚያ የማይኖሩ ግለሰቦች ንብረት መሆናቸው በዓለምም ልዩ ያደርጋቸዋል ።

እንዲያም ሲባል የኬንያ ጋዜጠኞች ምንም ገደብ የለባቸውም ማለት አይደለም ። የት ድረስ መተቸት እንደሚችሉ ያውቃሉ ። የቱ



በፕሬዚዳንቱ ገሸሽ እንደተደረገና ቢነቀፍም ችግር እንደማያስከትል ያውቃሉ ። የቱ የአፍሪካ አገር ቢነቀፍ ወቀሳ እንደሚያስከትልባቸው ያውቁታል ። ብሔራዊ ፖሊሲን በመተቸት ጥያቄ ውስጥ ካስገቡ ፣ ወይም መንግሥት እንደማይሠራ ከወቀሱ ወይም ፕሬዚዳንቱና ቤተሰቦቹን ከነቀፉ በቀጥታ በፕሬዚዳንቱ የሚታዘዘው የፖሊስ ኃይል መጥቶ ጆሮአቸውን ይዞ ከቤት እንደሚወስዳቸው ጠንቅቀው ያውቃሉ።

አንድ ኬንያዊ ጋዜጠኛ እንደገለጠልኝ ። "ስለፕሬስ ነፃነት ስንናገር ስለስፖርት ለመፃፍ ወይም የፍርድ ውሣኔውን ለማቅረብ ከሆነ በእርግጥ ነፃነት አለን ። ነገር ግን መንግሥትን የሚያሳፍር ፣ባለሥልጣንን የሚነቀፍ ጉዳይ ግን መፃፍ አንችልም ። ሁሉምነገር አንፃራዊ ነውና ማለት ያለብህንና የሌለብህን ታውቀዋለህ ። ጥርጣሬ ከገባህም ትተወዋለህ " በማለት አስረዳኝ ። ራስን ሳንሱር ማድረግ ከሁሉም የከፋና ጋዜጠኝነትን የሚገድል አሠራር ነው ።

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

# አቅም ያለው ይኖራል

" የአፍሪካ ሕዝብ ስለካንሰር በሽታ ሥጋት የሚያሳድርበት ረጅም እድሜ ድረስ አይኖርም ። ስለዚህም በምዕራብ የምንኖር የሚያሳስቡን የእርጅና በሽታዎች እሱን አያሳስቡትም ። በአፍሪካ ትልቁ ዘዴ እንደምንም ብሎ አምስት ዓመት እስኪሞላ መኖር መቻል ነው ። "

— ዶክተር ዴቪድ ፍሬንች
ከዓለም የጤና ድርጅት

ዶክተር ሚካኤል ውድ አብራሪው መቀመጫ ላይ ገብ አሉ ። አውሮፕላናቸው አነስተኛዋ ባለሁለት ሞተር ሴስና የምትባለዋ ናት ። የአውሮፕላኗን መሣሪያዎች ተመለከቱና ወደ መንደሪደሪያው አመሩ ። ከናይሮቢ ዊልሰን አይሮፕላን ማረፊያ ሴስና 182 የተባለች አውሮፕላናቸውን አበረሩና በቀስታ ወደ ላይኛው ቀዝቃዛ የማለዳ አየር ይዘዋት መጠቁ ። ከዚያም ወደ ደቡብ በማዞር አልፎ አልፎ ዛፍ በሚታይበት ቆላ ቀመሱ የግጦሽ መሬት ላይ ማብረር ቀጠሉ ። ከኒውዮርክ የመጡት ዶክተር ቶምሬስ ከካኪ ቁምጣቸው ላይ የአካባቢውን አገሮች የሚያሳይ ካርታ ዘርግተው ከጐናቸው ተቀምጠዋል ። እሳቸውም እንደ ዶክተር ውድ ታዋቂ የፕላስቲክ ቀዶ ሕክምና ሐኪም ናቸው ። ቀደም ሲል በ1950 ውሲኪ እየጠጡ ሲያወጉ አንድ ቅዱስ ሃሳብ መጥቶላቸዋል ። በየጫካው የሚኖሩ አፍሪካውያንን የሚያገለግል በራሪ ሆስፒታል ለመፍጠር የሚያስችል በቂ ገንዘብ መሰብሰብ ይቻል ይሆን ? የሚል ሃሳብ ነበር ።

ዶክተር ውድ አውሮፕላኑዋን ወደ 9,000 ጫማ ከፍ አደገው አመጠቋት ። የናይሮቢ ከተማ ትላልቅ ፎቅ ሕንፃዎች ከዓይን ራቁ ። ወዲያውም ከፊታችን ያለው ሜዳ ውስጥ ያሉት ቀጭኔና የሜዳ አህዮች ነጥብ አክለው ታዩን ። ከፊት ለፊት የክሊማንጃሮ ተራራ የበረዶ ቆቡን አድርጐ ከአካባቢው ልቆ ብቻውን ተገትሯል ። ከሥሩ እንጨት በሚያከስሉ ሰዎች የሚነዱ እሳቶች ብልጭ እልም ይላሉ።

"በአፍሪካ ጥሩ ሐኪም ለመሆን ከፈለግህ ወደ ታካሚዎች መሄድ አለብህ ። እስኪመጡ ከጠበቅህ ይሞታሉ ። አሁን የምናከማቸው ሰዎች ነፍሳቸው አለመውጣቷ እንጅ በከፊል የሞቱ ናቸው" ሲሉ ዶክተር ውድ ከኋላቸው ላሉት የሕክምና ዕቃና መድኃኒት ለያዙት አጫወቷቸው ።

ማይክ ውድ በ1946 ከሕክምና ትምህርት ቤት እንደተመረቁ በወጣትነታቸው ወደ አፍሪካ መጡ ። የመጡት ስድስት ወር ለማገልገል ነበር ። ነገር ግን ኬንያን በጣም ወደዱ ፤ በውበቷና ሊሰራ በሚገባው ሁሉ በመደሰታቸው ሳይመለሱ ቀሩ ። በኋላም አውሮፕላን ማብረር ቱማሩና ይችን አሮጌ ሴስና አውሮፕላን ገዙ ። ከዚያም ከዶክተር ሪስ እና ከዶክተር ምክንዶ ጋር ሆነው የምሥራቅ አፍሪካ በራሪ ሃኪሞች አገልግሎት እየተባለ የሚታወቀውን ድርጅት አቋቋሙ ። ይህም የርዳታ ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤቱ ናይሮቢ ሆኖ ከመላው ዓለም በሚያገኘው ርዳታ የሚሠራ ነው ። ከ1960 ጀምሮ በራሪ ሀኪሞች አራት ሚሊዮን ማይልስ በረው ግማሽ ሚሊዮን ገበሬዎች አከመዋል ። በፋኖስ መብራት ምልክት በጫካ ዳር ባገኙት ሜዳ እያረፉ በመቶ የሚቆጠር ሕይወት አድነዋል ። በሺህ የሚቆጠሩ ክሊኒኮች በማቋቋም ስለንፅሕናና ስለመሠረተ ጤና ጥንቃቄ አስተምረዋል ።

ከናይሮቢ 140 ማይልስ በስተደቡብ ምሥራቅ ኢታላል የተሰኙ ቦታ ለማረፍ አውሮፕላኑዋን ዝቅ ሲያደርጓት የጭቃ ቤቶችና የዘላኖች ጐጆዎች ታዩን ። የማሳይ ጐሳ ዘላኖች ከተንገፉ ክሊኒክ አጠገብ ተደርድረዋል ። ክሊኒኩ በአውራጐዳና ወደዚያ የተጓዘው ትናንት ነው ። ዶክተር ውድ ሴስናቸውን በአቅራቢያው ካለ መስክ ላይ አቆሙና ራቁታቸውን ቆመው አውሮፕላኗ ላይ የሚያፈጡትን



ልጆች በስዋሂሊ ቋንቋ ቅርንጫፍ ቆርጠው ጉማዎቹን እንዲሸፍኑ ነገሯቸው ። ከአሁን ቀደም የአውሮፕላንዋን ጎማ ጅብ በጭቆባቸው መመለሻ ተቸግረው ስለነበረ ነው ።

የማሳይ ጐሳ አባላት ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ሀኪም ለማነጋገር ከሰላሳ ማይል ርቀት ድረስ የመጡ ናቸው ። ልጆች ያቀፉ እናቶች አሉባቸው ፤ ዝንብ የወረራቸው ሕፃናት ተደርድረዋል ፤ ወባ ያንኮታኮታቸው አዛውንቶች መመርመሪያቸው ድንኳን ጥግ ተጋድመዋል ። አንበሳ የገደሉ ጐረምሶች ልዩ ምልክታቸውን አድርገውና ጦራቸውን ጨብጠው ቆመዋል ፤ የፈንጣጣ ክትባት ለመወጋት ግን ይሰቃጠጣሉ ። ከታካሚዎች መካከል አንበሳ የቦጨቃቸው ፤ ዝሆን የረገጣቸው ፤ እሳት የፈጃቸው ሲገኙበት ፤ ዶክተር ውድ የፕላስቲክ ቀዶ ሕክምና ያደርጉላቸዋል ። በዶክተሩ ግምት ሕዝቡ ጥንቃቄ ቢያደርግና በአቅራቢያው ዘመናዊ የጤና ክሊኒክ ቢኖረው ከታካሚዎች ሰማንያ በመቶው እዚህ ባልደረሱም ነበር ።

ዶክተሮች ሲመረምሩ ከጎን በኩል ፈንጠር ብሎ ደግሞ ኬንያዊው ረዳታቸው የተቅማጥ በሽታን እንዴት ማዳን እንደሚቻል ለሕዝቡ ትምህርት ይሰጣል ። ዶክተር ውድ ብቅ አሉና "ሥራችንን ተመለከትህ አይደለም? . . . የአፍሪካ የጤና አገልግሎት ደረጃ በአውሮፓ ከኢንዱስትሪ አብዮት በፊት የነበረው ዓይነት ነው ። እንዲያው እንሯሯጣለን እንጅ ይህን ትውልድ ለማዳን ጊዜው አልፎብናል ። ጥያቄው የሚቀጥለውን ትውልድ ለመርዳት ምን ማድረግ አለብን ነው ።

የአፍሪካን እድገትና ልማት አንቆ የያዘው ከምንም ይበልጥ የጤና ችግር ነው ። አፍሪካውያን ሁሉም "የአምላክ ፈቃድ ነው" በማለት ያልፉታል ። እናቶች አሥራ ስድስት ድረስ በመውለድ ምናልባት ግማሾቹ ቢያድጉልኝ በሚል ተስፋ ያደርጋሉ ። ወላጆች እንዲት ጠብታ መድኃኒት የለምሻ በሽታን ለማስወገድ ትችላለች ብለው ለማመን ይቸገራሉ ። በእነሱ እምነት ልጆቻቸውን ሽባ የሚያደርገው ርኩስ መንፈስ ነው ። ንፁህ ውሃ መጠጣት ጤናን ለመጠበቅ ስለ መርዳቱ እምነት የላቸውም ። ልጆቻቸው ሲታመሙ "የእግዚአብሔር

ቁጣ ነው ፣ ፈቃዱ ቢሆን ጠንቋይዋ ታድናቸዋለች” በማለት ሁሉንም ወደ ታላቁ ኃይል ያያይዛሉ ። ወይም በቤተሰባቸው ቀደም ሲል ለተሠራ ኃጢያት አምላክ ያዘዘው ቅጣት ነው ይላሉ ።

ከበድ ያለ ወረርሺኝ በሽታ በሚመጣበት ጊዜ አፍሪካውያን የተለየ ጥንቃቄ ያደጋሉ ። በ1977 ቻድ ውስጥ ኮሌራ ገብቶ የመንደሮችን ሕዝብ ግማሽ ያህል ሲገድል ኅብረተሰቡ ውሃ አፍልቶ እያበረደ መጠጣት ለመደ ። ነገር ግን ወዲያው በሽታው ጋብ ሲል ወደ ቀድሞው ዓይነት አኗኗር ተመለሰ ።

ዳንኤል ምዋንጊ የተባለ ኬንያዊ በስድስት ዓመቱ ዓይኑን እየቆጠቆጠና እይታውን እየጋረደ ራስ ምታት ጭምር ሲያስቸግረው አባቱ እርግማን ነው በሚል ከሀኪም ቤት ይልቅ ወደ ጠንቋይ ቤት መሄድን መረጠ ። አሥራ ስድስት ዓመት ሲሞላው ዳንኤል ሙሉ በሙሉ ታወረ ። የጠንቋዮች ቅጠል መበጠስና ሥር መማስ ወይም ይህን እረድ ፣ ያንን አድርግ ማለት አላዳነውም ። የልጁ በሽታ ትራኮማ ስለነበር በቀላሉ በዘመናዊ ሕክምና ሊወገድ የሚችል ነው ። የዳንኤል አባቱ ግን እስከ ዕለተ ሞቱ ልጁ በቤታችን በተፈጸመ ኃጢያት ቅጣቱ በእሱ ላይ እንዲፈጸም አምላክ ወስኖ ነው ከሚለው እምነቱ ዝንፍ አላለም ።

አባቱ እንዲያ ያደረገው ባለማወቅ መሆኑን ስለሚገነዘብ ዳንኤል በማንም ቅሬታ የለውም ። በአጋጣሚም እውራን ት/ቤት ገብቶ ስለተማረ ሥራ ተቀጥሯል ። እሱ እድለኛ ይሁን እንጅ በኬንያ ያሉት ብዛት ያላቸው አካለ ጎደሎዎች የሥራ ዕድል አላገኙም ። በኬንያ አንድ አስረኛው ሕዝብ የአካል ጉድለት ያለበት ነው ። ትምህርትም ሆነ ሥራ የሌላቸውና መንግሥት ልዩ ክብካቤ ያላደረገላቸው ስለሆነ የወደፊት ዕድላቸው ጨለማ ነው ። ለዚህ ሥራ ይስማማሉ ሳይባሉ የተረሱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሶስተኛው ዓለም ሕዝቦች ። የየአንዳንዱ አፍሪካ አገር ከተሞች ብዙ ቁጥር ባላቸው በየአውራ መንገዱ ማቋረጫ የሚንኳተቱ ሰባራና ሰንካላ ለማኞች የተሞሉ ናቸው ።

በቆየው የአፍሪካ ልማድ በገጠሩ የታወሩና የደነቆሩ ወይም አካላቸው የጐደለ በቤተሰባቸውና በኅብረተሰቡ ክብካቤ ይደረግላቸው



ስለነበር ልዩ ትምህርት ቤትም ሆነ የሕክምና አገልግሎት አያሻም ነበር ። በአፍሪካ ከተሞች እያደጉ ሲመጡ ግን ኅብረተሰቡ ዋጋ ይሰጠው የነበረው ይህ ባህል ተለወጠ ። አካለ ስንኩሎችም ወደ ከተሞች መጉረፍ ጀመሩ ። ሳንቲም ልመናና ሕክምና ፍለጋ ባዘኑ ። ለብዙዎቹ ምንም ሥራ የለም ። የቀርቀሃ ሥራዎችንና አሻንጉሊቶችን በመሥራት ለቱሪስቶች መሸጥ የሚሞክሩት ጥቂቶች ናቸው ። የአፍሪካ መንግሥታትም የገንዘብ ችግርና ሙሉ አካል ያላቸውንም የሥራ ዕድል ለመስጠት መሰናከል ስላለባቸው ለእነዚህ ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጡ አልቻሉም ።

አፍሪካ የሕክምና አገልግሎት ያልተስፋፋባት ደካማ አህጉር በመሆንዋ አልታደለችም ። ከአንድ ሺህ ሕፃናት አንድ መቶ ሰላሳ ሰባት አምስት ዓመት ሳይሞላቸው በሞት ይቀጫሉ ። ይህም አሃዝ ከዩናይትድ እስቴትስ በአሥራ አንድ እጅ ይበልጣል ። በአውሮፓ ለአምስት መቶ ሰማንያ ሰዎች አንድ ሀኪም አላቸው ፣ የተሻለ አድጋለች በምትባለው ኬንያ ለ25,600 ሰዎች አንድ ሀኪም ሲኖር ፣ የመጨረሻ ድሃ ከሚባሉት አንዷ በሆነችው ቡርኪናፋሶ ለ92,000 ሕዝብ አንድ ሀኪም ብቻ አለ ።

መንጋጋ ቆልፍ ፣ ለምሻ ፣ የሚያስተኛ በሽታ ፣ ወዘተ የሚባሉት ሕመሞች በበለፀገው ዓለም ያልነበሩና ወይም ጨርሶ የተረሱ ሲሆን የአፍሪካን ሕፃናት ግን ዛሬም በመቶ ሺዎች እየፈጁ ነው ። ተቅማጥ ነክ በሽታዎች ብቻ በአፍሪካና በደቡብ ምሥራቅ እስያ በየዓመቱ 17,000,000 ሕፃናትን ይገድላሉ ። ይህም በየዓመቱ የታንዛንያን ሕዝብ ያህል ያልቃል ማለት ነው ።

ይህ ሁሉ መከራ ተደራርቦበት የአፍሪካ ሕዝብ ቻይ ነው ። የሚማረር ወጣትም ሆነ ጎልማሳ የለም ። ሴቷ ዛሬ ወልዳ በማግሥቱ ለሥራ ደፋ ቀና ትላለች ። ከባድ ቀዶ ሕክምና የሚደረግላቸው ወንዶች በነጋታው ተነስተው ይሄዳሉ ። ከኦፕራሲዮን በኋላ የሚያጋጥመው የአካል ማመርቀዝ ወይም ቂም መያዝ (ኢንፌክሽን) በአፍሪካ አራት በመቶ ብቻ ሲሆን ፣ በምዕራቡ ዓለም ሆስፒታሎች አሥራ አምስት በመቶ እንደሚደርስ እነዚሁ በራሪ ሀኪሞች ይናገራሉ ። ይህም የሚያ

ሳየው አፍሪካውያን በተፈጥሮ ምርጫ ሂደት ጠንካራ የሆኑና ከሕፃ
ንነትም በሽታዎችን ተቋቁመው ያደጉ መሆናቸውን ነው ።

የአፍሪካውያን አመጋገብ የተሟላ ስላልሆነ በሽታዎችን ለመ
ቋቋም የሚያበቃ አቅም ለማግኘት የሚያስችል አይደለም ። ከአፍሪካ
ሕፃናት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የተመጣጠነ ምግብ እንደማያገኙ
ኤክስፐርቶች ይናገራሉ ። የናይሮቢ የእህል ሰብል ሳይንስ መምሪያ
እንደገመተው የምሥራቅ አፍሪካ የአመጋገብ ባህል ለሕዝቡ የሚያስ
ገኘው ከአስፈላጊው መጠን ሙቀት ሰጭ ምግብ (ካሎሪስ) 44% ብቻ
እና 18% ገንቢ ምግብ (ፕሮቲን) ብቻ እንደሆነ ያስረዳል ። በከተማ
የሚኖሩ ሀብታም ኬንያውያን እንደ አሜሪካውያን ሥጋ ፡ ድንችና አት
ክልት ያቀፈ ራት ሊመገቡ ቢችሉም አብዛኛው አፍሪካዊ ግን የሚ
መገበው በባህሉ መሠረትና መሬቷ ያፈራችውን ነው ።

በቪክቶርያ ሀይቅ ዳርቻ የሚኖሩ ኬንያውያን በፀሐይ የደረቀ ዓሣ
ሲመገቡ አቅራቢያቸው ያሉ ሌሎች ጐሳዎች ደግሞ ዓሣ አይቀም
ሱም ። በዚህም ምክንያት ፕሮቲን አያገኙም ፡ ልጆቻቸው በተመጣጠነ
ምግብ ማጣት በሕፃንነታቸው በበሽታ ሲቀጩ ለምን እንደሆነ አይ
ገባቸውም ። ናይሮቢ አካባቢ በሚኖሩት የኩኩዩና የካምባ ጐሣዎች
ከዓመት እስከ ዓመት በየቀኑ የበቆሎ ገንፎ ይመገባሉ ። ከብት አርቢ
የሆኑት የማሳይ ጎሳ አባላት በወተት ፣ በቅጠላቅጠልና ከከብቶቻቸው
በሚመጡት ደም ይኖራሉ ። በኡጋንዳ አይጦች ምርጥ ምግብ ሲሆኑ፥
በዛየር ደግሞ የዝንጀሮ ሥጋ ብርቅየ ነው ።

በአሥራ ስምንተኛው ምዕት ዓመት ወደ አፍሪካ ከመጡት አው
ሮፓውያን ብዙ በሞት ተቀጠፉ ። አፍሪካውያን የተቋቋሚቸውን ብዙ
በሽታዎች ሊቋቋሙ ተሳናቸው ። ዛሬም ቢሆን በመሬት ወገብ አካባቢ
የሚገኙ በሽታዎች (ትሮፒካል ዲዚዝ) በሰፊው በተጠኑበት ዘመን
መድኃኒት ያልተገኘላቸው በርካታ በሽታዎች አሉ ።

የእረንጓዴ ዝንጀሮ በሽታ የሚባለው ለምሳሌ በከባድ ትኩሳት
ከታችና ከላይ ደም አስተፍቶ በሳምንት ውስጥ የሚገድል በሽታ
ሲሆን መድኃኒት አልተገኘለትም ። ሌላው የቀንድ አውጣ ትኩሳት
የተሰኘና ወደ ደም ውስጥ በሚዘልቁ ተዋሃሲያን ጉበትና ጣፊያን



አሳብጦ አንጀትን በማድማት የሚገድል በሽታ ሲሆን መድኃኒት
የለውም ። ከዚህ ሌላ የሚያስተኛ በሽታ የሚያስከትሉ ጼ.ጼ. ዝንብ
የተሰኙት እንሰሳትና ሰውን የሚያሳምሙ ናቸው ። የበሽታውም ምል
ክቶች ትኩሳት ፣ ድካም ፣ ማንቀጥቀጥ ፣ የመሳሰሉት ሲሆኑ ካልታ
ከሙ ሞትን ያስከትላል ። ከ1900 እስከ 1922 በኡጋንዳ 330,000
ሕዝብ የፈጀ ሲሆን እስካሁንም መከላከያ ክትባት ያልተገኘለት ከመ
ሆኑም በቀር መድኃኒቱም ቢሆን ሌላውን የአካል ክፍል የሚመርዝ
ነው ።

በአፍሪካ ሌላው አስቸጋሪ በሽታ በወንዝዳር ያሉትን የሚያ
ጠቃ የዓይን በሽታ ነው ። በፍጥነት በሚወርድ ወንዝ አካባቢ በሚ
ራቡ አነስተኛ በራሪ ቢምቢዎች ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍና
በከፊል ወይም በሙሉ የሚያሳውር አደገኛ በሽታ ነው ። በምዕራብ
አፍሪካ በቡርኪናፋሶ በብዛት ችግር እያደረሰ ነው ። በዚህም የተነሳ
ነዋሪዎች ለሙን የወንዝ ዳር እየለቀቁ ወደ ተራቆተው መሬት
በመሄድ አምርተው ለመብላት ተስኗቸው ይገኛሉ ። ተፈጥሮን መግ
ራት ተስኖት መሬቷ እየተቆጣጠረችውና የወደፊት ዕድሉን እየወ
ሰነች ነው ።

የዓለም ጤና ጥበቃ በዓመት 10,000,000 ዶላር እያወጣ ባካ
ሄደው ጥረት ዛሬ በሽታው በብዙው ቀንሷል ። ይህ ዓይነቱ የዓይን
በሽታ (ሪቨር ብላይንድነስ) በላቲን አሜሪካም የሚገኝ ሲሆን ፤ ከምሥ
ራቅ አፍሪካ አካባቢ ለማጥፋት ቢቻልም በምዕራብና ማዕከላዊ አፍ
ሪካ እንደተንሰራፋ ነው ።

ይህ በሽታ ከምሥራቅ አፍሪካ መጥፋቱ የሰው ልጅ በሽታም
ችን በማስወገድ ጤንነትን ሊያላብስ እንደሚችል ሌላው ማረጋገጫ
ነው ። በ1980 ፈንጣጣ ከዚህ ዓለም ምድር መወገዱ የሰው ልጅ
በታሪኩ ለመጀመሪያ ጊዜ በሽታን ጨርሶ ማጥፋት እንደሚችል
ያስመዘገበበት ዘመን ነው ። ከአሥር ዓመታት በፊት ይህ በሽታ ከሶስ
ተኛው ዓለም በዓመት ሁለት ሚሊዮን ሕይወት ይቀስፍ ነበር ። በምዕ
ራብ አፍሪካ ደግሞ ይኸው በሽታ አንድ አሥረኛ የሚሆኑትን ሕፃ
ናት ወይ ገድሏል ፤ ያለዚያም የአእምሮ በሽተኛ አድርጓቸው ቀርተዋል ።

የፈንጣጣ ማጥፊያ ፕሮግራም ከ1967 እስከ 1980 ድረስ 300,000,000 ዶላር ወጪ ተደርጎበታል ። ይህ የገንዘብ መጠን የላስ ቬጋስ ዱርየዎች በየዓመቱ በቁማር ከሚያጠፉት እሩብ ብቻ ነው ። የመጨረሻው የፈንጣጣ በሽታ የጠፋው በአፍሪካ (በኢትዮጵያና ሶማሊያ ድንበር) መሆኑም አያስደንቅም ። የመጨረሻዎቹን የፈንጣጣ ሕመምተኞች ፈልጐ ለማከምና ጨርሶ መጥፋቱን ለማረጋገጥ በሁለቱ ሀገሮች ድንበር አካባቢ በተደረገው የሐኪሞች ዘመቻ ፣ ፈንጣጣ የያዘውን ሰው የጠቆመ አንድ ሺህ ዶላር እንደሚሰጠው ታውጆ ነበር ። በዚሁ በሀኪሞች የአየር ፣ የመኪናና የእግር አሰሳ ሜርቃ በምትባል የሶማሊያ ከተማ የመጨረሻው ታማሚ አሊ ማው ማሊን የተሰኘ የሃያ ሶስት ዓመት ወጣት ተገኘና ሕክምና ተደረገለት ። ሌላ ሪፖርት የተደረገ የፈንጣጣ ሕመምተኛ ባለመገኘቱ የዓለም ጤና ጥበቃ ድርጅት በ1980 በጄኔቫ ባደረገው ጠቅላላ ስብሰባ ፈንጣጣ መሞቱን አበሰረ ።

የፈንጣጣ መጥፋት በአፍሪካ የአካል በሽታዎችን ለማስወገድ ያለውን ተስፋ ሲያበስር ለአእምሮ ሕመምተኞች ግን እድሉ ጠባብ ነው ። በብዙ የአፍሪካ አገሮች የአእምሮ ሕመም አሁንም በአስፕሪንና በባህል መድኃኒት የሚታከም ነው ። የሥነ—አእምሮ ሕክምና በአፍሪካ የማይታወቅ ሙያ ነው ። የአእምሮ መታወክ ወይም ጭንቀት ያለዚያም ከመጠን ያለፈ ደስታ ሲሰማቸው ከፋኝ ወይም ተደሰትሁ ከሚሉት ቃላት ሌላ የሥነ—አእምሮ ሁኔታ መግለጫ ሳይንሳዊ ቃላት የላቸውም ። ለምሳሌ ኬንያ ሰባት የሥነ—አእምሮ ሐኪሞች ሲኖሯት በሌሎች አገሮች ከዚህም ያነሰ ነው ። ከጥቂት ዓመታት በኋላ በ2000 ዓ/ም የሥነ አእምሮ በሽታ በአፍሪካ ከፍተኛውን ደረጃ እንደሚይዝ በሊቃውንቱ ተገምቷል ። ሆኖም ለዚህ ችግር እስካሁን ምንም ዝግጅት የለም ።

በአፍሪካ ማህበራዊ ችግሩ የአእምሮ መቀወስን የሚያስከትል እየሆነ በመምጣቱ ፣ ራስን መግደል ፣ ጠጭነት ፣ ጭንቀትና ብስጭት የመሳሰሉት ኑሮ በከበደ ቁጥርና የገንዘብ ዋስትና በጠፋ ጊዜ ሁሉ እየጨመሩ መሄዳቸው ይታያል ።



እንግሊዝ አገር የሰለጠኑት ኡጋንዳዊ የሥነ—አእምሮ ሐኪም ዶክተር ዮሴፍ ሙሃንጊ ስለችግሩ ሲያስረዱኝ ፣ “. . . አምስት ሚስቶችና ሃያ ልጆች ያሉት አንድ አፍሪካዊ እስላም ፣ በያዛት ትንሽ መሬት ላይ በኋላቀር መሣሪያ አርሶ ለማብላት በሚያደርገው መፍጨርጨር ጭንቀት የለበትም ይመስልሃል?” አሉኝ ።

መላው የአፍሪካ ሕብረተሰብ በሽግግር ወቅት በሚሆንበት ዘመንስ? ማኅበራዊ አወቃቀሮች ሲቀየሩ ፣ የገጠሩ ሕዝብ ወደ ከተሞች መፍለስ ሲጀምር ፣ የቆዩ ወግና ልማዶች በምዕራቡ ባህል ሲለወጡ፣ ወጣቶች ኑሮን ለማሳካት ገጥሟቸው የማያውቁት ዓይነት ፉክክር ውስጥ ሲገቡስ ? ይህን ሁሉ ስናጤን አፍሪካውያን ዛሬ ከሰለጠነው ዓለም ሕዝብ በበለጠ የኑሮ ጫና አለባቸው ።”

ዶክተር ዮሴፍ ሙሃንጊ በሚሰሩበት የሥነ አእምሮ ክሊኒክ የተሰበሰቡ ሕመምተኞች በሽታው የአእምሮ መሆኑን አይረዱም ። ሙሃንጊ ሲጠይቋቸው “ኮሌራ ሳይዘኝ አልቀረም” የሚል መልስ ይሰጣሉ ።

ከታካሚዎቹ አንዱ ፊሊፕ ንጌዎ ከሀኪሙ ፊት ፈዝዞ ቁጭ አለ ። ዕድሜው አርባ ዘጠኝ ሲሆን የሕክምና ላቦራቶር ቴክኒሽያን በመሆን በወር አንድ መቶ ዶላር ያገኛል ። ከዚህ ገቢ ግማሹን ለአሥራ ሶስቱ ልጆች ትምህርት ይከፍላል ። የቡና ሰብሉን ከባድ ዝናብ አበላሽቶበታል ። የከንድ ቁርጥማትና ድካም ሲሰማው ከርሞ እንደጥ ሚስቱ ከሞተች በኋላ ደግሞ ብሶበታል ። ቀደም ሲል በተደረገለት ምርመራ ግን ምንም የትውሳክ ምልክት አልተገኘም ። እንደቀድሞው የልማት ሥራውን ለማከናወን ጉልበት እንደማያገኝ ፍርሃት አድሮበታል ።

“እስቲ ንገረኝ ፊሊፕ ፣ ሌሊት እንቅልፍ በደንብ ይወስድሃል?” አሉት ዶክተሩ ።

“እንዲያውም ጭራሽ አልተኛም ። ዶሮ ሳይጮህ ነው የምነሳው ፣ ሁልጊዜ ይደክመኛል ፣ ግን እንቅልፍ አይወስደኝም” አለ ።

“ችግሩ ምን ይመስልሃል ?”

"ኮሌራ ይመስለኛል ። በኮሌራ ተረግሜ ነው" ።

"እሃ ፣ እሺ የሚያስፈሩህ ነገሮችስ ?አእምሮህ እንዴት አካል ህን እንደ ሚቆጣጠርና ሕመም እንደሚፈጥር ላስረዳህ ። በልጅነቴ ኡጋንዳ ውስጥ ፍየሎች ስጠብቅ አንዳንድ ጊዜ በቆንጥር ውስጥ ስሮጥ እግሬ ይቆስላል ። ያን ጊዜ ሀሳቤ ሁሉ በጐችን መጠበቅ ላይ ስለሆነ አይሰማኝም ። ሲመሽ እቤት ገብቼ እናቴ ደሙን አይታ ስት ጠይቀኝ ህመሙ መሰማት ይጀምረኛል ።

ሙሃንጊ ለፊሊፕ ሕመም ማስታገሻ መድኃኒት እየፃፉለት

"ሕመሙ የእውነት ነው ፣ ግን በሽታህ ከአእምሮህ የሚመነጭ እንጅ ከአካልህ አይደለም" አሉት ።

"ይሆናል ፣ ግን ለኮሌራው የሚረዳኝ ክኒን የለዎትም?" በማለት ጠየቀ ። ፊሊፕ በሩን ከፍቶ ሲወጣ ቴሬሳ የምትባል ድንክ ልጅ ከእ ናቷ ጋር ገባች ። ቴሬሳ አሥራ አምስት ዓመቷ ሆኖ ቁመቷ ግን ሶስት ጫማ ብቻ ነው ። በክፍሏ ውስጥ አንደኛ ናት ። ድንክ መሆኗ ከተነ ገራት ጀምሮ ራስ ምታት ፣ የሆድ መታወክና እንቅልፍ ማጣት ተጠና ውቷታል ። የትምህርት ቤቷ ድሬክተር ትንሽ ስለሆነች ወደሚቀ ጥለው ክፍል እንዳትዛወር ከልክሏታል ። አንድ ኬንያዊ ሐኪም ደግሞ ልትታከም ሄዳ አግኝቷት የሕክምና ተማሪዎችን ስለ ድንክ ለማሳየት ሲል አንድ ክፍል አስገብቶ ማስተማሪያ አድርጓት ነበር ።

ሙሃንጊ ተበሳጩና "የትምህርት ቤቱ ድሬክተር ደደብ ነው"። አሉና ለልጅቷ የሚጫጫናትን የሚያቀልላት መድኃኒት በማዘዝ ለድ ሬክተሩ ደግሞ ከጓደኞቿ ጋር መዛወር አለባት የሚል ማስታወሻ ፃፉ ።

ቀጠል አደረጉና ሙሃንጊ ለእናቷ "ጉበዝ ልጅ ነች ። ሌላው ቢያቅታት አንድ ቀን አዋቂ ሆና መጽሐፍ የምትደርስና ማርቸዲስ የምትገዛ ልትሆን ትችላለች ። "ተብታባዎች እንኳ ጥሩ ዲስኩር ተና ጋሪ ይሆናሉ ። ቴሬሳም የተሟላ ደስተኛ ሕይወት ሊኖራት ይች ላል ። ይገባሻል እናት?" አሏት ። እናትየዋ ምንም መልስ ሳትሰጥ ሌላ የሚነግሯት ካለ ለመስማት በዝምታ ጥቂት ጠበቀች ። ዶክተሩ ግን ሌላ የሚሉት ነገር አልነበራቸውም ።



በኬንያ የአእምሮ ሕሙምተኞች ማቆያ አንድ ሆስፒታል ብቻ አለ ። ሊይዝ የሚችለው አንድ ሺህ ሕሙማንን ብቻ ሲሆን ከአጥፍ በላይ ታጭቀውበታል ። ከአንድ ሶስተኛ የሚበልጡት በወንጀል ክስ (ንብረት በማውደም) የገቡ ናቸው ። ከፊሉቹ ሐኪም የማነጋገር እድል ሳያገኙ ትንሽ ሳምንታት ቆይተው እንደዚያው እየተዘባነኑ ይወጣሉ። በሆስፒታል ውስጥ ያለው መቆያቸው እንደ አራዊት መመልከቻ ግቢ (ዙ) የመሰለ የብረት መስኮት ያለው ሲሆን በየወለሉ ላይ የሙዝ ልጣጭና ሰገራ የተንጠባጠበበት ሆኖ ከላይ ጣርያ የሌለው በረት ነው ። በውስጡ እንደ እንስሳ የታጎሩ ስድሳና ሰባ የሚሆኑ ሰዎች አሉበት ። ዓይናቸው እየተጉረጠረጠና በከፊል ራቁታቸውን ሆነው ይታያሉ ።

ከዚህ ሁኔታ ተነስተን ስንመረምር በአፍሪካ እንደቀድሞው ሁሉ የአሁኑ ጊዜም የጤና ክብካቤ ቀዳሚ ምንጭ የባህላዊ ሕክምና ሆኖ እናገኘዋለን ። መድኃኒት አዋቂ ወይም ጠንቋይ የሚሏቸው የባህል መድኃኒት አዋቂዎችን ፣ የአካልም ሆነ የአእምሮ በሽታ የሚያክሙ ፣ ኮከብ በመቁጠር ወይም አጋንንት በመሳብ እርግማንን የሚያስሰርዙ አድርገው ይገምቷቸዋል ።

የባህል መድኃኒት አዋቂዎች ጥንቆላም ጨምሩ ፣ ቅጠልም በጠሉ፣ ሥርም ማሱ ፣ ዞሮ ዞሮ ከጎሳ መሪዎች ብዙም ባላነሰ ተከብረው ለአያሌ ትውልዶች ሕዝቡን ሲያክሙ ኖረዋል ። በተፈጥሮ ተሰጥኦ ወይም ከወላጆቻቸው በተላለፈ ታምራዊ እውቀት እንደሚያክሙ የሚናገሩት እነዚህ ሰዎች ኋላቀር መተተኞች ተብለው መጀመሪያ በመጡ የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ተጥላልተው ነበር ። ሥራቸውን በድ ብቅ አደረጉት እንጅ ሕዝቡ ወደ እነሱ ከመሄድ አልተቆጠበም።

አውሮፓውያን ሀኪሞች ወደ አፍሪካ ከመምጣታቸው በፊት ለአያሌ ምዕት ዓመታት አፍሪካውያን ሲረዱ የኖሩት በባህል መድኃኒት አዋቂዎች ነው ። ዛሬም ቢሆን በብዙ የአፍሪካ አገሮች አብዛኛውን ሕዝብ የሚያክሙ እነሱ ናቸው ። ለምሳሌ በምዕራብ አፍሪካ በማሊ ዘመናዊ የጤና አገልግሎት የሚያገኘው ሕዝብ አሥራ አምስት በመቶ ብቻ ነው ። የቀሩት በባህላዊ ሕክምና የሚረዱ ናቸው። በአንዳንድ በሽታዎች የባህል መድኃኒት የተሻለና ፈጣን ፈውስ

የሚሰጥበት ሁኔታም አለ ። ለምሳሌ የወፍ በሽታ እየተባለ ለሚጠቀ ሰው የጉበት ሕመም የዛፍ ግንድ ልጣጭ ፍቀውና ጨምቀው በወ ተት በመስጠት በሰባት ቀን ውስጥ ለታማሚው ፈውስ ያስገኛሉ ። ሆድ ለማለስለስ (ለድርቀት )፣ ለስኳር በሽተኞችና ለአስም ሕሙማን የሚሰጡትም መድኃኒት ውጤት የሚናቅ አይደለም ።

ባህላዊ መድኃኒት የበሽታውን አካላዊና ሕዋሳዊ ቅምር ቸል ሳይል አቀራረቡ ማኅበራዊና ሥነልቡናዊ ትኩረትም ይሰጣል ። የተ ዋወቅሁት የማሊ የባህል መድኃኒት አዋቂ ሳቲጊ ሕሙማንን ሲያነ ጋግር በቅድሚያ የሕይወት ታሪካቸውን ይጠይቃል ። በአእምሮአቸው ላይ ተጽዕኖ ያስከተለ የጋብቻ ወይም የገንዘብ ችግር እንዳለ ይመረ ምራል ። ከሌሎች ጋር ግጭት አጋጥሞ ከሆነም ይጠይቃል ። ርኩስ መንፈስ ጣልቃ ገብቶ በቤተሰብ ውስጥ መቃቃር ተከስቶ እንደሆነም ያጣራል ። በመኖርያ ቤቱ ካነጋገርሁት በኋላ ሲያሰናብተኝ “ዜናውን ስትጽፍ ታዲያ አጋንንት በመሳብ ሳይሆን ቅዱስ መንፈስን በመማ ፀን ሰይጣናዊ ልክፍትን እንደምዋጋ ግለጽ” አለኝ ።

በቅኝ ግዛት ዘመን እንደ ሳታጊ ያሉ የባህል መድኃኒት አዋቂ ዎች በገገርዎች ይታሰሩ ነበር ። ኋላቀርና ፀረ—ክርስትና ሆነው ስለ ታዩ በዘመናዊው አፍሪካ ቦታ የማይኖራቸው ተደርገው ተወስደው ነበር ። ዛሬ ይህ አመለካከት ተቀይሯል ። የዓለም ጤና ድርጅት በጤና ጥያቄ ላይ ሥርነቀል ለውጥ ለማድረግ እየሞከረ ነው ። ስለጤናም ሲገ ልጥ የአካላዊ ፣ የአእምሮአዊና የማህበራዊ ደህንነት ድምር ውጤት እንጅ የበሽታ አለመኖር ብቻ እንዳልሆነ ያስገነዝባል ። ይህን ለመቀ ዳጀት ደግሞ የአፍሪካ ትኩረት በመሠረተ ጤና ሊሆን ይገባል ። ንፁሕ የመጠጥ ውሃ ፣ ንፅሕና ፣ የተሻለ የወሊድ ቁጥጥር ፕሮግራም፣ የተመጣጠነ ምግብና በቂ የምግብ አቅርቦትን ማሳደግ ለአፍሪካ መድ ኃኒትና ዶክተር ከማግበስበስ የተሻለ ውጤት የሚያስገኙ ጠቃሚ ጉዳዮች ናቸው ። በኬንያ በ1970ዎቹ መጨረሻ እንደተቋቋመው የልብ ቀዶ ሕክምና ዓይነት አገልግሎት ለተከታዩ አሥር ዓመት ሊቆይ የሚችል ነው ። አፍሪካ የገጠሩን ብዙኃን ሕዝብ ችላ ብላ በከተ ሞች ልታተኩርም አይገባትም ።



ይህን ሁሉ በመገንዘብ የዓለም ጤና ድርጅትም በአሁኑ ጊዜ የዘመናዊና የባህል ሕክምና ተደጋግፈው እንዲጓዙና ተጨማሪ ጥናት እንዲካሄድ ሀሳብ በማቅረብ በመድኃኒት እፅዋትና በመተታዊ ወይም ሃይማኖታዊ መድኃኒቶች ላይ ምርምር እንዲስፋፋ አሳስቧል ። የባ ህል መድኃኒት አዋቂዎች ማህበር በይፋ እንዲቋቋምም አስፈላጊነ ቱን ጠቁሟል ። ከዚሁ ጋር የሕዝቡን አመለካከት በትምህርት ማጎል መ ስም ዓቢይ ጉዳይ ነው ።

አፍሪካውያን የዱቄት ወተት ለልጆቻቸው በተገቢው ጥንቃቄ ለመበጥበጥም ሆነ ሌላ መድኃኒት አወሳሰዱን በዝርዝር ተረድተው ለመጠቀም አንብቦ የመረዳት ችግር አለባቸው ።

የሰለጠነው ዓለም የመድኃኒት ኩባንያዎችም ስለጉዳዩ ባለመጨ ነቅ በማጭበርበሪያ ማስታወቂያዎች አህጉሪቱን ጊዜ ያለፈባቸው የማይረቡ መድኃኒቶች ሸቀጥ መጣያ አድርገዋታል ። በፊልምና በየ መንገዱ በተሰቀሉ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች መድኃኒቶቹ ሊያስገኙ ከሚችሉት ውጤት በላይ እያጋነኑ በማቅረብ “ . . . ወጣት ያደር ጋሉ ፣ ወሲባዊ አቅምን ይጨምራሉ ፣ አእምሮን ሳይቀር ብሩህ ያደር ጋሉ ፣ ”እያሉ በማስተጋባት ያሻሽጣሉ ። አብዛኛዎቹ ማስታወቂያዎች የለየላቸው ውሸቶች ሲሆኑ በአሜሪካ ቢሆን ሊለጠፉ አይፈቀድላ ቸውም ። በአፍሪካ ግን የሸማቹን መብት የሚያስጠብቅ ሕግና የው ሸት ማስታወቂያዎች ማገጃ ደንቦች ስለሌሉ በዚህ ቀዳዳ በመሹለክ የመድኃኒት ኩባንያዎች ሕዝቡን የኪኒን ጎተራ ያደርጉታል ። በአፈ ጮሌ አሻሻጮች መንታ ምላስ እየቀባጠሩ በአውሮፓና በአሜሪካ የተከ ለከሉ አንዳንድ መድኃኒቶችን ሳይቀር ለአፍሪካ ይቸበችባሉ ። ለምሳሌ አሚኖፒሪንና ኢፒሮን የተሰኙ የሕመም ማስታገሻዎች ሌላ ሕመም ስለሚያስከትሉ በአሜሪካና በእንግሊዝ ገበያዎች ከተከለከሉ ቆይተ ዋል ።

የበለፀጉ አገሮች ለአፍሪካውያን ጤና መጠበቅ በሚሊዮን የሚ ቆጠር ገንዘብ ቢረዱም ችግሩ ብዙም አልተቃለለም ። ምክንያቱም የሚያስፈልጋት መሠረታዊ የጤና እንክብካቤ ሥልት ሆኖ ሳለ እነሱ የሚረዱዋት ግን የተራቀቀ የሕክምና መሣሪያ ብቻ ነው ። አፍሪካን

በኢኮኖሚ እንድትገፋ ከተፈለገ አስቀድሞ ጤናማ ሕዝብ ለማድረግ መጣር ያሻል ። ችግሩ በአመዛኙ የሚወገደው በማከም ሳይሆን በማስተማር ነው ። ከመንደር መንደር እየተዘዋወሩ ማስተማር ። አሁን እንደሚታየው ብዙ የአፍሪካ አገሮች በገጠር የመሠረተ ጤና ትምህትና ክሊኒኮችን በማስፋፋት መልካም ጅምር ይዘዋል ።

ነገር ግን አፍሪካ ይህን ተግባር ብቻዋን ልትወጣ አትችልም ። አፍሪካን በባርነት የጨቆኑ ፣ በቅኝ አገዛዝ የማዕድን ሀብቷን የመዘበሩ ፣ እርስ በርስ እንድትተላለቅ ጦር መሣሪያ ያቀበሉ ፣ አንድ ሀኪም ሳያሰለጥኑላት መዝብረዋት የተመለሱ ሁሉም ከጤና ችግሮቿ ለመውጣት የሚያስፈልጋትን የገንዘብና የሰው ኃይል የመርዳት የሞራል ግዴታ አለባቸው ። በአንድ አልጋ ሁለት ሰዎች ተኝተው እየታከሙ ለፕሬዚዳንቱ ጉራ አውሮፕላን ጣቢያ ከመገንባት ፣ ጠመንጃ ከማቀበል ፣ ሌላም ለስም የሚሆን የተንዛዛ ፕሮጀክት ከማቋቋም ፣ ምናለበት ምሥራቁም ፣ ምዕራቡም የአፍሪካውያንን የደቀቀ አካልና መንፈስ ለማዳን በበሽታዋ ላይ ያተኮረ ጦርነት ቢያካሂዱላት? የጅል አስተሳሰብ ባይመስልብኝ ውጤቱ ግን ምንኛ ባማረ!



## ምዕራፍ አሥራ አራት

# የገንዘቡ የመግዛት አቅም

"ነፃ ሆነን ለመኖር ፣ ከአፍሪካ ተዝቆ የማያልቅ ቅምጥ ሀብት ሙሉ ጥቅሙን በማግኘት ለመደሰት ከፈለግን ለሁሉም ሕዝቦች የጋራ ብልጽግና የሰውና የማቴሪያል ሀብታችንን በተሟላ ጥቅም ላይ ለማዋል መተባበር አለብን ።"

—ክዋሜ ንክሩማ
የጋና ፕሬዚዳንት(1957—1966)

ከለንደን የተከራዩት ጄት አውሮፕላን በውድቅት ሌሊት ጋና ደረሰና ኮቶኮ ኢንተርናሽናል አውሮፕላን ጣቢያ በማረፍ እያዘገመ ወደ መቆሚያው ተጠጋ ። በጣቢያው ምንም መንገደኛ የለም ፣ ሁሉም ነገር ፀጥ ብሏል ። የታጠቁ በርካታ ወታደሮች ወደ ቦይንግ 707 አውሮፕላኑ ተጠጉ ። አውሮፕላኑ እንደመጣ በአቅራቢያ ወደምትገኘው የጋና ዋና ከተማ አክራ መልእክት ተላለፈ ። ወዲያውም የመንግሥቱ ሬዲዮ ጣቢያ የአየር ማረፊያው ፣ ወደቦችና ድንበሮች ሁሉ ሌላ መግለጫ እስኪሰጥ ላልተወሰነ ጊዜ መዘጋታቸውን አወጀ ።

ሌላ መፈንቅለ መንግሥት መሆኑ ነው?ወይስ የአገሪቱ መሪ በምስጢር ወደ ውጭ ሄዶ ቆይቶ መመለሱ ነው? አይደለም ። ጋና በዚያ ሰሞን የገንዘብ ኖቶቿን መለወጧ ነበር ። ሴዲ በሚል ስያሜ የሚታወቀው ገንዘብዋ የመግዛት አቅሙ ተዳክሞ ዋጋ ስላጣ ሰሞኑን ተሰብስቦ ከሥራ ይታገዳል ፣ ይቃጠላል ። በአውሮፕላኑ ውስጥ አዲሱ ሴዲስ የሚል ስያሜ የተሰጠው ገንዘብ ያኛውን ለመተካት ተጭኖ

መጥቷል ። 690,000,000 ዶላር ዋጋ ያለው አዲስ የገንዘብ ኖትና ሳንቲም ነው ።

ከኢትዮጵያ ብር አንስቶ እስከ አንጎላ ክዋንዛ በጥቁር አፍሪካ በዋጋዎች ንረት ፣ በአስተዳደር ጉድለት ፣ በገቢ ሸቀጦች ዋጋ ማሻቀብ ፣ ለውጭ ገበያ በሚቀርቡ ምርቶች ዋጋ ውጣ ውረድ ምክንያት የገንዘቡ የመግዛት አቅም ተዳክሟል ። የብዙዎቹ ሀገር ገንዘብ እንደትናንት ጋዜጣ ዋጋ አጥቷል ። ሌላ ጎረቤት አገርም አይቀበለውም ፣ በውጭ ባንክም ተቀባይነት የሌለውና ሊመነዘር የማይችል ነው ። የገንዘቡ ልዩነት ራሱ የአፍሪካ አገሮችን በኤኮኖሚና በማህበራዊም ልክ በፈንጅ እንደታጠረ ድንበር ለያይቷቸው ይገኛል ።

በአፍሪካ የገንዘቡ የመገብየት ችሎታ ሲዳከም የሚወሰደው ርምጃ ተጨማሪ ገንዘብ ማተም ነው ። ናይጀሪያ ከ1975 እስከ 1977 ብቻ የገንዘብ ሥርጭትዋን በ180% ጨምራለች ። ጋና ደግሞ በ1976 ብቻ የገንዘብ ኖቷን 80% ጨምራለች ። እንዲሁም ከ1965 እስከ 1979 የገንዘቡን ዋጋ ሰባት ጊዜ ቀንሳለች ። የኡጋንዳ የገንዘብ ሚኒስትር በአንድ ወቅት ለፕሬዚዳንት አሚን የገንዘብ እጥረት እንዳጋጠመ ሲነግሯቸው ። "መልካም ፣ ተጨማሪ አሳትሙ!" አሉት ።

ተጨማሪ ገንዘብ እየታተመ በአሉት ጥቂት ምርቶች ላይ ሁሉም ሲረባረብ የባሰውን ገንዘቡ ዋጋ እያጣ የዋጋ ግሽበት እያሻቀበ ይሄዳል ። ኡጋንዳና ዛየርን በመሳሰሉ አገሮች የዋጋ ግሽበት ከ100% ይበልጣል ። የኑሮ ውድነት እየከፋ ሲሄድም የወር ደመወዝና የዕቃወች ዋጋ ግንኙነት ይናጋል ። ድሃው የበለጠ ድሃ ይሆናል ። በጋና የምግብ ዋጋ ከ1963 እስከ 1977 ሃያ ሶስት እጅ አድጓል ። በ1981 አንድ የመኪና ጐማ ዋጋ 360 ዶላር ደረሰ ፣ የጥርስ ሳሙና ስድስት ዶላር ተኩል ሆነ ። በዛየር የታይም መጽሔት ዋጋ አሥር ዶላር ደረሰ፣ የዳቦ ዋጋም ወደ ሁለት ዶላር አደገ ። በዛምቢያ አንድ ወዛደር መጥበሻ ለመግዛት የሳምንት ክፍያውን ማውጣት አለበት ። የጋና የቀን ሠራተኛ በቀን አንድ ዶላር ተኩል የሚከፈለው ሲሆን ፣ ለቤተሰቡ መጠነኛ ምሳ ለማብላት ግን አሥራ አንድ ዶላር ማውጣት ይኖርበታል ።



"ሕዝቡ እንዴት እንደሚኖር አይገባኝም?" አሉ የጋና ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ያው ሳፉ ። በቤታቸው ውስጥ ተቀምጠን ሳለን ቡና መጋበዝ እንደማይችሉ ገልጠውልኝ ውሃ በብርጭቆ አቀበሉኝና "ሕዝቡ በችግር ነው የሚኖረው ፣ በቀን አንድ ጊዜ ብቻ ነው የሚበላው ፣ የተጠላ ሥራ ነው የሚያገኙት ፣ ልጆቻቸው ወተት የሚያገኙት ከስንት አንድ ቀን ነው ። ቅዳሚና እሁድ ወደ እርሻ ልማቶች ይሄዱና ሙዝ በመሰብሰብ ገንዘብ ያገኛሉ ። አንዳንዶቹ ወደ ምርት ልውውጥ ደረጃ ወርደዋል ። እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት መሠረታዊ ሸቀጦች በቀር ሌላ መግዛት አቁመዋል ።

"በሸቀጥ መደብሮች ምንም ነገር የለም ። አንድ የቅንጦት ሸቀጥ ሲመጣም እጅግ ውድ ከመሆኑ የተነሳ መግዛት አይቻልም ። በኪሴ ያለው ገንዘብ ምንም ትርጉም የለውም ፣ ምክንያቱም ምንም ሊሸምት አይችልም" በማለት አማረው ነገሩኝ ።

በሕይወት ለመቆየት አንዱ ዘዴ አለማባከን ነው ። አፍሪካውያን ሁሉንም ነገር በጥንቃቄ ይጠቀሙበታል ። የተጣሉ ፣ በሰም የተለበዱ የወተት መያዣዎች ለማገዶ ማቀጣጠያነት ይውላሉ ። ፌስታሎች ሲቆሸሹ እየታጠቡ ለረጅም ጊዜ ያገለግላሉ ። አሮጌ ጎማዎች ሰንደል ነጠላ ጫማ ይሠራባቸዋል ። ባዶ ጠርሙሶች ይሸጣሉ ። ጋዜጦች ለመጠቅለያ ያገለግላሉ ። ልብሶች ሲቀደዱ እየተጣፉ እስኪቦጫጨቁ ይለበሳሉ ። ማጠቢያ ስፖንጆችን እስኪበጣጠሱ ይጠቀሙባቸዋል ። የቆርቆሮ ጣሳዎች ለመኪና አካል መበየጃ እንደ ላሜራ ያገለግላሉ ። የሰው ዓይነምድር ለማዳበሪያነት ይውላል ። የቁምሳጥን ስብርባሪዎች ለድሆች ቤቶች ግድግዳ ይሆናሉ ። በብዙ አገሮች ባዶ ጠርሙስ ካላመጣህ ከግሮሰሪ ቢራ መግዛት አትችልም ።

በበለፀጉትም ሆነ ባልበለፀጉት ሀገሮች የአንድ አገር ገንዘብ የመግዛት ኃይል የሚለካው የአገሩ ኤኮኖሚ ዕቃዎች ለማምረትና አገልግሎት ለማሟላት ባለው አቅም ነው ። የደቡብ አፍሪካ ራንድ ጠንካራ ሆኖ የኖረው የአገሪቱ ኢኮኖሚ አዳጊ በመሆኑ ነው ። ላይቤሪያም የአሜሪካን ዶላር ስለምትጠቀም ድጋፍ ጨብጣለች ። በአፍሪካ ግን የገንዘብ ሥርጭት በጨመረ ቁጥር ምርቱ እየቀነሰ በ1970

ዎቹ በሃያ አገሮች የነፍስ ወከፍ ዕቢም እንዳቆለቆለ የዓለም ባንክ ዘገባ ይጠቁማል ። ገንዘቡ በላዩ ላይ የተፃፈውን ቁጥር ያህል የሚመጥን የመግዛት አቅም እንዲኖረው ወርቅ ካላስያዙ ፣ ወይም ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባለው ገንዘብ ዋስትና ካላሰጡት ፣ ያለዚያም ዕቃዎችን በማምረትና አገልግሎትን በማሟላት ችሎታ ካልተደገፈ የአፍሪካ ገንዘብ የመግዛት አቅም አጥቶ የፖስታ ቴምብር ሆኖ መቅረቱ ነው።

የአፍሪካ አገሮች ነፃ ሲወጡ በቅኝ ገዢዎች ገንዘብ መጠቀም ለምደው ነበር ። በእንግሊዝ ፓውንድ ፣ በፈረንሳይ ፍራንክ ፣ በፖርቱጊዝ ኤስኩዶ ፣ በቤልጅግ ፍራንክ ይጠቀሙ ነበር ። እያደር ከሩይናንሱ ተጨባጭ ጥቅም ይልቅ ብሔራዊ ስሜት እያየለ በመሄዱ አገሮች አንድ በአንድ የአውሮፓ ድጋፍ ያለውን ገንዘብ እየተው ከአገር ውጭ ዋጋ የማያወጣና የማይመነዘር የየራሳቸውን የገንዘብ ዓይነት ፈጠሩ። በቦትስዋና ፑላ ፣ በጋምቢያ ዳላሲ ። በኢኳቶሪያል ጊኒ ኤኩሌ ፣ በስዋዚላንድ ሊላንጌኒ ፣ በናይጀርያ ናይራ ፣ በሞሪታንያ አውጉያ ፣ በዛየር ዛየሬ ፣ የተባሉት ተፈጠሩ ። ሌላ ጥቅም ባይኖረውም አዲሶቹ ፕሬዚዳንቶች ፎቶግራፋቸውን መለጠፊያ አገኙ ። ነገር ግን ብዙዎቹ እየተገለበጡ ሌላ የወረቀት ገንዘብ ይለወጥና ደግሞ የአዲሱ መሪ ፎቶግራፍ ይሳልበታል ።

ከዚያም የማይቀረውና ለኤኮኖሚ መረጋጋት ጤና የሚያውከው ጥቁር ገበያ መጣ ። የዕቃዎች የዋጋ መጋሸብ ለአገር ቤቱ ገንዘብ ሰው ሰራሽ ኤኮኖሚ ፈጠረ ። እውነተኛው ኤኮኖሚ በሕገወጥ የውጭ ምንዛሪ ልውውጥና በኮንትሮባንድ ላይ ተመሠረተ ። ወደዚህ ኢኮኖሚ ለመግባትም ዶላር ወይም ፓውንድ መለወጥ አስፈላጊ ሆነ ። ስለዚህም አብዛኛው አፍሪካዊ በጋሸበው ኤኮኖሚ ውስጥ በችጋር መኖር ሲገደድ አቅም ያለው ግን ሕጋዊ ባልሆነ ጥቁር ገበያ እየመነዘረ ያስኬደው ጀመር ።

እነዚህ የገንዘብ ገቢያዎች በምዕራብ አፍሪካ በሊባኒዞች ፣ በምሥራቅ አፍሪካ በሕንዶች ፣ ቁጥጥር የሚካሄዱ ሲሆኑ ፣ እነዚህ ከበርቴዎች ብዙውን ጊዜ በአካባቢው አገሮች ሕጋዊ ንግድ ያላቸውና አየር ባየር ንግድም የሚያካሔዱ ናቸው ። የአገሬውን ገንዘብ በርካሽ ዋጋ



ወደ ዶላር ወይም ፓውንድ ይለውጡና ወደ አውሮፓ ባንኮች በድብቅ ያሻግሩታል ።

ለምሳሌ የኡጋንዳን ሁኔታ እንመልከት ። በ1980 ያልተዋጣላትን ኤኮኖሚዋን እንዲያገግም ለመርዳት የዓለም የገንዘብ ድርጅት የኡጋንዳ ገንዘብ ዋጋ እንዲቀንስ አዘዘ ። በሕጋዊ ምንዛሪ የኡጋንዳ ሰባት ሺልንግ አንድ ዶላር ሆነ ። ነገር ግን የጥቁር ገበያ ነጋዴዎች ለአንዱ ዶላር 140 ሺልንግ ይሰጡሃል ። ባንኩ ከሚመነዝርልህ ሃያ ጊዜ የበለጠ ማለት ነው ። በዚያ ሰሞን የካምፓላ ኢንተርናሽናል ሆቴል ለመኝታ የሚያስከፍለው 1,000 ሺልንግ ነበረ ። አንተ ሺልንጎች ብቻ ያሉህ አፍሪካዊ ብትሆን የመኝታው ክፍል ኪራይ 140 ዶላር መሆኑ ነው ። ግን ዶላሩ ኖሮህ በጥቁር ገበያ መንዝረህ ብትከፍል ግን ዋጋው ሰባት ዶላር ብቻ ይሆናል ማለት ነው ። በዚህ መልክ እነዚህ ሁለት ገንዘቦች ፊትና ኋላ ናቸው ። የታደለውና ዶላር ሊያገኝ የቻለው ከሕንዶች አስመጭና ላኪዎች ብዙ ሺልንግ እየለወጠ በርካሽ ይምነሸነሻል። ያልታደለው ብዙኃን ጭቁን ሲማቅቅ ይኖራል ።

የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት በጣም ችግር ስለሆነ እንደ ታንዛንያና ጋና ባሉት አገሮች ለትልልቅ ሆቴሎች የሚከፈለው በውጭ ምንዛሪ ብቻ ነው ። የኬንያ አየር መንገድ ቲኬት የሚሸጠው በውጭ ምንዛሪ ነው ። በአንዳንድ አገሮች ከአገር የሚወጡ መንገደኞች የኮቴ በዶላር እንዲከፍሉ ይገደዳሉ ። በብዙ የአፍሪካ አገሮች የአየር መንገድ ቲኬቶች የሚሸጡት በዶላር ብቻ ነው ።

የአፍሪካ አስቂኝ ገንዘብ የአህጉሩን ኢኮኖሚ ሁኔታ ያመለክታል። የአፍሪካ ብዙኃን ኑሮ እያሽቆለቆለ የቢሮክራቱ ኑሮ እየለመለመ ነው ። በአፍሪካ የነፍስ ወከፍ ገቢ በአማካይ 365 ዶላር ወይም በቀን አንድ ዶላር ሲሆን ፣ ዛሬ በአንዲት ዶላር የሚገዛው ከአሥር ዓመት በፊት ከነበረው በብዙ ያነሰ ነው ። የምግብ አቅርቦት ተዳክሟል ፣ የእርሻ ምርት አዘቅዝቋል ፣ የወሊድ ብዛት ግን በእጥፍ ድርብ ጨምሯል ። በዛምቢያ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከ1970 ወዲህ 14% ሲቀንስ ፣ ወደ ውጭ የሚላከው 25% ወርዷል ፣ የሸቀጦች ዋጋ ደግሞ 70% አድጓል ። ወደ ትራክተር ሳይሆን በበሬ ወደማረስ ደረጃ ዝቅ ማለት ያለ

ባቸው ሁኔታ ላይ ደርሰዋል ፡፡ ይህን ማድረግ እንደሚሻል የፈረንሳይ የእርሻ ምሁር ሬኔ ዱምንት ቢያስገነዝቡም አውሮፓውያን ወደ ኋላ ሊመልሱን ይሻሉ በሚል አልተቀበሏቸውም ፡፡

የአፍሪካውያን ስሜት ከችግራቸው ጋር ተጣጥሞ አይራመድም፡፡ ባርያ ንግድና ቅኝ ግዛት የተወው ጠባሳ ጥልቅ ስለሆነ ነጮችን በጥርጣሬ ይመለከቷቸዋል ፡፡ ያለፈው ኋላቀርነት ደግሞ ስለሚሰማቸው አፍሪካውያን ምንም ውጤት ይምጣ ምን በሚፈጥሩት ስህተት እየተደሰቱ በእውር ዳበሳ ዓይነት ወደፊት መቀጠሉን ይመርጣሉ ፡፡

ሕዝቡ በኢኮኖሚው ሁኔታ የበለጠ በተማረረ ቁጥር የአፍሪካ መሪዎች ሥልጣናቸውን ለመጠበቅ ማህበራዊ ቁጥጥሩን የበለጠ ያጠብቃሉ ፡፡ የአገሪቱ ብሔራዊ የብድር ዕዳ በበዛ መጠን የበለጠ የውጭ መንግሥታት ጥገኛ ይሆናሉ ፡፡ የየዓመቱ ብድርም ለሕዝቡ ኑሮ መሻሻል ከመርዳቱ ይበልጥ መንግሥትን በሥልጣን ለማቆየት የሚያግዝ ነው ፡፡ ይህም አጥፊ ሂደት እድገት የማያስገኝና እዚያው ሞላ እዚያው ፈላ ዓይነት ሆኖ አዲስ ጠቃሚ ሀሳብና ጥልቅ እውቀት ያላቸው መሪዎችና ባለሥልጣኖች በውድድር እየላቁ ወደ ሥልጣን በመውጣት አገሪቱንና ሕዝቡን ወደ ተሻለ እድገት እንዳይመሩት አሥሮ የያዘ ነው ፡፡ በዚህም የተነሳ የአፍሪካ አዲስ ትውልድ ወጣት ምሁራን በአገሪቱ የሚጫወቱት ሚና ኢምንት ሆኖ እንዲቀርና እነሱም በብስጭትና በጭንቀት እንዲባዝኑ ተደርገዋል ፡፡ የላይቤሪያ ከፍተኛ የፋይናንስ አማካሪ የነበረው ለሃምሳ አለቃ ሳሙኤል ዶ ፡ ስለዋጋዎች መጨመር ምክንያት ሲያብራሩላቸው ሊገባቸው ስላልቻለ የሚያሻጥርባቸው መስሏቸው ሲያገሉት ወደ አሜሪካ ተሰደደ ፡፡

አንዳንድ የአፍሪካ አገሮች ድህነታቸው ሥር የሰደደ በመሆኑ ያለርዳታ መኖር የሚችሉ አይመስልም ፡፡ በዚህ ከፍተኛ ቅምጥ ሀብት ባለው አህጉር ከዓለም ታላላቅ ማዕድናት ሰላሳ በመቶ በከርሰ ምድሩ እያሉ እንዴት እንዲህ ኢኮኖሚያቸው የተንኮታኮቱ ለማኝ ሀገሮች የተሰበሰቡበት ምድር ሆነ! መልሱ በቅኝ ግዛት ውርስና ከነፃነት በኋላ በተከተሉት ባህርይ ላይ የተመሠረተ ነው ፡፡

አውሮፓውያን አህጉሩን በቅኝ ግዛትነት ይዘው ያስተዳድሩት



በነበረ ጊዜ የአፍሪካ ገበሬዎች ለአውሮፓ ፍላጎት መሟላት ሲባል ወደ ውጭ የሚላክ ሰብል እንዲያመርቱ ይገደዱ ነበር ፡፡ ይህም የቅኝ ግዛት ወጪያቸውን ለመሸፈንና ለአውሮፓ የሚያስፈልገውን ለማቅረብ ሲባል የሚካሄድ ነበር ፡፡ የቅኝ ግዛት ኢኮኖሚና በኋላም ነፃ የወጡት ሀገሮች ኢኮኖሚ ሆኖ የቀጠለው በአንድ ዓይነት ምርት ላይ ብቻ የተመሠረተ ነበር ፡፡ ይህም የተለያዩ አማራጭ ምርቶችን በማፍራት የአንዱ ዋጋ ቢያዘቀዝቅ በአንዱ ለመመርኮዝ የሚያስችል አልነበረም ፡፡ እያንዳንዱ አገር በአንዲት የምርት ዓይነት ላይ ብቻ በመመካት እንቁላሏን በአንድ ቅርጫት ውስጥ እንዳስቀመጠች እመቤት ሆኑ ፡፡ አደጋ ቢከሰትና ድርቅ ወይም ውርጭ ቢመታው ወይም የአስተዳደር ጉድለት ቢከሰት በጫፍ ላይ ያለው ኢኮኖሚ ይንኮታኮታል ፡፡

ለኬንያ የውጭ ምንዛሪ ማስገኛ ምርቷ ቡናና ሻይ ነው ፡፡ የአንድ የምርት ወራት የአየር ጠባይ ሲናጋ አጨብጭባ ባዶ እጅዋን ትቀራለች ፡፡ በዓለም ገበያ ዋጋው ቢወድቅም እንዲሁ ነው ፡፡ በናይጀርያ የመንግሥት 85% የገቢ ምንጭ ነዳጅ ዘይት ነው ፡፡ ዛምቢያ 96% ገቢዋ የተመሠረተው በመዳብና በኮባልት ማዕድናት ነው ፡፡ ጊኒ ቢሳው ከቦለቄ በስተቀር ይህን ያህል የሚያስመካ ሌላ ምርት የላትም ፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች አፍሪካ በዓለም የኢኮኖሚ ቀውስ ሲከሰት በሁለት በኩል ትጎዳለች ፡፡ አንድም በሌሎች ቁጥጥር ሥር ያለው የምርቶችዋ ገበያ ዋጋ ሲወድቅ ፣ ሌላው ደግሞ የምታስመጣቸው ሸቀጦች ፣ መለዋወጫዎች ፣ ነዳጅ ፣ ወዘተ ዋጋ ሲንር ችግሯ ይባባሳል ፡፡ ምዕራባውያን ብዙ ዓይነት ምርት ስላላቸው የዕቃዎቻቸውን ዋጋ በመጨመር የሚያጋጥማቸውን የዋጋ ግሽበት ያጣጣሉ ፡፡ አፍሪካ ግን እንዲህ ለማድረግ የተመቻቸ ኢኮኖሚ የላትም ፡፡ አፍሪካ እየደኸየች የምትሄድ ናት ፡፡ በ1970 ነዳጅ ለማስመጣት ከገቢዋ 10% ከፈለች ፣ በ1980 ይህ ወጭ ወደ 22% አደገ ፡፡ ኡጋንዳ በዓመት ከቡና የምታገኘውን 10,000,000 ዶላር ገቢ በሙሉ ነዳጅ ለመግዛ ታውለዋለች ፡፡ ታንዛንያ ነዳጅ ግዢዋን ወደ 700,000 ቶንስ ብትቀንስም የነዳጅ ዋጋ በመጨመሩ ምክንያት ዛሬ የምትከፍለው ግን ከ1970ዎቹ በአስር እጅ የላቀ ነው ፡፡ በዚህ ሁኔታ ብሔራዊ ልማት ዋጋ ቢስ ይሆ

ናል ። የሚጣጣሩት ለመኖር ኅያህል ብቻ ይሆናል ። አፍሪካ ልትገዛ ስትፈልግ ልክ በየዓመቱ ደመወዙ እንደሚቀነስበት ሰው የመግዛት አቅምዋ የተዳከመ ሆና ታገኘዋለች ።

ለዚህ ሁኔታ ጥሩ ምሳሌ ጋና ናት ። የጥቁር አፍሪካ የእድገት ሕልም በዚያች ሀገር ተወለደና በዚያው አገር ተቀበረ ። ለዚህ ችግር ጊዜያዊ ምክንያት የአገሪቱ ስግብግብና ጅል ወታደራዊ መሪዎች የተበላሸ አመራር ለአሥር ዓመታት ስለአመሰቃቀላት ነው ። የተማሩና ኩሩ ፣ ከሕዝብ መግባባት የሚችሉ የጋና ሕዝቦች ዛሬ አገራቸው የወደቀችበትን አዘቅት ሲያስተውሉ በመገረም ራሳቸውን ይነቀንቃሉ። ይህ የተጕሳቆለና ሞራሉ የደቀቀ አገር አንድ ቀን ተመልሶ ቀድሞ "የአፍሪካ ኮከብ "እንደተባለው ሊሆን ይችላል? በማለት ይጠይቃሉ። በ1957 ጋና ነፃ ስትወጣ የመጀመሪያዋ ጥቁር አፍሪካዊት አገር ነበረች ። ያን ጊዜ ጕልድ ኮስት የሚል ስያሜ የሰጧት በባርያ ንግድ ገንዘብ ያካበቱ ነጋዴዎች እንጅ ብዙ ወርቅ ኖሯት አይደለም ።

የጋና ወታደራዊ አምባገነን መሪዎች የሀገሪቱን ሀብት በመቀራመትና በአውሮፓ ባንኮች በማካበት ያለርህራሄ አሟጠጡት ። የሚያስቡት ለሀገሪቱ እድገት ሳይሆን ከአገሪቱ ገቢ ቆርጠው የባንክ ሂሳባቸውን ለማሳደግ ነበር ። በዚህም ምክንያት የትራንስፖርት ሥርዓቷ ተንኮታኩተ ፣ የሸቀጥ መደብሮቿ መደርደሪያዎች ባዶ ቀሩ ፣ ሕጋዊው ኢኮኖሚ በጥቁር ገበያ ተተካና ማጭበርበርና ኮንትሮባንድ ተንሰራፉ ። ከሃያ ዓመት በፊት የጋና ሕዝቦች የሚያወሩት ውጤት ለመጨበጥ ስለመቻላቸው ነበር ፣ ዛሬ ግን የሚወያዩት ችግሩን ተቋቁመው ለመኖር ስለመቻላቸው ሆኗል ።

የጋና የኢኮኖሚ መንኮታኮት የተፈጥሮ ሀብት የሌላት ሆና አይደለም ። የካካዋ ሽያጭዋ በዓመት አንድ ቢሊዮን ዶላር ነው ። የእርሻ መሬቷ ለም ነው ። ወንዞቿ ዓሣ የሞላባቸው ናቸው ። ሜካማው የመሀል አገሩ ክፍል አልማዝ ፣ ወርቅ ፣ ቦክሳይትና ማንጋኒዝ ማዕድናትን ያዘለ ነው ።

በ1970ዎቹ መጨረሻ ጋና ዋና ዋና ማንቀሳቀሻ ዕቃዎቹ በሌቦች እንደወላለቀ መኪና ተሰነካክላ ተራቆተች ። ብዙ ዜጎችዋ



ወደ አካባቢው አገሮች ኮበለሉ ። በየቀኑ ሃምሳ የሚደርሱ የጋና ተማሪዎች ቪዛ ለመጠየቅ አሜሪካን ኤምባሲ በር ፊትለፊት ይሰለፋሉ ። ግማሾቹ የተጭበረበረ የትምህርት መረጃ በማቅረብ ቢከለከሉም በ1979 ብቻ 2000 የጋና ዜጎች በአሜሪካን ዩኒቨርሲቲዎች ለመማር ወደ ዩናይትድ እስቴትስ ተጓዙ ። 828 የሚሆኑት ደግሞ ለትምህርት ሳልሆን ዓላማ ወደዚያው ሄዱ ። ታዲያ በዋሽንግተን ታክሲ እየተከራያችሁ ስትዘዋወሩ ብትውሉ የምታገኟቸው ታክሲ ነጂዎች አብዛኛዎቹ ፣ ከጋና ፣ ከናይጀሪያ ፣ ወይም ከኢትዮጵያ እንደሚሆኑ አያጠያይቅም ።

ፕሬዚዳንት ክዋሜ ንክሩማ ብዙ ቃል የገቡላት ጋና እንዲያ ሆና መቅረቷ በጣም የሚያሳዝን ነው ። ንክሩማ ደከመኝ የማይሉ፣ ጥሩ ሃሶቦች የሚያመነጩ ጀግና መሪ ነበሩ ። በ1930ዎቹና በ1940ዎቹ በአሜሪካ ሲማሩና ሲዘዋወሩ ከቆዩ በኋላ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲያበቃ በጻፉት ፣ "የነፃነት ሐውልት እጅዋን ከፍ አድርጋ መልካም መንገድ ስትለኝ አየሁ ። እኔም በሀሳቤ ስለነፃነት እውነተኛ ትርጉም ዓይኔን ከፍተሽልኛል አልኳት ። መልዕክትሽን ለአፍሪካ ሳላደርስ እረፍት አይኖረኝም" በማለት አሰፈሩ ። እንዳሉትም አደረጉ ። "የራስ አስተዳደር አሁን" በሚል መፈክር ቢጋና ሕዝቡን በመቀስቀስ ብሔራዊ ጀግና ሆኑ ። ወዲያው ሕዝብን አነሳሳ በሚል በእንግሊዞች ታሰሩ ። በኋላም ተፈቱና እንደ ኔህሩና እንዲያውም እንደዘመናችን ሙሴ ተቆጥረው ትልቅ አድናቆትን አተረፉ ። መልከመልካምና ተስሚነት ያላቸው ስለነበሩ ሕዝባቸው እሳቸውን ተከትሎ የአፍሪካን የፖለቲካ እድገት መራ ። አስተሳሰባቸው ለነፃነት እንቅስቃሴዎችም ሆነ ለዜጐች መብቶች ትግል የሚያግዝ በመሆን በአፍሪካ አህጉርና ከዚያም አልፎ በአሜሪካ ሳይቀር ተቀባይነት ነበረው ።

ንክሩማ ራሳቸውን እንደ ለውጥ ሐዋርያ በመቁጠር ጥቁር ሕዝቦች በእርሻ ብቻ ከመተማመን ወጥተው ኢንዱስትሪዎችን በማስፋፋት ያለቀላቸው የፋብሪካ ምርቶችን ማቅረብ እስካልቻሉ ድረስ ከአገልጋይነት አይወጡም ብለው ያምኑ ነበር ። ንክሩማ በመጀመሪያ ጋናን የለወጡ ብዙ መልካም ሥራዎች ቢያካሂዱም በኋላ ግን ከአፍሪካ የብልጽግናና ነፃነት ሞዴልነት ወደ ድህነትና ጭቆና ምሳሌነት አወረዷት ።

ንክሩማ ለራሳቸውና ለሀገራቸው ክብር በሚል ብዙ የብድር ገንዘብ ያለአግባብ ለቅንጦት ፕሮጀክቶች አዋሉ ። የአፍሪካ አንድነት

ድርጅትን ጉባኤ ለማስተናገድ ለጉባኤ አዳራሽ ማሠሪያ 16,000,000 ዶላር አዋሉ ። ውሱን አገልግሎት ላለው አጭር አውራ ጐዳና ማሰሪያ ለጉራ ሲሉ 9,000,000 ዶላር አወጡ ። ለቤተመንግሥት ማስገንቢያ 8,000,000 ዶላር አፈሰሱ ። መርከብ መጠገኛ ወደብ ለማስገንባት 17,000,000 ዶላር ከሰከሱ ። በሰባት ዓመት ውስጥ (1958 - 1965 ) የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ የነበረው 481,000,000 ዶላር ተሟጦ በተቃራኒው አገሪቱ የአንድ ቢሊየን ዶላር ባለእዳ ሆነች ። በዚህም የተነሳ ሕዝቡ መንቀፍና መቆጣት ሲጀምር ንክሩማ ጠረጠሩና ጭካኔ አመጡ ። ተቃዋሚዎቻቸውን አሠሩ ፤ ራሳቸውን የእድሜልክ ፕሬዚዳንት አደረጉ ፤ ፓርላማውን አዳክመው ያቀረቡለትን ሁሉ የሚያፀድቅ ግዑዝ የላስቲክ ማህተት ዓይነት አደረጉት ። ከዚያም ተቃዋሚዎች ሁሉ ያለፍርድ አምስት ዓመት እንዲታሰሩ የሚያዝዝ ድንጋጌ አወጡ ። ወደ ኮሚኒስቱ ዓለም ተጠጉ ። በ1966 ወደ ቻይና ለጉብኝት እንደሄዱ ሲገለበጡ ሕዝቡ እጅግም አላዘነላቸውም ። ሐውልታቸውን ነቀሎ ጣለ ፤ ፎቶግራፋቸውን ለዓለም የኢንተርፖል አባል አገሮች አሰራጨ ። ያን የመሰለ ዓለም አቀፍ ዝና ያተረፉ ሰው ወደኋላ ያለእኔ ሰው የለም በማለት በማበላሸታቸው አሳፋሪ አወዳደቅ ደረሰባቸው ።

ንክሩማ በካንሰር እስከሞቱ ድረስ በጊኒ በስደት ኖሩ ። የጊኒው ፕሬዚዳንት ሴኩ ቱሬም ባልተለመደ ሁኔታ ምክትል ፕሬዚዳንት አደረጓቸው ። በ1966 ከገለበጧቸው ወታደሮች አንዱ የሆኑት ኮሎኔል አክዋሲ አማንክዋ ሲናገሩ ፤ "ንክሩማ ትልቅ ሰው ሊሆኑ ይችሉ ነበር። ጥሩ ጀምረው የአፍሪካ የነፃነት ምሳሌ ሆኑ ። በሂደት ውስጥ ሥልጣንን በመውደድ የራሳቸውን ገናና ስም መፍጠርን በመሻት በሕገ መንግሥቱ የተሰጣቸውን ሥልጣን ያለርኅራኄና ያለአግባብ ለምኞታቸው ማሟያ ተጠቀሙበት ። እንግዳ የሆነ የሥልጣን ፍቅር እያደረባቸው መጣ" ሲሉ ተችተዋል ።

የንክሩማ መወገድ ግን የጋናን ችግር አልፈታም ። በአፍሪካ የመጀመሪያው መፈንቅለ መንግሥት የመጨረሻው የሚሆንበት አጋጣሚ ኢምንት ነው ። እሳቸውን የገለበጡ ወታደሮች በሕዝብ ለተመረጠ



መንግሥት ሥልጣን ያስረከቡት ከሶስት ዓመት በኋላ ነበር ። ነገር ግን በ1972 ደግሞ የሲቢሉ መንግሥት በጄኔራል አቾምፖንግ ተገለበጠ ። ጄኔራሉ ያለማቋረጥ የሚያጨሱና ያለውስኪ ውለው የማያድሩ ነበሩ ። አቾምፖንግ በ1978 የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ በነበሩት በሌተና ጄኔራል ፍሬደሪክ አኩፎ ተገለበጡ ። በዓመቱ ደግሞ አኩፎ በሰላሳ ሁለት ዓመቱ የአየር ኃይል መቶ አለቃ ጀሪ ሮውሊንግስ ተገለበጡ ። መቶ አለቃውም ጋናን ለማፅዳት በሚል በምሥጢር ባካሄዱት ፍርድ ሁለቱንም የቀድሞውን መሪ ጄኔራሎች አቾምፖንግና አኩፎን ገደሏቸው ። የቀድሞ መሪዎችና ባለሥልጣኖች ዓይናቸው ተሸብቦ ሊሰቀሉ ሲነዱ ሕዝቡ "ተግባር!ተግባር! ሁሉንም ጨርሷቸው!" በማለት ጮኸ ። በመስከረም ወር 1979 ጀሪ ሮውሊንግስ ቃል በገቡት መሠረት ሥልጣኑን በሕዝብ ለተመረጠ መንግሥት ሲያስረክቡ ሕዝቡን አስገረሙ ።

በፕሬዚዳንት ሂላ ሊማን (የሠለጠኑ ዲፕሎማት) የሚመራው የሲቢል መንግሥት የውጭ መዋዕለ ንዋይ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ባለማበረታታቱ ጋና ጭራሽ ቆረቆዘች ። ብሔራዊ ዕዳዋ ወደ ሁለት ቢሊዮን አሻቀበ። የብድር ዕዳ መክፈል ካቆመ ሰማንያ ዘጠኝ ወራት አለፉ ፤ የዋጋ ግሽበት በየዓመቱ 100% ይጨምር ጀመር ፤ መሠረታዊ ሸቀጦች ለዓይን ስለጠፉ ናይጀርያ እንደ ገና ስጦታ ሃያ ሶስት የጭነት መኪና ምግብና መድኃኒት ላከችላት ።

በ1981 ጀሪ ሮውሊንግስ በጡረታ ከተሰናበቱበት ቦታ ጠመንጃ አንግበው የጦር ሠራዊቱን ድጋፍ ይዘው ብቅ በማለት ከሀያ ሰባት ወራት በኋላ ሥልጣን ዳግም በመንጠቅ ፕሬዚዳንት ሊማንን በማሠር በምዝበራና በአስተዳደር ጉድለት ከሰሷቸው ። ወዲያው የጋና ወታደሮች በደስታ እየፈነጠዙ የዋና ከተማዋን የአክራ ሱቆች በመዝረፍ አፀዱት ። ሮውሊንግስ በበኩላቸው "ከተገቢ ዲሞክራሲ ሌላ የምንጠይቀው ነገር የለም" በማለት በሬዲዮ ለፈፉ ።

እንደሌሎች የአፍሪካ አገሮች ሁሉ ጋና ዛሬ አንዱ ችግሯ የንግድ ልውውጥ የምታደርገው 'ከለሙት አገሮች ጋር መሆኑ ነው ። ከጐረቤቶችዋ ጋር የንግድ ልውውጥ የላትም ። ይህም የአፍሪካን ኢኮ

ኖሚ የሚያላሽቀውና በቂኝ ገዢዎች የተመሠረተው የአንድ ምርት ኢኮኖሚ ውርስ ነው ። አፍሪካ በጅስዋ አህጉር ካሉ አገሮች ጋር የምታደርገው የንግድ ልውውጥ አራት በመቶ ብቻ ነው ። ይህም በዓለም አነስተኛ የአህጉር አቀፍ የንግድ ልውውጥ ነው ። ይህ ሁኔታ የሚፈጥረውን ችግር ለመረዳት የአሜሪካ ሃምሳዎቹ እስቴቶች እርስ በርስ ሳይሆን ከሌላው ዓለም ጋር ብቻ ቢነግዱ ምን ይፈጠር እንደ ነበር እንደምሳሌ መውሰድ ይቻላል ። ስለዚህ እያንዳንዱ እስቴት ሥጋ ከአውስትራሊያ ፣ ሠላጣ ከሜክሲኮ ፣ ቢያስመጣና ዓሳቸውን ለኢጣልያ ፣ ጀልባዎችን ለብራዚል ቢልኩና የፋብሪካ ምርቶችን ከአውሮፓና ከእስያ በመግዛት እርስ በርስ ምንም ባይለዋወጡ ችግር ላይ ይወድቁ ነበር ። ምክንያቱም ኒውዮርክ ዋናው ምርቷ ፍራፍሬ በድርቅ ምክንያት ቢጠፋ ሌላ የምታካክስበት ምርት ስለማይኖራት ከእንግሊዝ ገንዘብ መበደር ይኖርባታል ማለት ነው ።

ይህን በውጭ ገበያ ላይ ጥገኛ መሆንን ለማስቀረት እያንዳንዱ የአሜሪካ እስቴት ቀላል ኢንዱስትሪዎች ማቋቋም ይጀምራል ። ግን ቅንጅት ስለማይኖር ጐረቤት አገር ምን እየተሠራ እንደሆነ አያውቅም እንበል ። ወዲያውም እያንዳንዱ እስቴት የራሱ ቢራ ፋብሪካ ፣ የሲሚንቶ ማምረቻ ፣ የሲጃራ ፋብሪካ ያቋቁማል ። ብዙዎች ትንሽ ስለሚሆኑ ትርፍ ማስገኘት ስለማያስችሉ በመንግሥት ድጐማና በከፍተኛ ታሪፍ ድጋፍ ይደረግላቸዋል ማለት ነው ። የሁኔታውን አጉልነት በመረዳት ጥቂት እስቴቶች የየራሳቸው ዓለምአቀፍ አየር መንገድ እንዳለ ሆኖ ክልላዊ የኢኮኖሚ ኮሚኒቲ ያቋቁማሉ ። ስድስቱን አየር መንገዶቻቸውን ወደ አንድ ያጠቃልላሉ ። የንግድ ገደብና የይለፍ እንጃ ግራንጃን ያስወግዳሉ ። አንዱ የሲጃራ ፋብሪካ ብቻ ለሁሉም የሚያስፈልገውን ምርት እንዲያቀርብ ይሆናል ። ነገር ግን ከጅምሩ ችግር ይኖራል ። እስቴቶች የሚናገሩት የተለያየ ቋንቋ ነው ። የሚጠቀሙበት በተለያየ የገንዘብ ዓይነት ነው ። የአንዱ እስቴት ገንዘብ በሌላው ተቀባይነት የለውም ። ገፅታውን ይበልጥ ለማብራራት ለምሳሌ ሁለት እስቴትስ ቤርሞንት እና ኒው ሀምፕሻየር በድንበር ውዝግብ ይዋጋሉ እንበል ። ሜን የምትባለዋ እስቴት በወታደር የምትገዛና



ማርክሲስት ፍልስፍና ለመከተል የወሰነች ናት ። ከኔቲከት የተሰኘችዋ እስቴት ደግሞ ወደ ካፒታሊዝም የሚያመራ የሲቢል መንግሥት አቋቁማለች ። ሮድ ደሴት ራሱን የዕድሜ ልክ ፕሬዚዳንት ባደረገ የፖሊስ መኮንን ትተዳደራለች ። ማሳቹሰትስ ደግሞ የመንግስት ግልበጣ ሙከራ ተደርጎባት በማከሸፍ ካናዳን የወታደር ርዳታ እንድታደርግላትና የግዛት አንድነቷን እንድትጠብቅላት ጠይቃለች።

ይህ አገላለጽ ለአሜሪካ እስቴቶች እንግዳ ነገር ቢመስልም የአፍሪካ የንግድና የክልል ግንኙነት ግን ይህን የመሰለ ነው ። በቅኝ ግዛት ውርሷ ወጥመድ ተይዛ ፣ በፖለቲካና በባህል ልዩነት ተከፋፍላ፣ በአህጉር አቀፍ አውራ ጐዳና እና የመገናኛ ሥርዓት አለመኖር ተለያይታ ፣ እያንዳንዱ አገር ቅጥ ባጣ ሁኔታ ከተበታተነ የገበያ ሥፍራ የማይሻል ፣ ከጎረቤቶቹ ጋር ግንኙነትም ሆነ መደጋገፍ የሌለው ነው ። በሶስትና በአራት ክልላዊ የኢኮኖሚ ኮሚኒቲዎች ብትሰባሰብ አፍሪካ ትልቅ የኢኮኖሚ ጥንካሬ ሊኖራት ይችላል ። ሃምሳ አንድ የተለያዩ ሀገሮች ሆና ግን እንዳችም ጥንካሬ ሊኖራት አትችልም ።

አፍሪካ በዚህ ሁኔታ ተበታትና ሥራ አጥ እየበዛ ፣ ምርት እየቀነሰ ሲሄድ ከችግር ሊያወጧት የሚችሉት ምሁራኖችዋ በአምባገነን ደንቆሮ መሪዎች ቀጽዕኖ እየደረሰባቸው በሀገራቸው የተነፈጉትን ነፃነት ለማግኘት ወደ አውሮፓና አሜሪካ ይኮበልላሉ ። ፋብሪካዎችም ኪሣራ ላይ ይወድቃሉ ፣ ይህ የሚሆነው የላብአደሩ ደመወዝ ከፍተኛ ሆኖ ሳይሆን የሥራ ዲስፕሊኑ ደካማና ሥራው ጥራት የሌለው ፣ ከሥራ መቅረትን የሚያበዛ ፣ የእጅ ሙያውን ያላሻሻለ በመሆኑ ነው ። በዚህም ምክንያት ምርት እየቀነሰ የሕዝብ ቁጥር እያደገ መጣ ። ሁሉ ነገር የመለማመጃ ዓይነት በመሞከርና በመሳሳት የሚካሄድ ሆነ ። ስለምርት መቀነስም የሚጨነቅ ያለ አይመስልም ።

ሌላው የአፍሪካ ሀብት የዱር አራዊት ሲሆን ፣ ቱሪስቶችን በመሳብ የውጭ ምንዛሪ ገቢ የሚያስገኝ ነው ። ጥሩ ብሔራዊ ፓርኮች ከተዘጋጁ ቱሪስቶች ይጐርፋሉ ። ለምሳሌ ኬንያ በዓመት 150,000,000 ዶላር ከቱሪዝም ታገኛለች ። ይህም ከቡና ከምታገኘው ያላነሰ

ነው ። ነገር ግን የእህጉሪቱ ይህ ታላቅ የአራዊት ሀብትም እየተመናመነ ነው ። ችግሩም ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ነው ።

ለዝሆን ጥርስ ሲባል ዝሆኖች እየታደኑ እያለቁ ናቸው ። የዝሆን ጥርስ ትልቅ ዋጋ እያገኘ በሄደ መጠን ለዝሆን ጠንቅ ሆነ ። በ1970 የዝሆን ጥርስ ግማሽ ኪሎ የማይሞላ ሁለት ዶላር ከሰላሳ ሳንቲም ነበረ ። በ1980 ያው መጠን ዋጋው ሰባ ዶላር ደረሰ ። የራይኖሰረስ ቀንድ ደግሞ በመካከለኛው ምሥራቅ ግማሽ ኪሎ የማይሞላ ሶስት መቶ ዶላር ደርሷል ። በዚህ ምክንያት አዳኝ በድብቅ እየተሰማራ ይህን የአውሬ መንጋ ይረፈርፈው ጀመር ። አምስትና ስድስት ዓመት ቢማስን የማያገኘውን ገንዘብ ከአንድ የዝሆን ጥርስ ያፍስ ጀመር ።

በናይሮቢ የሚኖር እንግሊዛዊ ሳይንቲስት ባካሄደው የመጀመሪያ አህጉር አቀፍ ጥናት እንዳመለከተው በአፍሪካ ሰላሳ አምስት አገሮች ውስጥ 1,300,000 ዝሆኖች እንደነበሩ ይገልጣል ። በአሁኑ ጊዜ ግን በዓመት ከ50,000 እስከ 150,000 በሚደርስ እየተገደሉ ስለሆነና ይህም ሊራቡ ከሚችሉት ቁጥር በላይ ስለሆነ እያለቁ ነው። በ1973 በኬንያ 70,000 ዝሆኖች ነበሩ ። ዛሬ ግን ምናልባት የዚያ ግማሽ ቢኖራት ነው ። የራይኖሰረስ ብዛት ደግሞ በኬንያ ከ10,000 ወደ 2,000 ዝቅ ብሏል ። በዚህ ሥጋት የተነሳ የሰለጠኑ ወታደሮች በአንዳንድ ፓርኮች ያሉ ራይኖዎችን በነፍስ ወከፍ እንዲጠብቁ የሃያ አራት ሰዓት ዘብ ተመድበዋል ። በ1966 በኡጋንዳ ደቡባዊ አውራጃ 8,000 ዝሆኖች ነበሩ ። የኢዲአሚን ወታደሮች ባካሄዱት ሥልት የተከተለ ጭፍጨፋ ወደ አንድ መቶ ስድሳ ቀነሷቸው ። ዛሬ ግን አንድም አይገኝም ። ከአንድና ሁለት ትውልድ በኋላ የአፍሪካ ዝሆንም እንደ አሜሪካ ቡፋሎ ብርቅዬ ሊሆን ይችላል የሚል ሥጋት አለ ።

ዓለም አቀፍ ግፊት እያየለ አራዊት እንዲጠበቁ ተጽዕኖ ሲበዛ ኬንያ አደንን በሕግ ከለከችና ለይስሙላ ያህል ሰባ ወታደሮች በመመደብ ታላቋ ብሪታንያን የሚያክለውን ሰፊ ክልል በእነዚህ ለማስጠበቅ ሞከረች ። ዝሆኖችን በመርዛማ ጦር ወይም ቀስት መግደል ፣ ወይም በሚያደነዝዝ ጥይት እየመቱ ጥርሳቸውን መውሰድ ቀጠለ ።



ገዳዩቹንና ዘራፊዎችን የሚያሰማሯቸው ደግሞ አንዳንድ ባለሥልጣኖች ስለሆኑ መቆጣጠር አልተቻለም ። የኩባንያዎች ባለንብረቶችም በተለይ ዩናይትድ አፍሪካን ኮርፖሬሽን የሚባለው በዚህ ሕገወጥ ንግድ ስማቸው የተጠራ ሲሆን የውጭ ሀገር ተቀባዮችም ከሆንግ ኮንግ በኬንያ የተቀበሉት በሕጋዊ መንገድ መንግሥት ከሸጠው ብዙ እንደማይበልጥ የንግድ እስታትስቲካቸው ያረጋግጣል ። የዓለም ባንክ ከኬንያ ለአራዊቱ ጥበቃ የሚመደቡ ሰዎች አሰልጥኖ ለማሰማራት የሚያስችል 3’000’000 ዶላር ለገሰ ። መንግሥት ግን በዚህ ገንዘብ ያሰለጠናቸውን ልዩ ኮማንዶዎች በበረሃው ሶማሊያ ድንበር በኩል አራዊት በሌለበት ለጥበቃ ዘብ እንዲቆሙ አደረገ ። ዘረፋው ቀጠለ ። የኬንያ ባለሥልጣኖችም እየከበሩ ሄዱ ።

አፍሪካ የዱር አራዊት ሀብቷን ብትንከባከብ መልካም ነበር ። ግን ለእነሱ አራዊት ብርቅም ድንቅም አይደሉም ። አሜሪካውያን በጃርት እንደማይደነቁት ማለት ነው ። ከባለሥልጣኖች ጋር ግንኙነት ላለውና ጠመንጃ ለያዘ እነዚህ አራዊት በቅጽበት ለመበልጸግ የሚያስችሉት ናቸው ። ዝሆኖች መንደሩንና ትምህርትቤቱን ደምስሰው ነፍሱን ለማዳን ዛፍ ላይ ተንጠልጥሎ ላደረ ኬንያዊ ዝሆኖችን ውደድ ማለት የማይመስል ነው ። በዚህ ላይ ዝሆን የሚያበላው (በቀን አንዱ ብቻ) መዐት ስለሆነ በሳምንት ውስጥ እልም ያለውን ለም ክልል ብረሃ ሊያደርገውና ብዙ ጋሻ መሬት እህል ሊያበላሽ ስለሚችል መሬት ለጠበበው ኬንያዊ ሊያርስ የሚችለውን መሬት ለዝሆንና ለቱሪስቶች ሲል መተው የማይቀበለው ቅንጦት ነው ።

በ1975 ሁለት የዝሆን መንጋዎች ወደ ሩዋንዳ ገበሬዎች እርሻዎች ዘልቀው አገር ሲያጠፉ የሩዋንዳ መንግሥት ፈረንጅ አዳኞችን ለመነና መንደሩን ለሕዝቡ እንዲያስለቅቁ አደረገ ። በእግርና በአየር በተደረገ አሰሳ 106 ዝሆኖች ተገደሉ ። ሃያ ስድስት ግልገሎችን በአደንዛዥ ጥይት በመምታት ወደ ብሔራዊ ፓርክ ወሰዷቸው ። ስለአራዊት ክብካቤ የሚሰብኩ የአውሮፓ ሊቃውንት እሪ አሉ ። የሩዋንዳ መንግሥት ግን ቀላል ምርጫ ማድረግ ነበረበት ፤ ከሕዝቡና ከዝ

ሆኖች ማንኛቸው ይኑሩ የሚለው ነው ። በኬንያም ሰው የሰፈረበትን ክልል ከወረሩ የሚደረገው ይኸው ነው ።

አንድ ቀን በኬንያ ሁለት መቶ ዝሆኖች ያህል ያሉበትን መንጋ ከተራቆተው ሰሜን ኬንያ ወደ አበርዳሬ ብሔራዊ ፓርክ ለመንዳት በእግርና በአውሮፕላን ጥረት ሲደረግ አብሬ ነበርሁ ። መንጋው ዝቅ ብላ በመብረር በምታስፈራራ ሄሊኮፕተር ደንብሮና ተደናግጦ በደጋማው ክፍል እንደታንክ ባታሊዮን እየተርመሰመሰና እንደነጐድጓድ እያስገመገመ ፣ ዛፎችን ፣ አጥሮችን ፣ መንደሮችን ሳይቀር እየደረመሰ ፣ ነጎደ ። ሰብሰብ ብለው በመቆም ኩምቢያቸውን ወደ ላይ ሰቅለው እንደጥሩንባ ነፊ አረፍ ይሉና እንደገናም ይንጋጋሉ ። መሬት ተንቀጠቀጠች ፣ መንደርተኛው ሁሉ ሽሽት ያዘ ። አቧራው ወደ ሰማይ ተነሳ ፣ መንጋው የሸለቆውን ደን አረገፈው ። ግልገሎቹ ወደኋላ ላለመቅረት ይጣደፉ ጀመር ፣ ትላልቆቹ ደግሞ ዝቅ ብላ በዛፎች አናት ጥግ በምትበረዋ ሄሊኮፕተር ፊት በአደጋ ጥሩምባ (ሳይረን) እየተነዱ ይነጉዳሉ ።

አብራሪው ሄሊኮፕተሯን ወዲህና ወዲያ እያዞረ ከብቶች እንደሚከበክብ ፈረሰኛ (ካው ቦይ) መንጋውን ወደሚፈለገው አቅጣጫ ይነዳዋል ። ለመንጋው መሄጃ የሚያመቸውን ሸለቆ ከላይ ሆኖ እየቃኘ በእግር ሆነው ለሚያግዙት መመሪያ ይሰጣል ።

“ወደ ደቡብ ሰብሮ ለማምለጥ የሚፈልግ መንጋ ስላለ ጥቂቶቻችሁ በዚያ በኩል ቅደሙ” የሚል መልእክት አስተላለፈ ። “መልካም ፣ ቦንጎ አንድ ፣ ትሰማኛለህ? መኪናዎቹ በቂ ርቀት ላይ ስለሆኑ ከዚያ በኩል መንጋወን ለመመለስ ካሉበት ተዋቸው ። ፊሊፕስ ምን አለ በአንተ በኩል? ”

ከዚያም ከሄሊኮፕተሯ በላይ በሴስና አውሮፕላን እየበረረ ከሚገኘው ጋር መልእክት ተለዋወጠና ከገበሬዎች ጋር ስላለው የመሬት ጭቅጭቅ ያስረዳኝ ጀመር ። እንዲሰማኝ ጮሀ በማለት “እዚያ ታች የምታየው ገበሬው ካላረስሁት እያለ የሚከራከርበት ምድር ነው። ኬንያም በአንድ በኩል የዱር አራዊቶችን እንከባከባለሁ ትላለች ።



የማይጣጣሙ ግቦች ናቸው ፣ አብረው ሊሄዱ የማይችሉ ሀሳቦች ናቸው ። ገበሬውና አራዊቱ በቀረቻቸው አነስተኛ መሬት ላይ ፉክክር ይዘዋል ። ኬንያ ሁለቱንም ማድረግ ስለማትችል ብሔራዊምርጫ ማድረግ ይኖርባታል ። የሰው ልጅና እንስሳ በጥቅም በተጋጩ ቁጥር እስከዛሬ በአሜሪካም ሆነ በአፍሪካ አሸናፊ ሲሆን የታየው አንዱ ብቻ ነው ” አለኝ ። በየፓርኮች የአራዊት ጥበቃ ኃላፊ በመሆን ኬንያን ሲያገለግሉ የኖሩት ፈረንጆች ሞያተኞች በጥቂሮች እየተተኩ ነው ። ጥቂት ቆይቶ በቱሪዝም ኮሚሽን ያሉት ፈረንጆችም ይባረሩና የአራዊት ሀብት በድብቅ በሚያሸሹ ቢሮክራቶች ይሞላሉ ። የዱር አራዊቱ ከማለቅ የማይድኑ መሆናቸው በጣም ያሳዝናል ።

እስከአሁን ስለችግሩ ተወያየን ፣ መፍትሔውስ ? ለመሆኑ መፍትሔ ይኖረው ይሆን ? ምዕራባውያን የሚረዱ ከሆነና አፍሪካም ይህን ታላቅ ሀብቷን ለመጠበቅ ከቆረጠችና የግል ጥቅም ሳይሆን የአገር ጥቅም ማስቀደም ከቻለች መልሱ አዎን ነው ። ስለ ሳውዲ አረቢያ ብልጭ እልም የሚል ተስፋ ስንት እንደተጻፈላት አስብ ። ያች አገር ያላት ነዳጅ ዘይት ብቻ ነው ። አፍሪካ ግን ነዳጅም አላት ። ሌሎች ማዕድናትም አሏት ። ማለቂያ የሌለው ራቧን የሚያስችላት የእርሻ መሬት አላት ። ሳውዲአረቢያ ገና መሠረተ ልማት እየዘረጋች ስትሆን አፍሪካ ግን የተሟላም ባይሆን ከመቶ ዓመት በፊት ጀምሮ የተዘረጉ የልማት መሠረቶች አሏት ። ሳውዲ አረቢያ ለምዕት ዓመታት ከዓለም ተገልላ የኖረች አገር ናት ። አፍሪካ ግን ለብዙ ትውልዶች ከዓለም ጋር ግንኙነት አድርጋ የቆየች ናት ። ሳውዲ አረቢያ አሸዋ ብቻ የሆነች የምታቃጥል በረሃ ስትሆን አብዛኛው የጥቁር አፍሪካ ምድር ግን የአየሩ ጠባይ ተስማሚ ፣ ዓይንን የሚማርክ ውበት ያለው በመሆኑ ከመላው ዓለም የሚጎርፉ ፣ ቱሪስቶች መዝናኛ ሥፍራ በመሆን የእያሌ ቢሊዮን ዶላር መፍሰሻ ምድር ሊሆን የሚችል ነው ።

አህጉሪቱ የፖለቲካ መረጋጋትና ተከታታይነት ያለው ልማት ማረጋገጥ አለባት ። የመከላከያና የደህንነት ወጭዋን መቀነስ ይገባታል ። በእርሻ ላይ ቅድሚያ ትኩረት ማድረግና በዚያም ላይ ተመሥርታ ቀላል ኢንዱስትሪዎች ማስፋፋት ይኖርባታል ። እንደአስፈላጊ

ነቱ በውጭ ኤክስፖርቶች መጠቀምም ይረዳል ። በፖለቲካና በርዕዮተዓለም ከማተኮር ይልቅ የሚያዋጣውን የኤኮኖሚ አቅጣጫ መከተል ጠቃሚ ነው ።

በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኤኮኖሚ ኮሚሽን በተለመው ግብ መሠረት አህጉሪቱ በ2000 ዓ.ም. የኢንዱስትሪ ምርቷ ከዓለም ተመሳሳይ ምርት አንድ ሃምሳኛው ይሆናል ። ይህም ሊሆን የሚችል ውጤት የሚጨበጠው አፍሪካ ምርታማነቷን ከ1980 በአራት እጅ ያሳደገች እንደሆነና አስፈላጊ የሆኑ አውራጐዳናዎችን ፣ ወደቦችን ፣ ፋብሪካዎችን ፣ የሙያ ማሰልጠኛዎችን ለመገንባት የሚያስፈልጋትን 250 ቢሊዮን ዶላር መዋዕለ ንዋይ አግኝታ ሥራ ላይ ያዋለች እንደሆነ ነው ። ይህ ሊሳካ የማይችል ቢመስልም የተፈጥሮ ሀብቷን ለማልማት ጠቃሚ ርምጃዎች ከወሰደች ሊሳካላት ይችላል ። አንደኛ የእርሻ ምርትን በመጨመር ወሊድ መቀነስ ፣ ሁለተኛ ከአዲሱ ትውልድ ታማኝነት ያላቸውን ፣ የተማሩትን ፣ ጥበብና ድፍረት ያላቸውን ፣ በብዙኃኑ ተወካይነት ብሔራዊ አመራር እንዲጨብጡ መፍቀድ ። ሶስተኛ ደግሞ የአካባቢ የኤኮኖሚ ኮሚኒቲዎች በመመሥረት ጠንካራ የኤኮኖሚ ትስስር መፍጠር ይገባል ።

የአካባቢ ቡድኖችን መመሥረት አዲስ ሃሳብ አይደለም ። በአንድ ወቅት ኬንያ ታንዛኒያና ኡጋንዳ አርአያነት ያለውና ኤኮኖሚስቶች ያደነቁት የምሥራቅ አፍሪካ ኮሚኒቲ መሥርተው ነበር ። ሶስቱም አንድ አየር መንገድ ፣ አንድ የፖስታና የትራንስፖርት ፣ እንዲሁም የጋራ ጉምሩክ አገልግሎት ነበራቸው ። ገንዘባቸው አንድ ዓይነት ሆኖ ሁሉም ክልል ውስጥ ይሰራበት ነበር ። የአንዱ ተወላጅ ያለገደብ ሌላው ዘንድ ሄዶ መኖርና መሥራት ይችል ነበር ። በምዕራብ አፍሪካም በ1975 አሥራ አምስት አገሮች ያውም በቋንቋ የተለያዩ ሆነው የምዕራብ አፍሪካን የኤኮኖሚ ኮሚኒቲ (ኤኮዎስ) መስርተዋል ። ላይቤርያ ፣ ሴራሊዮንና ጊኒ ደግሞ የማኖ ወንዝ ሕብረት የሚል አቋቁመዋል ። በ1981 ደግሞ ሴኔጋልና ጋምቢያ ሴኔጋምቢያ የተሰኘ ማህበር መሠረቱ ።



ሲያወሩት ለአፍ የሚቀለው ግን በሥራ ለማዋል አስቸጋሪ ነው ። የካይሮ ኬፕታውን አህጉር አቋራጭ አውራ መንገድ እንዳልተሠራ ሁሉ የኮሚኒቲዎች ትብብርም አልሰራም ። በጉርብትና ከመተባበር ይልቅ የድንበር ግጭቶች ያይላሉ ። በ1977 የምሥራቅ አፍሪካ ኮሚኒቲ የፈረሰው በፖለቲካ ልዩነት ኬንያ ካፒታሊስት ፣ ታንዛንያ ሶሻሊስት ፣ ኡጋንዳ ወታደራዊ አቅጣጫ በመያዛቸው ነው ። በውጤቱ የሁሉም ጥቅም ተዳከመ ። የአህጉር አቋራጩ አውራ ጐዳና መሠራት ጉዳይ ልክ እንደ ደቡብ አሜሪካው ሁሉ ጊዜው ገና አልደረሰም ። ፕሬዚዳንቶች በተራ ምቀኝነት ይዘጉታል ፣ ወታደሮች ቀረጥ ለመሰብሰብ ሲሉ ኬላ ያበጁበታል ፣ መንግሥታቱም ማደስ ይሳናቸዋል ። አፍሪካ አህጉር አቋራጭ ትራንስፖርት እስክትመሠረትና የመገናኛ መረብ እስክትዘረጋ ፣ ብሎም የአካባቢውን መግባባትና ወዳጅነት እስክትፈጥር ድረስ ብዙዎቹ አገሮች ከእርስ በርስ ይልቅ ከአውሮፓ ጋር መነገድን የተሻለ ርካሽ አድርገው መቀጠላቸው የማይቀር ነው ።

የአፍሪካ የወረቀት ገንዘብ መዳከምን በተመለከተ መፍትሔው ቀጥተኛ ይመስላል ። የየአገሩ ብሔራዊ ገንዘብ ቀርቶ በየክልሉ በርካታ ሀገሮች አንድ ዓይነት ገንዘብ በመጠቀምና ያም ገንዘብ ከጀርባ የበለጸጉ አገሮች ድጋፍ እንዲኖረው በማድረግ ማቆራኘት ይጠቅማል ።

የምዕራቡ ዓለም አፍሪካ ነፃ ከወጣች በኋላ ያደረገው ድጋፍ በአመዛኙ አቅጣጫውን የሳተና መናኛ ነበር ። ቅጥ ባጣ መንገድ ለአፍሪካ የተወረወረው የርዳታ ገንዘብ እምብዛም አልጠቀመም ። የፈጠረው ነገር በምፅዋት የመኖርን ስሜት ነው ። መንግሥታትም ከውጭ በነፃ የሚመጣውን የረሀብ ርዳታ በመተማመን እጃቸውን አጣጥፈው ተቀመጡ ። የአፍሪካን ኤኮኖሚ የሚያንቀሳቅሰው ሞተር ድህነት ሆኖ አረፈው ።

ፕሬዚዳንቶች አስቸኳይ ርዳታ ያስፈልገናል ብለው በለፈፉ ቁጥር ምዕራባውያን የሚያስፈልገውን እህል መጠን በመርከብ እስካ

ቀበሉ ድረስ አፍሪካ ምርትን ስለማሳደግ ምን አስጨነቃት ። የምራቡ ዓለም ማድረግ ያለበት ነገር አስገዳጅ እቅድ በማውጣት ሶስተኛው ዓለም የበለጠ በማምረት የሚያባክነውን በመቀነስ እንዲሰራ ማድረግ ነው ። ምንም ዓይነት ርዕዮተዓለም ቢከተሉ ሁሉንም አገሮች መርዳት ያስፈልጋል ። ያለዚያ የአካባቢው ትብብሮችን ማደናቀፍና የክልሉን የእድገት አቅም ማዳከም ይሆናል ። አሜሪካ እንደምታደርገው የራሷን የፖለቲካ አመለካከት የሚከተሉትን ብቻ ለመጥቀም መሞከርና ርዳታን የፖለቲካ ፍላጐት ማስፈጸሚያ ማድረግ ፣ የወሰን ግጭቶችን በማባባስ የአፍሪካን የጋራ ልማት ከሚያዳክም በስተቀር ፋይዳ የለውም ።

ለአፍሪካ ልማት ቁልፉ በምዕራቡ እጅ ነው ። አፍሪካም ከአውሮፓ ጋር የበለጠ የኤኮኖሚ መቀራረብ ማድረግ ይኖርባታል ። ፕሬዚዳንቶችም ፎቶግራፋቸው ያለበትን የወረቀት ገንዘብ ሰርዘው ለክልሉ ሁሉ አንድ ዓይነት በሆነ ገንዘብ በመተካት ብሔራዊ ክብር የሚሉትን የግል ኩራትን አውልቀው ለመጣል ፈቃደኛ ሊሆኑ ይገባል ። ይህ ርምጃ ለኤኮኖሚ መረጋጋትና ለክልላዊ ትብብር ገንቢ ቢሆንና ድሃ አገሮችን የሚያጠናክር ፣ እንደ ናይጀሪያ ሀብታም የሆኑትን የሚያከብር ቢሆንም አንዳንድ ተቺዎች የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ሃሳብ አድርገው ሊመለከቱት እንደሚችሉ አያጠራጥርም ። ነገር ግን አፍሪካ የኤኮኖሚ ተስፋዋን ልትገነዘብ ካስቻላት ፣ ዛሬ እንደምታደርገው ወደኋላ ከመንሸራተት ወደፊት መራመድ አይሻላትም ?



## ምዕራፍ አሥራ አምስት

# ናይጀርያ — አዱኛው አሁን ነው

"ናይጀርያ እየተራመደች ነው ። በዚህ ጉዞ እያንዳንዱ ቀን አዲስ ነው ። ሰልፍህ ወዴት ነው ? ወደ ትናንት ፣ ዛሬ ፣ ወይስ ወደ ነገ ? ናይጀርያ ገንቢና ትርጉም ያለው አስተዋፅኦህን ትሻለች ።"

— በናይጀርያ ቴሌቪዥን በየምሽቱ
በሶስት ሰዐት የሚተላለፍ መልእክት

ናይጀርያ የተሰየመችው በናይጀር ወንዝ ነው ። ትርጉሙም ጥቁር ማለት ነው ። ሞቅ ደመቅ ያለችና ብዙ የሚመኙ ያሉባት ልዩ አገር ናት ። አያሌ ትርምስ ያለባትና ተስፋ የሚፈነጥቅ አስደናቂ እንቅስቃሴ ያለባት አገር ።

ናይጀርያ አንድ መቶ ቋንቋዎች የሚናገሩ ሁለት መቶ ሃምሳ ጐሣዎች ያሉባት አገር ናት ። በሰሜን በረሃማ ፣ በመሃል ተራራማ ፣ በደቡብ ደግሞ ረግረጋማ ምድር አላት ። ከተሞቿ ሕዝብ የበዛባቸው ፣ ለአስተዳደር የማይመቹ ፣ ውጥንቅጡ የወጣ በነዳጅ ገንዘብ የሰከረች አገር ናት ። ናይጀርያ የአፍሪካ ብራዚል በመሆን አዱኛዋ የፈካና አፍሪካ ላሉባት ችግሮች ባዕድ ናት ባትባልም ለጊዜው ሕይወት ያላት አገር ሆናለች ።

ናይጀርያ ረጅም ታሪክ ያላት አገር ናት ። የሰሜን ከተሞቿ ካኖ እና ካሲና የጥንት ነጋዴዎች መመላለሻና መናኸሪያዎች ነበሩ ። አሜሪካን ገና ኮለምበስ ሳያገኛትና ዓለም ሳያውቃት ናይጀርያ የተደራጀ

ግዛት ፡ መደበኛ ቋሚ ጦርና ፣ድንቅ የተባለላቸው የእደጥበብ ባለሙያዎች የነበሯት አገር ናት ። ዛሬም ከብሯ፡ ከዝሆን ጥርስ ፡ ከእንጨት፣ ከመዳብ ፣ የተሰሩ ቅርፃቅርፆቿ በመላው ዓለም ተወዳጅነት ያላቸው ናቸው ።

እንግሊዞች በ1900 ናይጀርያን በቅኝ ከያዙ ጀምሮ ተረፈ ሀብቷን በማጤን ነጮች በዚያ እንዲሰፍሩ አልፈቀዱም ። ከ1922 ጀምሮም እንግሊዞች በአስተዳደር ምክር ቤት ውስጥ አፍሪካውያንን በመጨመር የተለየ ከበሬታ ያሳዩ ነበር ። በ1943 ደግሞ ሶስት ናይጀርያውያን ሥራ አስፈጻሚ የምክር ቤት አባሎችን በመመደብ እንግሊዝ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ናይጀርያን በፌዴራላዊ አስተዳደር ውክልና የራስ አስተዳደር ወደ መመሥረት እንድታመራ አደረገቻት ። ይህንንም ማለሳለስ ያደረገችው የማይቀረው ነፃ መውጣት ሲመጣ ናይጀርያ ከጋራ ንብረት ሀገሮች ማህበር አባልነት እንዳታፈነግጥ ለማባበል ነበር ።

በጥቅምት ወር 1960 ናይጀርያ ያለውዝግብ ነፃ ስትወጣ ብዙ የተመቻቸ ሁኔታ ነበራት ። የራስዋ ነጋዴዎች ፣ አስመጭና ላኪዎች ፣ ጥቂት የተማሩ ሰዎች ፣ ለመቶ ዓመት ሲሰራ የነበረ ነፃ ጋዜጣ ፣ ንቁ ፓርላማ ፣ በቂ የምግብ እህል የሚያመርት የእርሻ ዘርፍና ጠንካራ ኤኮኖሚ ነበራት ። አምስት መቶ ጥቁር ዶክተሮችም ስለነበሯት ከሁሉም የአፍሪካ አገሮች የተሻለ አጀማመር ታየባት ።ከዚህም በላይ ከአራት ዓመት በፊት በናይጀር ወንዝ መዳረሻ ነዳጅ ዘይት ተገኝቶ ስለነበር ተፈጥሮም ራሷ ለናይጀርያ ፈገግታዋን የለገሰቻት ይመስል ነበር ።

ነገር ግን የአፍሪካ ትልቋ ተስፋ ወዲያው ጨለመ ። በመጀመሪያዎቹ አሥራ ስድስት ዓመታት ሶስት መፈንቅለ መንግሥት ተካሄደ ። ሁለት መሪዎች ተገደሉ ። የአንድ ሚሊዮን ሕዝብ ሕይወት የቀጠፈ የእርስ በርስ ጦርነት ተካሄደ ። የአገሪቱ የነዳጅ ዘይት ሽያጭ ገቢ በሚያስገርም ሁኔታ ባከነ ። በምዝበራና በአሠራር ጉድለት ወንጅለው ሲቢል አስተዳደሮችን የገለበጡ ወታደሮች የባሱ መዝባሪዎችና ሥራ



አዋኪዎች ሆነው ተገኙ ። ከተሞች በሕዝብ ብዛት ተንኮታኮቱ ፣ የእርሻ መሬቶች ባዶ ቀርተው ምርት አልባ ሆኑ ። ፓርላማው ተበተነ ፣ ኤኮኖሚው አሽቆለቆለ ፡ ተስፋዋ ሁሉ ተበታተነ ።

ናይጀርያ ከዚያም በኋላ ወደ ሲቢል አስተዳደር እንደገናም ወደ ወታደራዊ አመራር እየነጠረች የተበላሸውን ለማስተካከል ሞከረች ። ናይጀርያ በሕዝብ ብዛትና በተፈጥሮ ሀብት ፣ በዲሞክራሲያዊ አስተተዳደር ፣ በነዳጅ ሀብቷ ከፍተኛነት በዓለም የተለየ ቦታ አላት ። ምዕራባውያንም ከበሬታ ይሰጢታል ።

በ1960 የነዳጅ ዋጋ ከመጨመሩ በፊት ናይጀርያ ከነዳጅ በዓመት 400.000.000 ዶላር ገቢ ታገኝ ነበር ። ዋጋው በድንገት ሲንር ደግሞ በ1975 ዓመታዊ ትርፉ አምስት ቢሊዮን ደረሰ ። በዚያ ወቅት ያለመችውን ሁሉ ለማሳካት ብዙ አዳጋች አልነበረም ።

የናይጀርያ መንግሥት በጥቁር አፍሪካ መንግሥት ተደርጐ የማያውቅ የትየለሌ የሆነ የመቶ ቢሊዮን ዶላር የልማት እቅድ ነደፈ ። በዚህም እቅድ መሠረት ከ1975 – 1980 ባለው ጊዜ ናይጀርያን ከጥንታዊ የብዙ ብሔረሰቦች አገር ወደ ዘመናዊ አንድነቱ የጠበቀ ኅብረተሰብ ለመለወጥ ተነሳሳ ።

ወታደር ፖለቲከኞችና ነጋዴዎች ከየአንዳንዱ ፕሮጀክት በሚሊዮን የሚገመት ገንዘብ እየመዘበሩ እንደታሰበው ባይሳካም ለሰባት አዳዲስ ዩኒቨርስቲዎች ፣ ለአሥራ ሶስት አዲስ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች ፣ ለሰላሳ አራት አዲስ ወህኒ ቤቶች ፣ ለሶስት አዲስ ዓለም አቀፍ ያውሮፕላን ማረፊያዎች ፣ ለአንድ አዲስ የፌደራሉ መንግሥት ዋና ከተማ (አቡጃ) መሥሪያ ዕቅድ ተነድፎ ሥራ ተጀመረ ። የብሔራዊ ግምጃ ቤቱ ተቀማጭ ገንዘብ ሳይረጋገጥ በገንዘብ በመስከር የአገሪቱ መነሻ ደመወዝ በእጥፍ እንዲያድግ ተደረገ ። የመንግሥት ሠራተኞች በሙሉ ስድሳ በመቶ የደመወዝ ጭማሪ እንዲሰጣቸው መንግሥት በመወሰኑ ያለፉት አሥር ወራት ጭማሪ ከታክስ ነፃ ሆኖ አንድ ጊዜ ተከፈላቸው ። ለሠራተኛ ማህበራትም ተመሳሳይ ጭማሪ ተሰጣቸው ።

የመገናኛ አገልግሎትን ለማሻሻል ሶስት ቢሊዮን ዶላር ፣ 13.000 ኪሎሜትር መንገድ በአስፋልት ለመሥራት እንደዚሁ ሶስት ቢሊዮን ዶላር ፣ የፔትሮኬሚካል ፋብሪካ ለማቋቋም ሁለት ቢሊዮን ዶላር ፣ ዓለምአቀፍ የጥቁሮች ፌስቲቫል ለማስተናገድ 200.000.000 ዶላር ፣ ኢንተርናሽናል የንግድ ትርኢት ለማዘጋጀት 100.000.000 ዶላር መደቡ ። አዲሲቱን ናይጀርያ ለመገንባት የሚያስችል የሙያና የቴክኒክ እውቀት ለመማር 50.000 ናይጀርያውያን ወደ አውሮፓና አሜሪካ ተላኩ ።

እንደተገመተው ዓለም ሁሉ ወደናይጀርያ አተኮረ ። ሞስኮና ዋሽንግተን ሊወዳጅዋት ተሯሯጡ ። ሆቴሎች በዲፕሎማቶችና በነጋዴዎች ተሞሉ ። የሌጎስ ከተማ መንገዶች ተጨናነቁ ፣ ስልኮችም ፣ የውሃ አገልግሎትም ፣ የፎቅ መወጣጫ አሳንሰሮችም ፣ አየር መቅዘፊያዎችም ተሰነካከሉ ። ከተማዋ በራሷ እድገት ተተብትባ ስትሰነካከል ማንም ግድ ያደረገ አይመስልም ።

ናይጀርያ በነዳጅ ዘይት ዋጋ መቀነስ ምክንያት ለዘረጋቻቸው ፕሮጀክቶች ልትሰጥ የምትችለው ገንዘብ ከታቀደላቸው ሩቡን ብቻ ነው ። ቁጠባ አወጀች ፣ ሁለት ሺህ የሚደርሱ የባለሥልጣኖች ማመላለሻ ሽንጣም መኪናዎችን በጨረታ ሸጠች ። የደመወዝና የዋጋ ጭማሪ እንዲቆም አዘዘች ፣ የማያስፈልጉ የሸቀጥ ዕቃዎች እንዳይገቡ ወሰነች ።

ናይጀርያ ለአርባ ዓመት የማያልቅ ሰፊ የነዳጅ ዘይትና ገና ያልተነካ የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት ስላላት ባትደኸይም ፣ በአንድ ምርት ብቻ መተማመን የሚያስከትለውን ችግር ተገነዘበች ። ከሚገባው ፍጥነት በላይ ለመራመድ መቻኮልም አደጋ እንዳለበት ተገነዘበች ።

የነዳጅ ዘይት መገኘት ለናይጀርያ ብዙ መፍትሔ ያስገኘላትን ያህል ችግሮችም አስከትሎባታል ። ሌሎች በማዕድን ሀብት የታደሉ የአፍሪካ አገሮች እንደሚያደርጉት ሁሉ ናይጀርያም የእርሻውን ዘርፍ ችላ አለችው ። ራሷን መመገብ የማትችል አገር ደግሞ በእርግጥ ነፃ ልትሆን አትችልም ። ሕዝቡ በነዳጅ ገንዘብ ተሳክሮ



እርሻውን እየጣለ ወደከተማ ሲጎርፍ የግብርና ምርት ተዳከመ ፣ ከውጭ የሚመጣው እህል ዋጋም ናረ ። በአንድ ወቅት በምግብ እህል ራሷን ችላ የነበረችው ናይጀርያ ዛሬ ለሕዝቧ የሚያስፈልጋትን ምግብ ለማስመጣት በዓመት አንድ ቢሊዮን ዶላር ታወጣ ጀመር ። የከተሞች መጨናነቅም አገልግሎቶች ከአቅም በላይ ጫና በዝቶባቸው እንዲሰባበሩ አደረገ ። የነዳጅ ዋጋ በናረባቸው ዘመናት ናይጀርያ የቅብጠቷ ብዛት በየወሩ አምስት ሚሊዮን ዶላር እያወጣች ትኩስ ስጋ ከውጭ ሀገር ታስመጣ ነበር ። በኋላ ናይጀርያ የራሷ ሀብት እስረኛ ሆነች ። የሌጎስ መጨናነቅም የሚያስጠላ ደረጃ ስለደረሰ የውጭ ዜጎች ወደዚያ መሄዱን ጠሉ ። የሌጎስ ከተማ ሕዝብ ብዛት በአሥር ዓመት ውስጥ ከ300,000 ወደ ሶስት ሚሊየን ስላደገ ከተማዋ የራሷን ክብደት መሸከም ተስኗት ወደቀች ።

የመኪና መጨናነቅን ለመቀነስ ሲባል በፈረቃ እንዲነዳና አንድ ቀን ሙሉ ቁጥር ታርጋ ያላቸው ፣ ሌላ ቀን ደግሞ ጎደሎ ቁጥር ያላቸው እንዲዘዋወሩ ተፈቀደ ። የአገሪቱ ሀብታሞች ሁለቱም ዓይነት ቁጥር ያላቸው መኪናዎች በመግዛት መንገዶችን ማጨናነቅ ቀጠሉ ።

ሀብታሙ እየከበረ ድሃው የባሰ እየደኸየ በመሄድ በሌጎስ ኑሮ እጅግ ውድ በመሆን ለመኖር ቀርቶ ለመሰንበት የማያስችል ዋጋ ጠየቀ ። ምግብና ቤት ኪራይ በሚያስገርም ሁኔታ አሻቀበ ። አንድ ደህና ቪላ ቤት በዓመት 50,000 ዶላር ይከራይ ጀመር ። ለዚያውም የሶስት ዓመት ኪራይ በቅድሚያ መክፈል ግድ ነው ። በ1980 በሌጎስ የምግብና መጠጥ ዋጋ ከለንደን ሁለት እጅ ተኩል ፣ ከኒውዮርክ ደግሞ ሶስት እጥፍ ይበልጥ እንደነበር ዋና መሥሪያ ቤቱ በለንደን የሆነው ኤግዚኪውቲቭ ሪሶርስስ ኢንተርናሽናል የተሰኘ ድርጅት ዘግቧል ።

የካፒታሊዝም ሥርዓትን በሚከተሉ ብዙዎቹ የሶስተኛው ዓለም አገሮች እንደሚታየው በበለፀጉት አገሮች ካለው በባሰ ሁኔታ የብሔራዊ ሀብት ሥርጭት የተዛባና ልክ ያልሆነ ነው ። በናይጀርያም እንደዚሁ ገንዘብ የሚዘዋወረው ከላይ ባሉ ከበርቴዎችና ባለሥልጣኖች

መካከል ነው ። ከናይጀርያ ሀብት 75% ውን አንድ በመቶ የሚሆኑት የአገሪቱ ዜጎች ሲቆጣጠሩት ብዙሃኑ በዓመት በአማካይ ስድስት መቶ ዶላር ብቻ ያገኛሉ ። ከልጆቻቸው በሕክምና እጦት ከአሥር አንድ ይሞታል ። ከከተሞች ውጭ ያለው ገጠሩ በሚያሳዝን ሁኔታ ኋላቀር ነው ። ለትምህርት መስፋፋት መንግሥት ብዙ ገንዘብ ቢያፈስም ከናይጀርያ ሕፃናት የትምህርት ዕድል ያገኙት አንድ አምስተኞች ብቻ ናቸው ። ለመኖር የሚቻለው በብርቱ ትግል በመሟሟትና በጉቦና በምዝበራ የተወሳሰበ መንገድ በመሹለክ ነው ። ያለጉቦ የሚሠራ ቅንጣት ነገር የለም ። የሆቴል መኝታ ለመከራየት በጉቦ ። ሆስፒታል ተኝቶ ለመታከም ጉቦ ፣ የኮንስትራክሽን ኮንትራት ለመፈራረም ጉቦ ፣ የመግቢያ ቪዛ ለማግኘት ጉቦ ፣ ሁሉም የሚያከናውነው በጉቦ ነው ።

“ ታውቃለህ ፣ በእውነተኝነት እንደ አንድ ሕዝብና አገር መተባበር ከቻልን በዚች አገር ትልቅ የተፈጥሮ ቅምጥ ሀብት አለን ። ነገር ግን እነዚህ ጥልቅ ክፍፍሎች በታትነውን ይገኛሉ ። ስለሚሻለን ጉዳይ ትምህርት አግኝተናል ብየ ተስፋ አደርጋለሁ ። በእርግጥ ተምረናል? አላውቅም ። የእኔ ግምት ነው። መማራችን የሚታወቀው በጐሣና በዘር አኳያ ሳይሆን በአገር ደረጃ ማሰብ ለመጀመር ዝግጁ ከሆንን ነው ” በማለት ናይጀርያዊው ከበርቴ አቃቤ ሕግ ጎድፍሬ አግቺሬ ብዙ አጫወተኝ ።

በእርግጥም እስላሙ በሰሜን ፣ ክርስቲያኑ በደቡብ ሆነው ናይጀርያ በጐሣ በተከፋፈለውና ተጋፊና ንትርክ ወዳጅ በሆነው ሕዝቧ ምክንያት ቀድሞ ለማስተዳደር አስቸጋሪና ዲሲፕሊን ከሌላቸው የአፍሪካ አገሮች አንዷ ሆና ቆይታለች ። ናይጀርያ በስተሰሜን ሀውሳ እና ፉላኒ የተሰኙ አረብ የመሰሉ ጐሣዎች አሏት ። በምዕራብ ደግሞ ዮሩባ የሚባሉት ከአራት መቶ ጣኦት በላይ የሚያመልኩ ሲኖሩ ከሌጐስ ሕዝብ አብዛኞቹ እነሱ ናቸው ። በምሥራቅ ከብት አርቢና ኋላቀር የሆኑ ኢቦ ጐሳዎች ይገኛሉ ። የእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች የሚያቀርቧቸው የኢቦ ጐሳ ተወላጆችን ነበር ። በዚህም ምክንያት የመማርና ሥራ የማግኘት ዕድል አገኙ ። የተዋጣላቸው አስተዳ



ዳሪዎች ፣ አስተማሪዎችና ነጋዴዎች ሆኑ ። የሚኩራሩና የአዲሲቱ ነፃ ናይጀርያ መሪ ስለሆኑም ሌሎቹ ቀኑባቸው ።

በነፃነት ማግስት ትላልቆቹ ጐሣዎች የሥልጣን ሽኩቻና የተፈጥሮ ሀብቶችን የመቆጣጠር ትግል ጀመሩ ። የኢቦና የሃውሳ ጐሣዎች ግንባር በመፍጠር የዮሩባ ጐሳን ለመቃወም ተነሱ ። በ1966 የኢቦ ጐሳ ተወላጅ የሆኑ የጦር መኮንኖች መንግሥት ገልብጠው ጠቅላይ ሚኒስትሩንና ሌሎች የሰሜን ሰዎችን በመግደል ሥልጣን ያዙ ። ከስድስት ወራት በኋላ የሰሜን ጐሳዎች አባላት ኢቦዎችን በመገልበጥ ሥልጣን ነጠቁ ። የሰሜን ወታደሮች በአሥር ሺዎች የሚቆጠሩ የኢቦ ጐሣ ተወላጆችን እያሳደዱ ገደሉ ። በመጨረሻም በምሥራቅ ያሉ የኢቦ ጐሳ ሽማግሌዎች ከፌዴራሉ መንግሥት ጋር እርቅ እንደማይቻልና ጭፍጨፋ እንደሚቀጥል በመፍራት የኢቦ ወንድማማቾች አንድነት ጥሪ በማድረግ ሁሉም ወደ ትውልድ አካባቢያቸው እንዲሰባሰቡ አሳሰቡ ። ከዚያም እንደተሰባሰቡ በክልሉ ዋና ከተማ በኢኑጉ የአሥር ሚሊየን ኢኑጐ ተወላጆች መሪ ነበሩት አክስፎርድ ዩኒቨርስቲ (እንግሊዝ) የተማሩት ሌተና ኮሎኔል ኦጅኩ የሪሴፕሽን ግብዣ አደረጉና የአገሪቱ ከፍተኛው የነዳጅ ሀብት ክምችት ያለበትን ክልል ተገንጥለው ነፃ የቢያፍራ ሪፑብሊክ መቋቋሙን አበሰሩ ።

ለሰላሣ ወራት ኢቦዎች ለመገንጠል ተዋጉ ። ማንም ድጋፍ የሰጣቸው ግን አልነበረም ። ፈረንሣይ ብቻ ነዳጅ ዘይት ለማግኘት ስትል ትንሽ ረዳች ። አውሮፓ ፣ አሜሪካና ፣ ሶቪዬት ኅብረት አሸናፊውን በመወዳጀት የናይጀርያን ጓደኝነት ለማግኘት ውስጥ ውስጡን ተሻኮቱ ። በኋላም ኢቦዎች ተሸነፉና ወደ ሰሜን ተባረው እጅ ሰጡ ። ኮሎኔል ኦጅኩም ተሰደዱ ።

የፌዴራሉን መንግሥት ጦር የመሩት ጄኔራል ጋዎን ተሳካላቸው ። ወዲያውም የበቀል ሳይሆን የብሔራዊ እርቅ ፖሊሲ በመከተል ኢቦዎች እየታደኑ እንዳይገደሉ አደረጉ ። ለመገንጠል ጠብ የጫሩ የኢቦ ተወላጆች ተመልሰው በአገር ግንባታ ተሳተፉ ፣ ያፈረሱትን ገንብተው የተሳካላቸው ታታሪ ሠራተኞች ሆኑ ። . . .

ኮሎኔል ኦጅኩ አይቮሪ ኮስት ውስጥ በስደት ሲኖሩ፣ የአትክልት
ንግድ ጀምረው ባለሚሊዮን ዶላር ከበርቴ ሆኑ። በ1979 ወደ አገራቸው
ተመልሰው በናይጀርያ ብሔራዊ የፕሬዚዳንት ምርጫ ለመወዳደር
ጠይቀው ሳይፈቀድላቸው ቀረ ። በ1982 ኦጅኩ ተፈቅዶላቸው ወደ
ናይጀርያ ተመለሱ ። ወደ ትውልድ ሀገራቸው በመሄድም "የኢቦዎች
የመጀመሪያ ደረጃ ኃላፊነት ከሁሉም አስቀድሞ ናይጀርያዊ መሆና
ቸውን ማሰብ ነው" ሲሉ አወጁ ።

አሰቃቂው የቢያፍራ ጦርነት የሚያስተምረን ብሔራዊ አንድ
ነት በናይጀርያ እንደሚቻል ነው ። በአፍሪካም እንዲሁ ። ጠንካራ
ማዕከላዊ መንግሥት ካለ ፣ ከጎሳ ስሜት ይልቅ ብሔራዊ የሀገር ስሜ
ትን ለማስቀደም ፈቃደኛነት ካለ ፣ ለሕዝቡ በቀደምትነት የሚያስፈ
ልጉትን የሚተልም የኅብረት አመራር ካለ ፣ ብሔራዊ ግዴታውን
እየተወጣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ጥቅም የሚያገኝ ሕዝብ ካለ የሀገር
ፍቅር ስሜት ይፈካል ።

በናይጀርያ የሲቢል መንግሥት በምርጫ ለማቋቋም ክብዙ ክር
ክር በኋላ ሕገመንግሥት ፀደቀ ። ጐሰኝነትን ለመቀነስ በሚል አሥራ
ዘጠኝ ፌደራል ክልሎች ድንበራቸው ተሰምሮ ተመሠረቱ ። ከየአንዳንዱ
እስቴት ቢያንስ አንድ ሚኒስትር ያለበት የሚኒስሮች ምክር ቤት እንዲ
ቋቋም ተደረገ ። ጐሰኝነትን ለመቀነስ ሲባልም የፖለቲካ ፓርቲዎች
በማዕከላዊው መንግሥት ዕውቅና ለማግኘት ክልላዊ ብቻ ሳይሆን
አገር አቀፍ ብሔራዊ መሠረት እንደሚያስፈልጋቸው ተሰመረበት ።

ናይጀርያ የቀየሰችው የፖለቲካ ሥርዓት የዩናይትድ ስቴትስ
ዓይነት ነበር ። በዚህም ለአራት ዓመት የሚያገለግሉ ፕሬዚዳንትና
ምክትል ፕሬዚዳንት ፣ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፣ መወሰኛ ሸንጐና የተወካ
ዮች ምክር ቤት ያሉበት ነበር ። የእንግሊዝ ዓይነቱ የፓርላማዊ ዲሞ
ክራሲ የሕዝብ ድጋፍ አጥቷል በሚል ሾት ፡አፍ ፡ ኖ ፡ ኮንፊደንስ በየ
ጊዜው ምርጫ እየተደረገ መንግሥትን ቶሎ ቶሎ የሚለዋውጥ ስለሆነ
አልወደዱትም ።

በመስከረም 1978 ፓርቲዎች ፕሮግራሞቻቸውን ለሕዝብ በማ
ስተዋወቅ ለምርጫ እንዲዘጋጁ በተፈቀደ በሁለት ሳምንት ውስጥ



ሃምሳ ሁለት ፓርቲዎች ለምርጫ ለመወዳደር ብቅ አሉ ። አርባ ሰባቱ
ብሔራዊ ወይም አገር አቀፍ መሠረትና ድጋፍ ስለሌላቸው ተከለ
ከሉ ። የፓርቲዎቹ አመለካከት የተለያየ ሆኖ ከሶሻሊስት እስከ ካፒ
ታሊስት ያሉትን አመለካከቶች የሚያጣቃልል ነበር ። ሁሉም የማይ
ፈጽሙትን ሁሉ ለሕዝቡ ቃል በመግባት (በምዕራቡ እንደሚደረገው)
ውድድር ጀመሩ ። ናይጀርያ ከግል ፍላጐት ይልቅ የሀገሪቱን ብሔ
ራዊ ጥቅሞች የሚያስቀድም ጠንካራ መንግሥት እንደሚያስፈል
ጋት ሁሉም ተስማምተዋል ። ለአገሪቱ እድገት የሚበጅ ተጨባጭ
ነት ያለው ወጭውን ከጥቅሙ ያገናዘበ የልማት ዕቅድ የሚዘረጋ
መንግሥት እንደሚያስፈልጋትም የጋራ ግንዛቤ ነበረ ።

ናይጀርያ እንደ ሌሎች ሰባት የጥቁር አፍሪካ አገሮች ዘረኝነት
ያየለባት ስለሆነች ከነፃነት ጀምሮ ብሔራዊ ተቀባይነት ያለው የሕ
ዝብ ቆጠራ አካሂዳ አታውቅም ። በ1963 የተካሄደው የነፍስ ወከፍ
ቆጠራ የሰሜን እስላሞች ቁጥር ከደቡቡ ክርስቲያኖች የሚበልጠው
በጥቂቱ መሆኑን በማሳየቱ ተቀባይነት አጣ ። የ1973 ቆጠራ ደግሞ
የሰሜን ሕዝብ ከደቡቡ እጥፍ ሊሆን እንደሚቃረብ ስለዘገበ ዋጋ
ቢስ ተባለ ። የሁለቱም ቆጠራዎች ትክክለኛነት ጥርጣሬ ላይ ስለወ
ደቀ ተሰረዘ ። ስለዚህም ተጨባጭነት ያለው የልማት ዕቅድ ለመቀ
የስ ችግር ሆኖ ቆይቷል ። የናይጀርያ ሕዝብ ብዛት ግምትም ከሰማ
ንያ እስከ አንድ መቶ ሃያ ሚሊዮን የሰፋ ሆኗል ።

የናይጀርያ ሕዝብ በ1979 ፕሬዚዳንቱን ለመምረጥ ወደ ምርጫ
ጣቢያዎች ጎረፈ ። ቀድሞ የትምህርት ቤት ድሬክተር የነበሩት አል
ሀጂ ሼሁ ሻጋሪ ፕሬዚዳንት ሆነው ተመረጡ ። ከሰሜን ሀውሳና
ፋላኒ እስልምና ተከታይ ጐሳ ስለነበሩና ምክትላቸው ከሌላ ጎሳ
እንዲሆኑ ሕገመንግሥቱ ሥለሚያዝዝ ምክትላቸውን ከኢቦ ጎሳ መረጡ፤
ለዲሞክራሲ ጠንካራ መሠረት ገነቡ ። በ1983 በድጋሚ ተመረጡ ።
የምርጫው ሂደት የተደነቀ ሲሆን በመላ አገሪቱ በተቋቋሙ 166.000
የምርጫ ጣቢያዎች የተከናወነ ነበር ።

በናይጀርያ የተካሄደው ምርጫና ወደ ሲቪል መንግሥት መሸጋ
ገር ለአፍሪካ የሚኖረው አርአያነት ጐልቶ ታየ ። ወታደሩ ቁጥር

ከምን ገብቶ ይዘልቅ ይሆን? ዘረኝነት እንደገና ይንሰራራ ይሆን? ከነዳጅ ሀብት የሚገኘው ለብዙኃኑ ሕዝብ እንዲጠቅም ለጥቂቶቹ መክበሪያ መሆኑ ይቀር ይሆን? እነዚህ ፈታኝ አግራሞች አጠያያቂ ሆነው ቆዩ። የተማረ ሕዝብ በብዛት ስላላትም ዲሞክራሲያዊ ጅምሩ ይዘልቃል የሚል ተስፋ ነበር። ነገር ግን አልሆነም። በ1983 መጨረሻ የናይጀርያ ሲቢል መንግሥት በወታደሮች ተገልብጦ ፕሬዚዳንት የነበሩትና ባለሥልጣኖቻቸው በምዝበራ ተወንጅለው ታሰሩ። አመራሩን የጨበጡት ጀኔራል ሞሐመድ ቡሀሪ ኢኮኖሚውን እቃንተው እንደሚያራምዱ ቃል ገቡ። የናይጀርያ አስደናቂ የዲሞክራሲ ሙከራ (ኤክስፐርመንት) አከተመ። እንደገና ወታደሮች ሥልጣን በጠመንጃ ነጠቁ።



<u>ምዕራፍ አሥራ ስድስት</u>

# ለብቻ ከአለም መጣላት

" ሌሎች የጥቁር አፍሪካ አገሮች ሁሉ ራሳቸውን ያስተዳድራሉ። እኛም በአፍሪካ ሶስት መቶ ዓመት ስለኖርን እንደ እነሱው ራሳችንን ለማስተዳደር መብት አለን። ይህን መብታችንን ከመጠቀም ወደ ኋላ ልንል አንችልም፣ አንሻምም። "

— ጆን ቮርስተር
የቀድሞ የደቡብ አፍሪካ ጠቅላይ
ሚኒስትር

"ወጣት የጦር መኮንን ከነበርሁበት የመጀመሪያዎቹ ቀናት ጀምሮ ለደቡብ አፍሪካ ነፃነት ብኖጋ የዕድሜ ልክ ምኞቴን እንዳሳካሁ እቆጥረዋለሁ የሚል ስሜት ነበረኝ። "

— ሌተና ጀኔራል ኦሉሴጉን ኦባሳንጆ
የናይጀርያ መሪ የነበሩ

ደቡብ አፍሪካ በአህጉሪቱ የበለፀገችና ከአንደኛው ዓለም የምትዳመር አገር ናት። ዘረኛነትን በተደራጀ መልኩ የምታራምድ በመሆኗ ትጠላለች እንጅ ደቡብ አፍሪካ እያንዳንዱ የአፍሪካ አገር የሚመኘው ደረጃ ላይ የደረሰች አገር ናት። በጥቁሮች ርካሽ ጉልበት፣ በነጮች ዕውቀት፣ ግለቲያ በሌለው የወርቅና የአልማዝ ሀብቷ ደቡብ አፍሪካ አውቶሚክ ቦምብ ለመሥራት በሚያስችላት ደረጃ ተራምዳለች። በዚህም የዓለምን ውግዘት ለመቋቋም የሚያስችል አቅም

ያላትና በሀብቷም አፍሪካ ቀርቶ አውሮፓዊ መንግሥት የሚቀናባት ናት ። የሚገርመው ግን እዚህ ደረጃ የደረሰችው ከሌሎች የበለጠ የተፈጥሮ ሀብት ኖሯት አይደለም ።

አንድን ፈረንጅ የደቡብ አፍሪካ ዜጋ አገሩ ከሌሎች በብዙ የተሻለ የሆነችው ለምንድነው ብለህ ብትጠይቀው ቀላል መልስ ይሰጥሃል ። "ደቡብ አፍሪካ በነጮች የምትመራ ስትሆን ሌሎች የጥቁር አፍሪካ አገሮች ግን የሚመሩት በጥቁሮች ነው ።"

ነጭ ደቡብ አፍሪካውያን ዓለምንም ሆነ የራሳቸውን አገር የሚመለከቱት በተለየ ዓይን ነው ። አያሌ ትልልቅ ውጤቶችን ያገኙት በከፍተኛ መስዋዕትነት ነው ። የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በጥቁር ዜጎች ላይ የሚፈፅመው በደል አንዳንድ ጥቁር መሪዎች በሀገራቸው ሕዝብ ላይ ካደረሱት ግፍ ያልከፋ መሆኑ ሐቅ ቢሆንም በአህጉሪቱ ውስጥ ለክርክር ሊቀርብ የሚችል አይደለም ። ለብዙ አፍሪካውያን በዓለም ላይ ከሁሉም የከፋ ወንጀል ነጮች በጥቁሮች ላይ የሚፈፅሙት ዘረኝነት ነው ። ሌሎች በድህነት ፣ በበሽታ ፣ በጦርነት ፣ በኮምኒዝም የደረሱ ችግሮች ላይ ሁሉ ጥላውን ስላጠላባቸው እንደዚያ ጉልተው አይታዩም ። በአፍሪካ ዘረኝነት በግልጽና በሕግ የሚካሄድበት አንድ አገር ብቻ ቀርቷል ። ያ ፣ እስኪወገድ ድረስ ፣ አፍሪካ ከራሷ ጋር ሰላም ሊኖራት አይችልም ።

ለአህጉሪቱ የወደፊት እድል ወሳኝ አካል የሆነችው ደቡብ አፍሪካን ጠጋ ብለን ከመመርመራችን በፊት ሁለት ነጥቦችን ላንሳ ። አንደኛ ደቡብ አፍሪካ 125,400 ሰዎች በእስር ቤት አጉራ የእስረኛው ቁጥር ከጠቅላላው ሕዝብ ቁጥር ሲነፃፀር በሰለጠነው ዓለም ካለው ሁሉ የበለጠና በአንደኛ ደረጃ የሚታይ ነው ። ዘረኛው መንግሥት ያሰራቸውን ሰዎች በዘራቸው ለይቶ መረጃ መስጠት ባይፈልግም የዲፕሎማቲክ ምንጮች እንደሚገምቱት የነጭ እሥረኞች ቁጥር 3% ብቻ ነው ። በሁለተኛ ደረጃ ማወቅ ያለብን በምዕራቡ አገር ከሚበየኑት የሞት ፍርዶች ዘጠና አምስት ከመቶ የሚካሄዱት በደቡብ አፍሪካ ነው ። በ1980 ብቻ 130 ሰዎች በስቅላት ሲቀጡ



አንዱ ብቻ ነጭ ነበር ። ደቡብ አፍሪካ የምዕራቡ ዓለም አካል ተደርጋ ተወስዳለች ።

ዛሬ ደቡብ አፍሪካን ስናስብ አላን ፓቶን ድርሰት ውስጥ የሰፈረው ጥልቅ ትርጉም ያለው አባባል ትዝ ይለናል ። "ክራይ ፣ ዘ ፣ ቢላቭድ ካንትሪ" (አልቅሽ ውድ አገሬ ) በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ያሰፈረው "አንድ ትልቅ ፍርሐት አለኝ ፣ አንድ ቀን ነጮች ጥላቻቸውን ወደ መውደድ ሲለውጡ እኛ ወደጥላቻ ተለውጠን ያገኙናል" የሚል ነው ።

በየምሽቱ የደቡብ አፍሪካ የመንገደኞች ባቡር ከማፑቶ (ሞዛምቢክ) ወደ ጆሃንስበርግ ይጓዛል ። እርቀቱ 376 ማይልስ ብቻ ይሁን እንጅ ጉዞው በሁለት እጅግ የተለያዩ ዓለማት መካከል ነው ። በአስተሳሰብ ጨርሶ በማይገናኙ ግን ተደጋግፈው በሚኖሩ ሁለት ጠላቶች መካከል ነው ።

ድንበሩን አቋርጦ መግባት ልክ አንድ ልዩ ፕላኔት ላይ እንደ ማረፍ ያህል ነው ። በርዕዮተዓለምም በፖለቲካም ጨርሶ የተራራቁ አገሮች በመሆናቸው ነው ። ሞዛምቢክ አብዮታዊ ማርክሲስት አገር ስትሆን ፖርቱጊዞችን በጦርነት ድል ነስታ ነፃነት የተቀዳጀችና የፕሬቶርያ የጥቂት ነጮች መንግሥት እንዲወድቅ የምትታገል ናት ። ደቡብ አፍሪካ ደግሞ ፋሺስት መሰል መንግሥትዋ የናዚን መመሪያ የሚያራምድ ሆና ለነጭ ዘር የበላይነት የቆመች ናት ።

በደቡባዊው የአፍሪካ ክፍል ያሉ አገሮች የኤኮኖሚ ድጋፍዋን ይፈልጉታል ፣ የዘር መድልኦ ፖሊሲዋን ግን በጥብቅ ይቃወሙታል ። ጠንካራ ኤኮኖሚና ጠንካራ ጦር ያላት ከመሆኗም በላይ ዓለም አቀፍ ኅብረተሰብ ጠንካራ የኤኮኖሚ ማዕቀብ ሊያደርግባት ስላልቻለ የአፍሪካ ጩኸትና ውሳኔ በወረቀት ላይ ሰፍሮ ቀርቷል ። የጥቁር አፍሪካ አገሮች በኤኮኖሚ ካልተጠናከሩ ተጽኗቸው ውጤት ሊያመጣ አይችልም ። ደቡብ አፍሪካ በዓለም ላይ ራሳቸውን በመመገብ በቂ የምግብ እህል ኖሯቸው ለውጭው ዓለም ከሚሸጡት አሥራ አንድ አገሮች አንዷ ስለሆነች በማንኛውም ረገድ ተጽዕኖ ለማሳደር የማትቻል ናት ።

የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በየዓመቱ 20% ማለትም ሶስት ቢሊዮን ዶላር ለመከላከያ በጀት ለማዋል ይችላል። የጦር ኃይሉ 86,000 ቋሚና 260,000 ተጠባባቂ ኃይል ሲኖረው 90% የሚሆኑ የጦር መኮንኖች ነጮች ናቸው። በየጦር ካምፑም የዘር መድልኦ ሥርዓት ሥራ ላይ ውሏል። የደቡብ አፍሪካ ጦር በዓለም ብቃት ካላቸው ጦር ኃይሎች አንዱ ሲሆን ጥቁር አፍሪካን በሙሉ በአንድ ወር ውስጥ እስከ ሰሃራ በረሃ ለመውረር የሚችል ነው።

ከደቡብ አፍሪካ ጋር የዲፕሎማቲክ ግንኙነት ያላት አፍሪካዊት አገር ማላዊ ብቻ ስትሆን ሌሎቹ የንግድ ልውውጥም የሚያደርጉት በድብቅ ነው። በየዓመቱ ሃያ የሚደርሱ የአፍሪካ አገሮች ከደቡብ አፍሪካ ጋር በምሥጢር በመነገድ አንድ ቢሊየን ዶላር የሚገመት የምርትና የአገልግሎት ክፍያ እያደረጉ አፓርታይድን በተግባር ይደግፉታል። ኬንያ ከደቡብ አፍሪካ በቆሎ እየገዛች ከሞዛምቢክ አስመጣሁ በማለት ትሸፋፍናለች። ዛምቢያ የከብት ሥጋ እያስመጣች ከቦትስዋና አስመስላ ትናገራለች። ጋቦን ደግሞ የሕንፃ መሣሪያዎች በማስመጣት ከአውሮፓ አስመጣሁ ትላለች። ዛየር 50% የሚሆነውን የምግብ እህል ፍላጎቷን የምታስመጣው ከደቡብ አፍሪካ ነው። ዚምባብዌ 80% የሚሆነው ወደ ውጭ የሚላከው ምርትዋ የሚሄደው በዚያው በኩል ነው። ማላዊ አዲሱን ዋና ከተማዋን ሊሎንግዌን የገነባችው ከደቡብ አፍሪካ ባገኘችው 12,000,000 ዶላር ብድር ነው። የሞዛምቢክ ወደቦችና የባቡር ሐዲዶች የሚንቀሳቀሱት በደቡብ አፍሪካ ቴክኒሺያኖችና አስተዳዳሪዎች ነው። ስድስት አጎራባች አገሮች 182,000 ላብ አደሮች በደቡብ አፍሪካ ማዕድናት እንዲሰሩ ያቀርባሉ። የኬፕ ቨርዴ ሪፑብሊክ 20% የውጭ ምንዛሪ ገቢዋን የምታገኘው የደቡብ አፍሪካ አየር መንገድ ወደ አውሮፓና አሜሪካ ሲመላለስ ነዳጅ ለመሙላት በዚያ ሲያርፍ ከሚሰጣት ክፍያ ነው። አውሮፕላን ማረፊያውን የሰራችላት ራሷ ደቡብ አፍሪካ ስትሆን አየር መንገዱ በማንኛውም የአፍሪካ አገር እንዳያርፍ ስለተከለከለ ኬፕ ቨርዴ ባትፈቅድለት በቀጥታ ወደ አውሮፓና ኒውዮርክ በረራ ለማድረግ አይችልም ነበር።



ጥቁር አፍሪካ ዘረኝነትን ብታወግዝም ለመኖር ስትል ከደቡብ አፍሪካ የኤኮኖሚ ግንኙነት ማድረጓ አልቀረም። በአንድ ወቅት የታንዛንያው ጁሊየስ ኒሬሬ ሲናገሩ፣ “ጫማ ባይኖረኝና ልገዛ የምችለው ከደቡብ አፍሪካ ብቻ ቢሆን ባዶ እግሬን መሄድ እመርጥ ነበር። የምበላው ባይኖረኝና ላገኝ የምችለው ከደቡብ አፍሪካ ብቻ ቢሆን ግን ወደዚያ መሄዴ አይቀርም” በማለት ገልጸውታል።

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ደቡብ አፍሪካ ከመሄዴ ዘጠኝ ወራት አስቀድሞ በጥቁር አፍሪካ አገሮች ተዘዋውሬ ሁኔታውን ተመልክቻለሁ። የቆሸሹ ሆስፒታሎች፣ የማይሰሩ ታይፕ ማድረጊያዎችና የተበላሹ ስልኮች የሞሉበት የመንግሥት መሥሪያ ቤት መመልከት እንግዳ ነገር አይሆንብኝም። መማሪያ ጠመኔ የሌለባቸው ትምህርት ቤቶችና መፀዳጃ ክፍሎቻቸው የሽንት ቤት መቀመጫ የሌላቸውና የተበላሹ ሆነው ማየት አዲስ ነገር አይደለም። ከአሁን ወዲያ የሚያስገርመኝ አይሆንም ብዬ ደምድሜአለሁ። ደቡብ አፍሪካ ስደርስ ግን እንደገና የሚያስገርም ነገር አጋጠመኝ። ሁሉ ነገር ይሰራል። ስልኩን አንሳው ይሠራል፣ ውሃ ቧንቧ ክፈት ይሰራል፣ አስተናጋጅ ጥራ በቅፅበት የምግብ ዝርዝር ያለበት (ሜኑ) ይዞልህ ከተፍ ይላል። የአውሮፕላን ቲኬት ብትገዛ ልክ በሰዐቱ መብረር ትችላለህ። በየከተሞች ብትዘዋወር ሱቆች ሁሉ በልዩ ልዩ ዕቃ ጢቅ ብለዋል። ከአውሮፓ ከወጣሁ ጀምሮ ያላየሁት ነገር አጋጠመኝ። እንኳን የከተሞች ወደገጠር የሚወስዱት አውራ ጐዳናዎች ሁሉ ልዩ ናቸው።

በ1886 ወርቅ ሲገኝ የተመሠረተችው ጆሃንስበርግ ከተማ ለኑሮ እጅግ ምቹ ናት። አንድ ሚሊዮን ተኩል ሕዝብ የሚኖርባት ይህች ከተማ ታላላቅ ሕንፃዎች ሞልተዋታል። ከተማው እንደ ሌሎች የአፍሪካ አገሮች ከተሞች ኃይለኛ ነፋስ ከተነሳ አወላልቆ የሚወስደው የሚመስል ሳይሆን ደርዝ ያለውና ግርማ ሞገስ የተላበሰ ነው።

የሚገርመው ነጭ ከሆንህ በደቡብ አፍሪካ ጭቆናውንም ሆነ ጭንቀቱን አትረዳውም፣ አይሰማህም። እንዲያውም በከተማው ውስጥ ብዙም ጥቁር ስለማይታይ በጥቁር አፍሪካ ምድር መሆንህ

አይታወቅህም ። በሄድህበት ሥፍራ ሁሉ የት አሉ ጥቁሮች ? የሚል ሃሳብ ይመጣብሃል ። ከአገራቸው የት ቻደበቁ ያሰኛል ።

ያለመንግሥት ፈቃድ የማታያት ከተማ ስዌቶ (ሳውዝ ዌስት ታውንሺፕ ለሚለው ምህፃረ ቃል) ናት ። ከጆሃንስበርግ ግማሽ ሰዐት በባቡር የምታስሄደዋ ይህች ከተማ ሁለት ሚሊዮን ነዋሪዎች አሉባት ። ሁሉም ጥቁሮች ናቸው ። በአቧራማ መንገዷ ጋሪዎች ይዘዋወራሉ ። ኤሌክትሪክ የሌለባቸው ሳጥን የመሳሰሉ ቤቶች ተደርድረውባታል ። በብስጭት የሚኖሩት ጥቁሮች ማታ ማታ ብራንዲ ሲጎነጩ ያመሻሉ ። ወጣቶች እየተዘዋወሩ ከነጮች በሰረቁት ሽጉጥ በጨለማ መንገዶች ነፍስ ይቀማሉ ። በዚህ መስል ተስፋ መቁረጥና ብስጭት ቢኖሩ ነጮችም ያን ማድረጋቸው የማይቀር ነው ።

ከሌላው የአፍሪካ አገር ጋር ሲነፃፀር በዚያ ያሉት ጥቁሮች ዘልቀው የተማሩ ፣ በደንብ የለበሱ ፣ ሀብት ያፈሩ ፣ በተሻለ ምቾት የሚኖሩ ናቸው ። በአንፃራዊ ከአገሪቱ ሀብት አኳያ ሲታይ ግን በጣም ትንሽ ነው ። የደቡብ አፍሪካው ጥቁር ከሌላው የአፍሪካ ጥቁር ጋር ሲነፃፀር አይሻም ። ከነጩ ደቡብ አፍሪካዊ ጋር ነው ራሱንና እድሉን የሚያነፃፅረው ። በዚህም ብዙ ዝቅ ብሎ እንደሚገኝ ያያል ። ከነአካቴው የአገሩ ዜጋም አይደለም ፤ በመያዣ የተወሰደ (የተጠለፈ) ሰው ማለት ነው ። በስዌቶም ሆነ በአካባቢው የጥቁሮች መኖሪያዎች ንብረት መግዛት አይችልም ። ያለፈቃድ ጆሃንስበርግ ከተማ መግባት አይችልም ፣ ቢገባም ያለሌላ ፈቃድ ሌሊቱን በዚያ ማሳለፍ አይችልም ። ነጮች ብቻ ባሉበት ፓርላማ ውስጥ ምንም ድምፅ የለውም ፣ ስለእሱ የሚናገርለት የለም ። ከአሥራ ስድስት ዓመት በላይ ከሆነ ዘሩን ፣ ቀጣሪውን ፣ ታክስ መክፈሉን የሚገልጽ ፓስፖርት ሁልጊዜ መያዝ ይገደዳል ። በጆሃንስበርግ ከተማ መፀዳዳት ቢፈልግ የሚፈቀድለት 160 በሚሆኑ የጥቁር ሕዝብ መፀዳጃዎች መጠቀም ብቻ ነው ። የቀረው በሙሉ ለነጮች የተተወ ነው ።

ዘረኝነት በሕግ እንደሥርዓት የተዘረጋባት የእሱ አገር ብቻ ናት ። የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለነጮችና ለጥቁሮች የሚሠራው በተለያየ



መስመር (ቻነል) ነው ። የጥቁሩ ሕዝብ እያንዳንድዋ የሕይወት እንቅስቃሴው ከሶስት መቶ በሚበልጡ የዘር መድልኦ ሕጎች የተገደበና በተጽዕኖ ሥር የወደቀ ነው ። ማንን መውደድ እንደሚችል ፣ ማንን እንደሚስም ፣ ማንን እንደሚያገባና ከማን ጋር የወሲብ ግንኙነት ሊፈጽም እንደሚችል ፣ ከማን ጋር መኖር ፣ መብላት ፣ መንዝ ፣ መማር ፣ እንደሚችልና በሙያነት መሥራት የሚችለውንና በትርፍ ጊዜው ሊሠራ የሚገባውን ሁሉ የሚወስኑ ሕጎች ተጭነውበታል ። የደቡብ አፍሪካ "ልብ አቅልጥ ሕጎች" በየደረጃው በኅብረተሰቡ ውስጥ የዘር ልዩነትን ያዘሉ ናቸው ። የ1949 ድንጋጌ በጋብቻ ከሌላ ዘር መደባለቅን ይከለክላል ። የ1953 ድንጋጌ ደግሞ በተለያዩ ዘሮች መካከል ወሲብ ማድረግን ይከለክላል ። ይህን የሚጥሱ ይታሰራሉ ፣ ለፍርድ ይቀርባሉ ፣ እስከ ዘጠኝ ወር የሚደርስ እስራትም ይፈረድባቸዋል ። አድራጎቱን ላለመቀጠል ወንዱና ሴቷ ተፋቃሪዎች ቃል ከገቡ ውሳኔው ይታገድላቸዋል ።

ነጮች ይህን ሁሉ የሚያደርጉት ለጥቁሮች መብት ከተሰጠ የነጮች ጥቅም ይቀነሳል በሚል ፍርሃት ነው ። ነጮቹ አንዳንድ መናኛ ለውጦች በማድረግ ያሻሻሉ ቢመስላቸውም ጥቁሮች ግን እንደሌሎች የአፍሪካ አገሮች ሕዝቦች የተሟላ መብታቸው እንዲመለስ ይታገላሉ ። የበለፀገች አገራቸውን ለማፈራረስ ባይፈልጉም ለፖለቲካ መብትና ለድል የሚያስፈልገው ብቸኛ መንገድ የዚያ ዓይነት ትግል የሚጠይቅ ከሆነ ከማድረግ አይመለሱም ።

አንድ ሰው ከምን ዘር እንደሆነ የሚወስን የሕዝብ ምዝገባ ቦርድ የሚባል አለ ። የቆዳህ ቀለም ከየቱ እንደሚያዳምርህና በዚያም ምን መብት እንደሚኖርህ የሚወሰነው በዚህ አካል ነው ። ዝርያየና ቀለሜ ተሳስቶ ከሌላ የሚያዳምር የይለፍ ተሰጥቶኛል በማለት አቤቱታ የሚያቀርቡትን እየመረመረ ውሳኔ ይሰጣል ። ወራትና አንዳንዱም ዓመታት በሚወስደው በዚሁ ምርመራ የቆዳ ቀለምን ፣ የፊት አቀማመጥን ፣ የፀጉር ደረጃን ፣ አጥንቶ ቦርዱ ውሳኔ ይሰጣል ። የእሱም ውሣኔ ይግባኝ የለውም ። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ቦርዱ 150 ሰዎችን አጥንቶ ዘራቸውን እንደገና በመመደብ ወስኗል ። በዚህም

ውጤ አሥር ነጮች ሌላ ቀለም የተቀላቀለባቸው ክለርድ ተባሉ፤ ስድስት ሕንዶች ማላይ ተባሉ፤ ሁለት ማላይ ተብለው የነበሩ ሰዎች ሕንዶች ተባሉ። ሁለት ክለርድ ቻይናዊ ተባሉ፤ አንድ ነጭ ማላይ ተባለ፤ አሥር ሕንዶች ክለርድ ተባሉ፤ አንድ ሕንድ ነጭ ተባለ፤ አራት ጥቁሮች ተብለው ተመድበው የነበሩ ሕንዶች ተባሉ፤ ሶስት ነጮች ተብለው የቆዩ ቻይናዊ ተባሉ።

ቻይናውያን ብዙ ጊዜ ከፊል ነጭ ይባላሉ። ጃፓናውያን ነጋዴዎች ደግሞ “የክብር ነጮች” (ኦነሬሪ ዋይትስ) ይባላሉ። ከብዙ ዓመታት በፊት በደቡብ አፍሪካ በተደረገ የሁሉም ዘሮችና ቀለሞች የተሳተፉበት የቁንጅና ውድድር ጥቁር አፍሪካዊቷ ማይሞና ሳሊ አሸነፈች። ነገር ግን ሽልማቱ ለነጮች ብቻ የተፈቀደ መዝናኛ ሥፍራ ሄዶ ለሁለት ሳምንት መንሸራሸር የሚያስችል ስለነበረ ለጥቁር ስለማይፈቀድ ሳትቀበል ቀረች። በዚህ የተናደደው አሜሪካዊ የሸላሚው ድርጅት ባለንብረት ወደ መዝናኛው የሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ ሄደና አስተናጋጆችን “ይህ የህንድ ውቅያኖስ አይደለም እንዴ?” ሲል ጠየቃቸው። “አይ! አይደለም ጌታዬ፤ የአውሮፓውያን መዋኛ ውቅያኖስ ነው። የሕንዶች መዋኛ ሌላ ቦታ ነው” ሲሉ መለሱለት።

የወደብ ከተማዋ “ኬፕ ታውን” በጣም የምታምር ናት። የከተማዋ ሰማይ በጠራ ሌሊት ከዚያ ሆነን ሮቤን ደሴት ላይ ያሉ መብራቶች ይታዩኛል። በዚያች ደሴት በመቶ የሚቆጠሩ ታዋቂ የደቡብ አፍሪካ ታጋይ ጥቁሮች ታስረው ይገኙ ነበር። በሮቢን ደሴት ከታሰሩት መካከል ወደፊት በአገሪቱ የብዙኃን አመራር ሲመሠረት መሪ የሚሆኑት እነ ኔልሰን ማንዴላ፤ ዋልተር ሲሱሉ፤ ጐበን እምቤኪ ይገኙባቸዋል።

በደቡብ አፍሪካ የሚኖር ፈረንጅ አንድን ጥቁር ቤቱ ለመጋበዝ ቢፈልግ እንኳን ማስፈቀድ አለበት። የሚመለከተው የመንግሥት አካል ሳይፈቅድለት ቢጋብዘው ይቀጣል። ለብሔራዊ አንድነት የሚታገሉ ጥቁሮችን የነጮች መንግሥት እንደ ሽብር ፈጣሪና



ሻጥረኞች ይቆጥራቸዋል። በ1967 የወጣ ሕግ ሻጥር ይፈጽማል ተብሎ የተጠረጠረ ሰው ላልተወሰነ ጊዜ ይታሰራል ይላል። የጥቂት ነጮች መንግሥት ተቃዋሚዎችን ለማግለል ባወጣው ሌላ ሕግ ደግሞ ተቀናቃኝ የተባሉ ሰዎች ካሉበት ከተማ እንዳይወጡና በአንድ ጊዜ ከሁለት ሰው በላይ እንዳያነጋግሩ ይከለከላሉ። ጋዜጦችም እነሱን አነጋግረው እንዳይጽፉ ወይም መፃሕፍቶቻቸውን ጠቅሰው እንዳያትሙ ታግደዋል።

ከነጭ ደቡብ አፍሪካዊ ጋር ስለዘርና ቀለም ለመከራከር መሞከር ከግንብ ጋር እንደመወያየት ነው። በደቡብ አፍሪካ ያሉት ነጮች እንደሌሎች የአፍሪካ አገሮች ነጮች ሌላ አገር የላቸውም። አገራቸው አፍሪካ ብቻ ናት፤ ፓስፖርታቸው የደቡብ አፍሪካ ብቻ ነው። የፈረንሣይ፤ የደችና የጀርመን ዝርያ ያላቸውና ከሶስት መቶ ዓመት በፊት ወደዚህ የመጡ ቅድመ አያቶቻቸው የልጅ ልጆች ናቸው። ከራሳቸው በቀር ሌላውን ያለማመን፤ በግትርነት ራሳቸውን ብቻ የመውደድና ከሌላው ያለመደባለቅን የወሰኑ ናቸው። ሃይማኖት አጥባቂ ስለሆኑ በሰንበት ቀን ትያትር ቤቶችና ሆቴሎችን ሳይቀር የሚዘጉ ናቸው። በችግርና ለብቻቸው ከትውልድ ትውልድ መኖራቸው ጥንካሬና ጭካኔ አስተምሯቸዋል።

የደች ሠፋሪዎችና የእንግሊዝ ሠፋሪዎች ወደ ደቡብ አፍሪካ በመምጣት በመሬት ሲጣሉና ሲዋጉ ከኖሩ በኋላ በ1910 ሁለቱም የያዙትን ክልል በማዋሃድ የደቡብ አፍሪካ ኅብረት የሚል አቋቋሙ። በ1961 ደግሞ ከእንግሊዝ የጋራ ንብረት ሀገሮች በማፈንገጥ ደቡብ አፍሪካ የራሷን ሪፑብሊክ አቋቋመች። የደች ሰፋሪዎች (ቦርስ) ወይም ገበሬዎች ከእንግሊዝ ቅኝ ገዢዎች ጋር ያደረጓቸው ረጅምና መራራ ጦርነቶች የነፃነት ትግል ዓይነት ሆነው ብሔራዊ ስሜትን ፈጠሩ። አፍሪካነስ በሚል ስያሜ የሚታወቁት እነዚህ ዜጎች አፍሪካንስ የሚል ቋንቋቸውን እንዳይጠቀሙ በእንግሊዞች ተከልክለው ቆይተዋል።

በአፍሪካንስ ቋንቋ አፓርታይድ ማለት ልዩነት ሲሆን ሁሉም ዘር የተለየ ግብርና አስተዋጽኦ ስላለው በተለያየ ሁኔታና አቅጣጫ

መኖር አለበት ባይ ናቸው ። ሆኖም በተግባራዊ ሂደቱ ግን የነጮችን የበላይነት ለመጠበቅ የተዘረጋ ነው ። ስለዚህም በትምህርት ፣ በደመወዝና በኑሮ ሁሉ የጐላ ልዩነትና አድልኦ ይደረግባቸዋል ። ለምሳሌም መንግሥት ለነጮች ልጆች ትምህርት በዓመት ለአንድ ተማሪ 677 ዶላር ሲመድብ ፣ ለሌላ ቀለም (ክለርድ)277 ዶላር ፣ ለጥቁሮች ልጆች ደግሞ 66 ዶላር ብቻ ያወጣል ። በደመወዝ አከፋፈል ደግሞ ተመሳሳይ ሥራ ከሚያከናውኑ ውስጥ ለነጩ የማዕድን ሠራተኛ 16,630 ዶላር በዓመት ሲከፈለውና እንዲሁም ለብቻው የሚኖርበት ቤት ያለኪራይ ሲሰጠው ፣ ለጥቁር 2546 ዶላር ብቻ እየተከፈለው በተጨናነቁ የብዙ ሰዎች መኖሪያ ውስጥ እንዲያድር ይደረጋል ። በየሥራ ዘርፉ እንዲሁ የጐላ ልዩነት ይታያል ። ሕንዶችና ክልሶችም ከጥቁር የተሻለ ቢያገኙም ነጩ ግን ከእነሱም ሁለትና ሶስት እጥፍ ያፍሳል ።

በደቡብ አፍሪካ 24,500,000 ለሚሆኑ ጥቁሮች ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋት 13% ብቻ የሚሆነውና ልምላሜ የሌለው ደረቅ መሬት ሲሰጣቸው 4,500,000 ለሚሆኑ ነጮች ግን 85% የሚሆነው መላው ለም መሬት በ1937 በወጣ ድንጋጌ ተሰጥቷቸዋል ። በኋላም በ1982 የጥቁሮች ነፃ ግዛቶች በሚል የውሸት ነፃነት “ ባንቱስታን ” በሚል ስያሜ የተለያየ ዘርና ቀለም ያላቸውን ለመለያየት የተቀየሰ ቢሆንም በዓለም ኅብረተሰብ ተቀባይነት አላገኘም ።

በደቡብ አፍሪካ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ነጮች ከጠቅላላ ነጮች ቁጥር 40% ሲሆኑ የቀሩት 60% አፍሪካነርስ የሚባሉት የደች ዝርያ ነጮች ናቸው ። አፓርታይድን በጥብቅ የሚደግፉና የሚያራምዱም እነዚሁ ሲሆኑ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጀርመንን ደግፈው ሰልፍ ያካሄዱ ብቻ ሳይሆን በሁለተኛው የዓለም ጦርነትም በድምፅ ብልጫ ቢሸነፉም ሂትለርን የደገፉ የፓርላማ አባሎች ብዙ ነበሩ ።በድምጽ የተበለጡት 80 ለ 67 ነው ።

ባለፉት ዓመታት የዓለም ኅብረተሰብ በደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት ላይ የተለያዩ ማዕቀቦችና እገዳዎች አድርጎበታል ። በ1982



ከደቡብ አፍሪካ መንግሥት ጋር በወዳጅነት ፀንታ የቀረች እሥራኤል ብቻ ናት ። በደቡብ አፍሪካ 120,000 አይሁዶች ይኖራሉ ። ግንኙነታቸው የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው በሚለው የተመሠረተ ነው ።

የዓለም ኅብረተሰብ እያወገዛት ደቡብ አፍሪካ መኖር መቻል ብቻ ሳይሆን እየበለጸገች ሄዳለች ። ይህም የሆነው ምዕራባውያን አገሮች ዕቀባውን ሥራ ላይ ባለማዋል ኩባንያዎቻቸውን በዚያ ሥራ እንዲቀጥሉ በማድረግና የንግድ ልውውጥ በመቀጠላቸው ነው ። ዛሬ ምዕራቡ ዓለም ከሚሸምተው ወርቅ ሶስት አራተኛውን የምታቀርበው ደቡብ አፍሪካ ናት ። ከማቀዝቀዣ እስከ መኪና ሁሉን ነገር ትፈበርካለች ። ጨርቃጨርቅ ፣ ምግብ ፣ ልዩ ልዩ የፋብሪካ መሣሪያ አምርታ ለውጭ ገበያ ታቀርባለች ። በዚህ ላይ በዓለም አሥረኛዋ የጦር መሣሪያ አምራች አገር ናት ። የጦር መሣሪያዎቹ የሚመረቱት በጥቁሮች ላብ ቢሆንም የነጮችን አገዛዝ ለማቆየት ከፍተኛ ድርሻ የሚያበረክተው ይኸው የመሣሪያ ብዛትና ጥራት ነው ።

ደቡብ አፍሪካ ሁሉም ዘሮች ተደባልቀው በሰላም አብረው የሚኖሩበት ኅብረተሰብ የግድ መፍጠር አለባት ። ይህ ለውጥ በሰላምና በውይይት ሊመጣ ካልቻለ በኃይል በደም መፋሰስና በአያሌ ንብረት መውደም መምጣቱ ግድ ይሆናል ። ይህን ለማስቀረት አሜሪካ ሚና ልትጫወት ትችላለች ። በዚያ የሚሠሩ 350 ኩባንያዎቿን ብታስወጣ ወይም ለጥቁሮችም እኩል ክፍያ እንዲሰጡና በሙያውም እንዲያሰለጥኗቸው ብታስገድድ ውጤት የሚኖረው ተጽዕኖ ልታደርግ ትችላለች ። በዚህ ላይ አሜሪካ በየዓመቱ ከደቡብ አፍሪካ በብዙ ቢሊዮን ዶላር የሚገመት የንግድ ልውውጧን ብታቆምና መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ በግንባታ ከመርዳት ብትታቀብ ግፊቱ ከፍተኛ ይሆናል ።

ይህ ግን የሚሳካ አይመስልም ። ምክንያቱም የኢኮኖሚ እቀባውን የሚያፈርሱ አገሮችና ኩባንያዎች አይጠፉም ። ሁለተኛም የደቡብ አፍሪካ ኢኮኖሚ ቢያቆለቁል በመጀመሪያ ተጐጂዎች ጥቁሮች እንጅ ነጮች አይሆኑም ። ሶስተኛ የአሜሪካ ኩባንያዎች እንዲወጡ ዋሽንግተን ትዕዛዝ ቢሰጥ የደቡብ አፍሪካ መንግሥት ገንዘባቸውን

ከባንክ እንዳያወጡ ማገዱ የማይቀር ነው ። በዚህ ላይ ፈረንሣይ
ወይም ጃፓን ዘው ብለው በመግባት በንግድ ገበያው የአሜሪካን
ድርሻ አከሲዮን ሊወስዱ ይችላሉ ። አራተኛ አሜሪካ የንግድ ግንኙ
ነቷን ብታቋርጥ ብዙ ኪሣራ ላይ ትወድቃለች ። አምስተኛውም
የጥቁር አፍሪካ አጐራባች አገሮች ለጥቅም ሲሉ ከደቡብ አፍሪካ
ጋር ንግዳቸውን ከቀጠሉና ራሳቸው መውሰድ ያቃታቸውን ርምጃ
ሌላው እንዲወስድ ከጠየቁ ትርጉም አይኖረውም ።

ስለዚህም ዋሽንግተን ማድረግ ያለበት የተሻለው አማራጭ
የራሷ ኩባንያዎች ጥቁሮችን በእኩልነት በመያዝ እኩል ክፍያና ሥል
ጠና በመስጠት ፣ በየፋብሪካው የዘር መድሎን በመተውና ጥቁሮችን
ወደ ሥልጣን ከፍ በማድረግ የአፓርታይድ ሥርዓት መፍረሱ እንደ
ማይቀር ማሳየት ነው ።

በመጨረሻም ለአፍሪካነሩ ነጮች የበላይነት ጥንካሬውን የሰ
ጠው አፓርታይድ ራሱን የሚያጠፋ ሊሆን ይችላል ። በኢንዱስትሪ
የበለፀገ አገር በመሆኑ የሚያስፈልገውን ሙያና የአገልግሎት ሥራ
ሁሉ ነጮች ብቻ ሊያሟሉ አይችሉም ። ስለዚህ እድል ሲነፈጉ የነበ
ሩት ጥቁሮች ዛሬ ለእድገቷ መቀጠል እጅግ አስፈላጊ ስለሆኑ በየሙ
ያው ተሠማርተዋል ። ነጮች ይህን ሥርዓት ለመጠበቅ ከፍተኛ ሚሊ
ተሪያዊ ኃይልና የኑክሌር አቅም ሳይቀር ገንብተዋል ። ነገር ግን ፈተ
ናው ከውስጥ ከራሳቸው ሕዝብ ስለሆነ ምርጫቸው ሁለት ነው ።
በአገራቸው ላይ ቦምብ በማዝነብ የራሳቸውን ሕልውና ማጥፋት
ወይም የማይቀረውን ለውጥ መቀበል ነው ። ብዙሃኑን ጥቁሮች በባር
ነት ሠንሰለት ቀፍድደው የተደላደለና ዓለም የሚቀናበት ደረጃ ላይ
ደርሰዋል ። የሮቢን ደሴት እሥር ቤት ሞልቷል ፣ ታዲያ አዲሱን የተ
ማሩ ጥቁሮች ትውልድ የት ሊያደርጉት ነው ? የዛሬው ትውልድ
ደግሞ ከአባቶቹ የባሰ ትዕግሥት ስለሚያንሰው በዝምታ አይመለከ
ታቸውም ።

ስለዚህም የሚበጀው በሰላማዊ መንገድ የተለያዩ በርካታ ዘር
ችና ቀለሞች ያሏቸው የደቡብ አፍሪካ ነዋሪዎች በጋራ ተባብረውና



እጅ ለእጅ ተያይዘው በእኩልነት ላይ የተመሠረተ ሁሉን አቀፍ
ኅብረተሰብ መመሥረት ነው ። ብቸኛው አማራጭም ይኸው ነው ።

ይህም በ1984 መልካም ጅምር አሳይቷል ። ደቡብ አፍሪካ ከሞዛም
ምቢክና ከአንጐላ ጋር ወረራ ባለማካሄድ መስማማቷና ለሰላም መፈ
ጠር የሚበጁ እቅጣጫዎችን መወያየታቸው ተስፋ የፈነጠቀ ጅምር
ነው ። ይህ ከዘለቀ ደቡብ አፍሪካም በአፍሪካ የተከበረ ቦታ ይኖራ
ታል ። በበኩሏም አፍሪካን በቴክኑክና በኤኮኖሚ በማገዝ በአህጉሩ
የሚፈለገው አገልግሎት ሁሉ እንዲሟላ ልታደርግ ትችላለች ። ስለዚ
ህም የደቡብ አፍሪካ ነጮች በዚምባብዌ የተደረገውን ሰላማዊ ሽግ
ግር እንደ ምሳሌ በመውሰድ ጊዜ ሳያመልጣቸውና የንብረት መው
ደምና ደም መፋሰስ ሳይመጣ ውሳኔ ማድረግ ይኖርባቸዋል ።

## ምዕራፍ አሥራ ሰባት

# ያለፈውን በማጤን የወደፊቱን ስንቃኝ

« በካፒታሊዝም ውስጥ ያለው መጥፎ ነገር ሀብትን እኩል መካፈል አለመቻል ነው ፤ በሶሻሊዝም ውስጥ ያለው መልካም ነገር ችግሮችን እኩል መካፈል ነው ። »

— ዊንስተን ቸርቺል

አራቱ ዓመት ምን ጊዜ እንዳለፈ ሳናውቀው እኔና ባለቤቴ ሳንዲ በእኩለ ሌሊት ከናይሮቢ ተነስተን አፍሪካን በመሰናበት ወደ ሮም ተጓዝን ። ከምወዳቸው ሰዎችና ሥፍራዎች መለየትን ጊዜያዊ አድርጌ ስለምመለከተው መሰናበት አልወድም ። ስለዚህም እኔና ሳንዲ ያለመ ሰናበቻ ድግስ ድምፃችንን አጥፍተን ከናይሮቢ በሹልክታ ወጣን ። ጓዛችንን ከአሰናዳን በኋላ በመኖሪያ ቤታችን ሳሎን የእሳት መሞቂያ አጠገብ ቆም ብዬ በየምሽቱ በዚያ እየተሰበሰቡ ስለአፍሪካ የሚ ያወያዩኝ ጓደኞቼን ውካታ አሰብሁ ። አፍሪካ ምን ደረጃ ላይ ናት ? ወዴትስ ነው የምትጓዘው ? እያልን እንወያይ ነበር ። አፍሪካን ለጊዜው መቆያ ቦታ ብቻ አድርገን ልንመለከት አልቻልንም ።አፍሪካ ፍቅር አሳድራብናለች ። ከአእምሯችንም የማትጠፋ ሆናብናለች ። አፍሪካን ልትወዳት ወይም ልትጠላት ትችላለህ ፤ ስለእሷ ደንታ ቢስ ልትሆን ግን አትችልም ።

በአፍሪካ ቆይታየ በየአገሮቹ ስዘዋወር ያደረግሁትን ጥናትና የጽሁፎች ስብሰብ በአንድ ትልቅ ካርቶን አሽጌ ለንደን ያለው የሉይ ድስ ኩባንያ የሃያ ሺህ ዶላር ዋስትና መድን እንዲገባለት አድርጌ አለሁ ። ያሰባሰብኳቸውን ጽሁፎች ፤ የጻፍሁባቸውን ማስታወሻ ደብ

ተሮች ፣ ካርታዎችንና ፎቶግራፎችን ያደረግሁበትን ካርቶን እንዱ ይሰርቀኛል ብሎ ለማሰብ የማይቻል ቢሆንም ሎስ እንጀለስ ደርሶ ሲራገፍ እስካየው ድረስ የሕሊና እረፍት አልነበረኝም ። በማግስቱም አሜሪካ እንደገባሁ በመጀሪያ የፃፍሁበትን ማስታወሻ ደብተር ጉርጉሬ አወጣሁ ። ጆሞ ኬንያታ ለኬንያ ሕዝብ ንግግር ሲያደርጉ የወሰድሁት ማስታወሻ ነበር ። የኬንያታ ቀን እየተባለ በሚጠራው ብሔራዊ በዓል ላይ ካደረጉት ንግግር በማስታወሻዬ የከተብሁት ነው ። በነገራችን ላይ ይህ ክብረ በዐል በ1952 ኬንያታ በእንግሊዞች የታሰሩበትን ቀን የሚያስታውስ ነው ። እንዲህ የሚል ጽሁፍ ሜሞሬበት ነበር ። " ሕዝቡ ፀጥ ብሏል ፣ እረጭ . . .ጆ/ኬ በቆዳ ጃኬት . . .በቀኝ እጅ ጭራ . . .ትኩር ብለው ይመለከታሉ ፣ ድምፃቸው የሚያስተጋባ ነጐድጓዳዊ . . .ግርማ ሞገስ የተላበሱና የሚያፈዙ ። እንዲህ ሲሉ የተናገሩትን ቃል በቃል ዘግቤው ነበር ። " በታሪክ ውስጥ ከአንድነት በስተቀር ለሰብዓዊ መብት መከበር ለመታገል የሚረዳ ሌላ የላቀ መሣሪያ አልነበረም ። "

አሁን ኬንያታ ሞተዋል ፣ አብዛኞቹ አፍሪካን ከቅኝ አገዛዝ ወደ ነፃነት የመሩ ሰዎች አልፈዋል ፣ በሰብዓዊ ፍትህ መንደል ላይ የሰው ልጅ የተቀዳጀውን አንድ ታላቅ ድል የሚያስታውሱን ናቸው ።ነገር ግን በዚች በቆሰለች አህጉር ኬንያታ የተናገሩለት አንድነት ግልጽ ያልሆነ ሕልም ሆኖ ቀርቷል ። የሰብዓዊ መብቶች በእኩልነት መከበር ጉዳይም ለመስበክ ቀላል ለመፈጸም ግን አስቸጋሪ መሆኑ ተረጋግጧል ።

ገና ብዙ ሥራ ይቀራል ። ከሰላሣ ዓመታት በፊት ኬንያታ በእሥር ቤት እንዳሉ ጆን ፣ ጉንተር የተባለ ደራሲ " ኢንሳይድ አፍሪካ " (በአፍሪካ ውስጥ ) በተሰኘው መጽሐፉ እንዲህ የሚል አስፍሯል ። "አፍሪካ የሚያስፈልጓት ሁለት ነገሮች ልማትና ትምህርት ናቸው ።" ዛሬም ያ ፣ እውነት እንዳፈጠጠ ነው ። ወደ አሜሪካ ተመልሼ ሁኔታዎችን ሳመዛዝን በበለጸጉት የኢንዱስትሪ አገሮችና በዶግ በሚያርሰው ሶስተኛው ዓለም መካከል ያለው ልዩነት ለማመን የሚያስቸግር ነው ። ምዕራቡ ይህን ልዩነት ማጥበብ አለበት የሚል ሙሉ እምነት



አድርብኛል ። ዋጋ ያለው ዓለምአቀፍ ውድድር የሁሉንም ሰዎች ችሎታ የማሳደግ ሩጫ ነው ። የአፍሪካ አገሮችን ከማርዳት ይልቅ ቸል ማለትን መምረጥ ወደ ሶቪዬት ካምፕ እንዲነጉዱ መተው ነው ። ለአፍሪካ ችግሮች ቦታ አለመስጠት ፣ ዓለምአቀፍ ችግርን ፣ ረሀብን ፣ አለመረጋጋትን ፣ ግራመድና የዓለምን ሰላም የሚያሰጉትን ነገሮች ማባባስ ነው ።

አፍሪካ እንድትለማና ተዝቆ የማያልቅ የተፈጥሮ ቅምጥ ሀብቷን ተገንዝባ ለሕዝቦቿ እድገት እንድታውል ማስወገድ ያለባትን መሰናክሎች በስፋት ጽፌአለሁ ። ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ወሊድ ፣ የምግብ ምርት መቀነስ ፣ የጤና ችግር ፣ ብቃት የሌለው አመራር (ተቀዳሚ ዓላማቸው ለራሳቸው ሥልጣን ዘላቂነት የሆነ ) ፣ ከተሞችን የሚያዳክም ከገጠር ፈልሶ የመከማቸት ዘመቻ ፣ ያልሰለጠነና ሙያ የሌለው ሕዝብ ፣ ለተማሩት ዕድል ያለመስጠት ፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት ፣ በሥልጣን መባለግና ይፋ ምዝበራ ፣ ጉቦ ፣ በዘረኝነት ላይ የተመሠረተ አድልኦ የአፍሪካ ነቀርሳዎች ናቸው ።

ብዙዎቹ አገሮች የሚፈለገውን ብሔራዊ የኢኮኖሚ ግንባታ ለማሟላት ያልቻሉት ሠራተኞች የምርት ማበረታቻ ስለማይሰጣቸው ነው ። ቅኝ ገዢዎች ጥለውት ከሄዱት ነገር ሁሉ ለመላቀቅ ሲሉ መንግሥታት ሶሻሊዝምን ብሎም ማርክሲዝምን በመምረጥ ሕዝቡ ለራሱ ከመሥራት ይልቅ ለኅብረተሰቡ የጋራ ጥቅም ይሠራል በሚል የተሳሳተ እምነት ተጓዙ ። የኢኮኖሚ ተቋሞች ሁሉ ተወርሰው የሠራተኛው የምርት ማበረታቻ ጉርሻ ሁሉ ተወገደ ።

የታንዛንያ ፕሬዚዳንት ጁሊየስ ኔሬሬ በአንድ ወቅት እንዲህ ብለዋል ። " ታዳጊ አገሮች ሶሻሊዝምን ካልመረጡ በደካማነት ይቀጥላሉ ፣ ይንጓጠጣሉ ፣ ይጨቆናሉ ፣ ይበዘበዛሉ ።የምንዋጋው ካፒታሊዝምን ነው ። "

ዛሬም በዚህ እምነታቸው የፀኑ ቢሆንም የኒሬሬ ሙከራ በነፃዋ አፍሪካ የታየ ታላቅ ውድቀትና ለሌሎች አገሮችም ትምህርት መሆን የሚገባው ነው ። ከወረሷቸው 330 ኩባንያዎች መካከል ግማሹ

በአሥር ዓመት ዕድሜ ከስረው ተዘጉ ። በታንዛንያ መዋዕለ ንዋይ
ምደባ ቦርድ ጥናት መሠረት ከ1969 እስከ 1979 ባለው ጊዜ የሠ
ራተኛ ምርታማነት 50% ቀንሰ ። የመንግሥት ቢሮክራሲያዊ መዋቅር
በየዓመቱ 14% ያድጋል ። የመንግሥት ወጪዎችም ከብሔራዊ ምርቱ
በሁለት እጅ እያደጉ ሄዱ ። ኒሬሬ ያላስተዋሉት ጉዳይ አፍሪካውያን
ራሳቸውን ለመመገብ ብቻ መሥራት የሌለባቸው መሆኑን ነው ።ከዚህ
አኳያ ደግሞ ሶሻሊዝም መጥፎ አማራጭ ነው ። ለሙ አፈርና ተስማ
ሚው የአየር ጠባይ በቀላሉ ሆድን መሙላት የሚያስችል ምግብ ያስ
ገኛል ። ለምርት ማበረታቻ ይሰጥ የነበረውን የገንዘብ ጉርሻ ስታስቀር
ባቸው ሠራተኞች እንደወትሮው ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው ብቻ
የሚበቃ ምርት እያበቀሉ ይኖራሉ ።

የዩናይትድ እስቴትስ 5,500,000 የእርሻ ሠራተኞች እያንዳንዳ
ቸው ለስድሳ ስምንት ሰው የሚበቃ ያመርታሉ ። (ከአሥር ዓመት
በፊት ለአርባ አምስት ሰው ብቻ ነበረ) ። ይህ የአሜሪካ የእርሻ መም
ሪያ ዘገባ ነው ። አፍሪካ 200,000,000 አራሾች አሏት ፤ በተሳካላ
ቸው ጊዜ የተሻለ አመረቱ የሚባለው የራሳቸውን ሆድ እንኳን በወጉ
የማይሞላ ነው ። አፍሪካ ሶሻሊዝምን በአስቸኳይ ትታ የአሜሪካ ዓይ
ነት ካፒታሊዝም ትከተል ማለቴ አይደለም ። ነገርግን እንደማስበው
አፍሪካ የፖለቲካ እና የማኅበራዊ አወቃቀሯን ለመለወጥ ከመቻሏ
አስቀድሞ የኤኮኖሚ ጤንነቷን ልታሻሽል ይገባል ። ወደዚያ አቅ
ጣጫ የመጀመሪያው ርምጃ ደግሞ ቅይጥ ኤኮኖሚ በመፍጠር የበ
ለጠ ጠንክሮ ለመሥራትና የላቀ ለማምረት ግፊት የሚሰጡ ምቹ ሁኔ
ታዎች መቀየስ ነው ።

ምዕራቡ ዓለም አፍሪካ የተያያዘችውን ራሷን የማጥፋት ጉዳና
ለመለወጥ ትልቅ ሚና ለመጫወት ይሻል ። ለሰብዓዊ ምክንያቶች
ብቻም አይደለም ። የአፍሪካ የማዕድን ሀብት ፣ የእርሻ ምቹነት ፣ እስት
ራቴጂያዊ አቀማመጧ ፣ በነገዋ ዓለም ክስተቶች ተሰሚነት የሚኖራት
እንደምትሆን የሚጠቁሙ ናቸው ። ራስን ለማገልገል ሲባል ብቻ ከድ
ሆችም ድሃ ለሆነችው እውቀቱንና ገንዘቡን ቢያካፍል ለምዕራቡ
ጥቅም ነው ። ምክንያቱም አፍሪካ የዓለም ኅብረተሰብን ሀብት በምዕ



ዋተኝነት ከምታሟጥጥ ሌላውን የሚረዳ አስተዋጽኦ ያላት ብትሆን
ጠቀሜታው ለሁሉም ነውና ።

የምዕራቡ እርዳታ በሙያ ሥልጠና ላይ ሊያተኩር ይገባል ።
አፍሪካ ሜካኒኮች ያስፈልጓታል ፤ የሕክምና ቴክኒሽያኖች ትሻለች ።
በአሁኑ ደረጃዋ የልብ ቀዶ ሕክምና የሚያደርጉ ብትሻ ቅንጦት ነው ።
ትኩረቱም በገጠር ልማት መሆን አለበት ። በአፍሪካ ከሚመረተው
የምግብ እህል 30% የሚያድርሰው በኀተራ አሠራር ድክመትና በትራን
ንስፖርት ችግር እየተበላሸ ምዕራቡም ሆነ ምሥራቁ አውሮፕላን
ማረፊያ በመስራትና ጦር መሣሪያ በማቀበል መርዳታቸው ከወንጀል
ያነሰ አይደለም ። ለአፍሪካ የሚላከው ርዳታ በብክነትና ሥርቆት ስለ
ሚጠፋ የበጐ አድራጊዎችን ሕሊና ከሚያዝናና በስተቀር የሚፈይ
ደው ጥቂት ነው ። ለምሳሌ አሜሪካ ለሴኔጋል ጥራጥሬ እህል ምርት
ፕሮጀክት 4.600.000 ዶላር አወጣች ፤ ነገርግን ምርቱን በሄክታር
አንድ ስልቻ እንኳን አላሳደገውም ። ለማላዊ የከብት ሀብት ልማት
ደግሞ ሌላ 13.000.000 ዶላር ሰጠች ፣ ግን የተገኘ ውጤት የለም ።
ሶማሊያ ደግሞ በአንድ ወቅት ከምዕራብ ጀርመን 12.000.000 ዶላር
የሚያወጣ የርዳታ ዕቃ ሲመጣላት ቀረጡን ጭምር በጐ አድራጊው
ድርጅት ካልከፈለ አይገባም አለች ። የጀርመን መንግሥት ተወካይ
በበኩሉ " ርዳታ ስለሆነ እንዴት ቀረጥ ያውም በጐ አድራጊው ራሱ
እንዲከፍል ይጠየቃል" ሲል ተከራከረ ። "ምንም ግንኙነት የለውም ፤
ቀረጡን ካልከፈላችሁ አይሆንም " በማለት የሶማሊያ ተወካይ ግትር
አቋም ወሰደ ። ይህን የመሳሰሉ ብዙ ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል ።
እንዲያም ሆኖ የዓለም ዓቀፍ ርዳታ አስተሳሰብ ጥሩ ሆኖ ቀጥሏል ።
ለአፍሪካ ልማት ርዳታ ጠቃሚም አስፈላጊም ነው ። ውድቀቱ የመ
ጣው ገንዘቡ በአግባቡ ሥራ ላይ ስለማይውልና ቅጥ ባጣ ሁኔታ ስለ
ሚባክን ነው ።

አፍሪካን የገጠሟትን ችግሮች ስንመለከት የአፍሪካ አገሮች ገና
በቅርቡነፃ የወጡ ታዳጊዎች መሆናቸውን እንረሳለን ። ምናልባትም
ዓለም በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሚገባው በላይ ውጤት እንዲጨብጥ ጠብቆ
ይሆናል ። ከጅምሩ ለአፍሪካ በነበረው ድጋፍና የቃላት ቷስፋ ተመስ

ስጠን ሊሆንም ይችላል ። ምዕራቡ ዓለም አፍሪካ ራሷን እንጅ ሌላውን ለመሆን አለመፈለጓን ወደ ጐን በመተው "እንደኛ እንዲሳከላቸሁ እንደእኛ ሁኑ " በማለት ጠየቀ ። የአፍሪካን መደንቃቀፍ ስንተችም በ1796 የናይትድ ስቴትስ ምዝበራ የተጧጧፈባት ፤ የፖለቲካ አንድነትና ብሔራዊ ብልጽግና የሩቅ ግቦች የሆኑባት ፤ ወደ እርስ በርስ ጦርነት የምታመራ አገር እንደነበረች አናንሳም ።

በአሁኑ ወቅት የአህጉሪቱ የወደፊት እድል ቁልፉ በደቡብ አፍሪካ ሰላማዊ ሽግግር መፈጠር ነው ። በደቡብ አፍሪካ ብዙ ዘሮች በአንድነትና በእኩልነት ተባብረው የሚኖሩበት ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ ለአፍሪካ ዘላቂ መፍትሔ ሊገኝ አይችልም ። ደቡብ አፍሪካ ከጐረቤቶችዋ ጋር መልካም ግንኙነት ቢኖራት እነዚያ አገሮች ከእጧ ምግብ ፤ ኢንዱስትሪ ፤ ጠበብትና የሥራ ቅልጥፍናና ጥራት ስለሚያገኙ የደቡባዊው የአፍሪካ ክፍል የኢኮኖሚ ባህርይ በሚያስደንቅ ሁኔታ ይለወጣል ። ከዚያም የቀረው ነገር ሁሉ ይስተካከላል ። ለፖለቲካ መረጋጋት ቀዳሚው አስፈላጊ ጉዳይ በኢኮኖሚ ራስን መቻል ነው ። የተማረውና ጥሩ ኑሮ ያለው ሕዝብ መበራከት ፣ የጤና ሁኔታ መሻሻል ፣ የወሊድ ቁጥጥር ወዘተ ሁሉ ከዚያ ተከትለው የሚመጡ ናቸው ።

በደቡብ አፍሪካ የጥቂት ነጮች አገዛዝ ሲያበቃ ፤ (ያከትማልም !) ጥያቄው በምን ዓይነት ሁኔት የሚለው ነው ፤ ያኔ ጥቁር አፍሪካ ችግሮቿን ለመቅረፍ የማትችልበት ምድራዊ ምክንያት አይኖርም ። አፍሪካ እየሰለጠነችና የበለጡ ከተሞች ሲስፋፉባት የዘረኝነት ስሜት እየደበዘዘ ይሄዳል ። ብሔራዊ ግቦችን በሙሉም ረገድ እያደገ የሚመጣው የተማረው ወጣት ተደማጭነትና ድርሻ እንዲኖረው በጠየቀ ቁጥር የአገሮች አመራርም የበለጠ ብቃት ያለው እየሆነ ይመጣል ። በአመዛኙ በጭብርባሮና በእድሉ ራሱን የመሠረተው ጥቂቱ ተማርሁ የሚለው ክፍልም እያደገ ለሚመጣውና በግል ችሎታ ፣ በትምህርት ፤ በታማኝነት ፤ በጥረት በተገኘ ገንዘብ በማያምን ፤ በሕጋዊነት ላይ በተመሠረተ የተማረ ኅብረተሰብ ሳይወድ በግድ ይተካል ።አዲስ ብሔራዊ ስሜት ሊከሰትም ይችላል ፤ ይህም በቅኝ ገዥዎች ላይ በተገኘ ድል ላይ ብቻ የተመሠረተ ሳይሆን በብሔራዊ ግኝቶች በመኩራት የተመሠረተ ይሆናል ።

የተሳፈርንበት አውሮፕላን በኬንያ ሰሜናዊ አየር እየተንሳፈፈ ሲያልፍ አፍሪካውያን በየአገሩና በተደጋጋሚ " ጊዜ ስጡን ፤ ገና ጀማሪ ነን ፣ " ያሉኝ ትዝ አለኝ ። ተገቢና ምክንያታዊ ጥያቄ መስሎኛል ።

# እስታቲስቲካዊ ገፅታ

| | አገር | ዋና ከተማ | ቅኝ ገዢ | ነፃነት | ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ በዶላር | ዋና የገቢ ምንጭ | የሕዝብ ብዛት በስኩዌር ማይልስ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አልጀሪያ | አልጀርስ | ፈረንሣይ | 1962 | 1260 | ነዳጅ | 20 |
| 2 | አንጎላ | ሉዋንዳ | ፖርቱጋል | 1975 | 300 | ነዳጅ | 14 |
| 3 | ቤኒን | ኮቶኑ | ፈረንሣይ | 1960 | 230 | ጥጥ | 78 |
| 4 | ቦትስዋና | ጋቦሮኒ | እንግሊዝ | 1966 | 620 | አልማዝ | 3 |
| 5 | ብሩንዲ | ቡጁምቡራ | ቤልጅግ | 1962 | 140 | ቡና | 372 |
| 6 | ካሜሩን | ያውንዴ | ፈረንሳይ/ እንግሊዝ | 1960 | 460 | ካካዋ | 44 |
| 7 | ኬፕ ቨርዴ | ፕራያ | ፖርቱጋል | 1975 | 160 | ሸንኮራ | 199 |
| 8 | ማዕከላዊ/አ | ባንጊ | ፈረንሣይ | 1960 | 250 | አልማዝ | 11 |
| 9 | ቻድ | እንጃሜና | ፈረንሣይ | 1960 | 140 | ኩበት | 9 |
| 10 | ኮሞሮስ | ሞሮኒ | ፈረንሣይ | 1975 | 180 | ኮከነት | 577 |
| 11 | ኮንጎ | ብራዛቪል | ፈረንሣይ | 1960 | 780 | ነዳጅ | 11 |
| 12 | ጅቡቲ | ጅቡቲ | ፈረንሣይ | 1977 | 450 | ርዳታ | 12 |
| 13 | ግብጽ | ካይሮ | እንግሊዝ | 1922 | 400 | ጥጥ | 109 |
| 14 | ኢኳቶሪያል ጊኒ | ማላቦ | እስፓኝ | 1968 | 100 | ካካዋ | 32 |
| 15 | ኢትዮጵያ | አዲስ አበባ | | | 120 | ቡና | 65 |
| 16 | ጋቦን | ሊበርቪል | ፈረንሣይ | 1960 | 3600 | ነዳጅ | 5 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | ጋምቢያ | ባንጁል | እንግሊዝ | 1965 | 230 | ለውዝ | 142 |
| 18 | ጋና | አክራ | እንግሊዝ | 1957 | 400 | ካካዋ | 119 |
| 19 | ጊኒ | ኮናክሪ | ፈረንሳይ | 1958 | 210 | ቦክሳይት | 50 |
| 20 | ጊኒ ቢሳው | ቢሳው | ፖርቱጋል | 1974 | 200 | ለውዝ | 39 |
| 21 | አይቮሪ ኮስት | አቢጃን | ፈረንሳይ | 1960 | 1000 | ካካዋ | 61 |
| 22 | ኬንያ | ናይሮቢ | እንግሊዝ | 1963 | 320 | ቡና | 66 |
| 23 | ሌሶቶ | ማሴሩ | እንግሊዝ | 1966 | 280 | ሽቀላ | 109 |
| 24 | ላይቤሪያ | ሞንሮቪያ | — | 1847 | 460 | ጎማ | 40 |
| 25 | ሊቢያ | ትሪፖሊ | ጣሊያን | 1951 | 7000 | ነዳጅ | 4 |
| 26 | ማዳጋስካር | ታናናሪቭ | ፈረንሳይ | 1960 | 250 | ቡና | 37 |
| 27 | ማላዊ | ሊሎንግዌ | እንግሊዝ | 1964 | 180 | ትንባሆ | 124 |
| 28 | ማሊ | ባማኮ | ፈረንሳይ | 1960 | 120 | ከብት | 14 |
| 29 | ሞሪታንያ | ኖአክሾት | ፈረንሳይ | 1960 | 270 | ከብት | 4 |
| 30 | ሞሪሽየስ | ፖርት ሉዊስ | እንግሊዝ | 1968 | 830 | ሸንኮራ | 1169 |
| 31 | ሞሮኮ | ራባት | ፈረንሳይ | 1956 | 670 | ፎስፌት | 110 |
| 32 | ሞዛምቢክ | ማፑቶ | ፖርቱጋል | 1975 | 140 | ካሺው ነትስ | 33 |
| 33 | ናሚቢያ | ዊንድሆክ | ደ/አፍሪካ | 1990 | 1080 | አልማዝ | 3 |
| 34 | ኒጀር | ኒያሚ | ፈረንሳይ | 1960 | 220 | ለውዝ | 10 |
| 35 | ናይጄሪያ | ሌጎስ | እንግሊዝ | 1960 | 560 | ነዳጅ | 202 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 36 | ሩዋንዳ | ኪጋሊ | ቤልጅግ | 1962 | 180 | ቡና | 444 |
| 37 | ሳኦቶሜናፕሪንችፔ | ሳኦቶሜ | ፖርቱጋል | 1975 | 490 | ካካዋ | 215 |
| 38 | ሴኔጋል | ዳካር | ፈረንሣይ | 1960 | 340 | አኩሪ አተር | 71 |
| 39 | ሲሼልስ | ቪክቶሪያ | እንግሊዝ | 1976 | 1060 | ቱሪዝም | 351 |
| 40 | ሴራሊዮን | ፍሪታውን | እንግሊዝ | 1961 | 210 | አልማዝ | 118 |
| 41 | ሶማሊያ | ሞቃዲሾ | ጣሊያን እንግሊዝ | 1960 | 130 | ከብት | 14 |
| 42 | ደቡብ አፍሪካ | ፕሪቶሪያ | — | 1910 | 1480 | ወርቅ | 59 |
| 43 | ሱዳን | ካርቱም | እንግሊዝ ግብጽ | 1956 | 320 | ጥጥ | 18 |
| 44 | ስዋዚላንድ | እምባባኒ | እንግሊዝ | 1968 | 590 | ሸንኮራ | 81 |
| 45 | ታንዛንያ | ዳሬሰላም | እንግሊዝ | 1961 | 230 | ቡና | 46 |
| 46 | ቶጎ | ሎሜ | ፈረንሣይ | 1960 | 320 | ፎስፌት | 110 |
| 47 | ቱኒዝያ | ቱኒዝ | ፈረንሣይ | 1956 | 950 | ነዳጅ | 96 |
| 48 | ኡጋንዳ | ካምፓላ | እንግሊዝ | 1962 | 200 | ቡና | 140 |
| 49 | ቡርኪናፋሶ | ኦጋዱጉ | ፈረንሣይ | 1960 | 160 | ሸቀላ | 62 |
| 50 | ምዕራብ ሰሃራ | ኤልአዩን | እስፓኝ | — | 200 | ፎስፌት | 0.7 |
| 51 | ዛየር | ኪንሻሳ | ቤልጅግ | 1960 | 210 | መዳብ | 31 |
| 52 | ዛምቢያ | ሉሳካ | እንግሊዝ | 1964 | 480 | መዳብ | 19 |
| 53 | ዚምባብዌ | ሐራሬ | እንግሊዝ | 1980 | 480 | ክሮም | 46 |